# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

## ክፍል አራት (Volume - 4)

### በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ኢዴፓ የሚያራምደው አቋም

(ረቂቅ - ፩)

ሰኔ 1995 ዓ.ም

## ብርቱ ማሳሰቢያ፣

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፣ ኢዴፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፣ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል — 4

# በግብርና፣ በኢንዱስትሪና በልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ የኢዴፓ ሀሳቦች

## 1. ግብርና

### 1.1 የግብርናው ዘርፍ ሁኔታ

ኢትዮጵያ የአፈር፣ የውሃ፣ የልዩ ልዩ ብዝሀ ሕይዎትና ሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ክምችት ባለቤት ናት:: አጠቃላይ የቆዳ ስፋቷም 111.5 ሚሊዮን ሄክታር እንደሚሆን የሚገመት ሲሆን ለግብርና ሥራ አመቺነት አለው ከሚባለው 77.6 ሚሊዮን ሄክታር የአገሪቱ መሬት ውስጥ እስከአሁን ለሰብል ጥቅም የዋለው 16.5 ሚሊዮን ሄክታር ያህል ነው::

በአገራችን የሚታረሰው መሬት መጠን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ መጥቷል:: በዝርዝር ሲታይም ከ1967 እስከ 1974 ዓ.ም በአማካይ ለዋና ዋና የሰብሎች እርሻ የዋለው መሬት 5.2 ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን ከ1975 አስከ 1983 ዓ.ም በአማካይ 5.3 ሄክታር ነበር:: እንዲሁም ከ1984 እስከ 1992 ዓ.ም በአማካይ 6.8 ሚሊዮን ሄክታር ነበር:: ይሁን እንጂ የነፍስ ወከፍ የመሬት ይዞታ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መጥቷል:: ከ1967 እስከ 1974 ዓ.ም በአማካይ ለዋና ዋና የሰብሎች እርሻ የዋለው መሬት የነፍስ ወከፍ ድርሻ 0.15 ሄክታር ሲሆን ከ1984 እስከ 1992 ዓ.ም አማካይ የነፍስ ወከፍ ድርሻ ወደ 0.12 ሄክታር ዝቅ ብሎ ነበር::

በሌላ በኩል ደግሞ ከ1967 ዓ.ም እስከ 1992 ዓ.ም ያለውን ዋና ዋና የሰብል ምርትን ሁኔታ ስንመለከት ወሳኝ ነገሮችን መገንዘብ ይቻላል:: አንደኛ ከ1967 አስከ 1974 ዓ.ም፣ ሁለተኛ ከ1975 አስከ 1983 ዓ.ም እና ሦስተኛ ከ1984 አስከ 1992 ዓ.ም ያለው ጊዜ ከአንድ ሄክታር በአማካይ የተመረተው የምርት መጠን በኩንታል ስንት እንደነበር ሲታይ፤ ጥራ ጥሬ (ማለትም ባቄላ፣ አተር፣ አደንጓሬ፣ ሽምብራ፣ ምስር) 9.4፣ 8.4 እና 7.2 ሲሆን፤ ጤፍ ደግሞ 8.1፣ 8.8 እና 8.7 ነበር:: እንደዚሁም ስንዴ 10.8፣ 11.9 እና 12.3 ሲሆን፣ ገብስ ደግሞ 11.3፣ 11.2 እና 10.8 ነበር:: በተጨማሪም በቆሎ 14.7፣ 15.5 እና 16.1 ሲሆን ማሽላ ደግሞ 11.7፣ 12.2 እና 11.9 ነበር:: ሁሉም ሰብሎች በአጠቃላይ ሲታዩ ደግሞ 10.6፣ 11.4 እና 10.9 ነበር::

በ1992 ዓ.ም በ3.9 ሚሊዮን ሄክታር ላይ በግብዓትነት 4.3 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ (ከዚህ ውስጥ ሩቡ ያህል ዩሪያና ዳፕ የሚባሉት ማዳበሪያዎች ድርሻ ነው) በጥቅም ላይ ውሏል:: ያም ሆኖ ማዳበሪያ፣ ምርጥ ዘርና ሌሎች ምርት የሚያሳድጉ ግብዓቶች መጠቀሙ ያስገኙት ጥቅም በአማካይ ሲታይ በመሬት ምርታማነት ላይ በአፈር መሸርሸርና በሌሎች ምክኒያቶች ሊደርስ የቻለውን ጉዳት ማካካስ እንኳን አልቻለም:: ስለሆነም ቀደም ብሎ ያለማዳበሪያ ከአንድ ሄክታር ይገኝ የነበረው ምርት አሁን ማዳበሪያ ጭምር ተጠቅሞም ሊገኝ አልቻለም:: መጠነኛ መሻሻል የታየው በበቆሎ ምርት ላይ ብቻ ነው:: በሌሎች ሰብሎች ላይ ግን የመቀነስ አዝማሚያ ታይቷል::

አገራችን ለግብርና ልማት መስፋፋት አመቺ ብትሆንም በደጋና ወይናደጋ አካባቢዎች ያለው ሕዝብና የእንስሳት ብዛት ካለው የመሬት ሀብት ጋር የተመጣጠነና ሚዛናዊ ባለመሆኑ እንዲሁም በዘመናዊ ቴክኖሎጂ ባለመደገፉ በተፈጥሮ ሀብት ላይ ከፍተኛ ጫናን አስከትሏል:፤ ይህም የመሬት መሸንሸንን፣ ለግብርና አገልግሎት መዋል የማይገባውን መሬት ለግብርና ተግባር መዋልንና ደን ያለአግባብ በመጨፍጨፉ የዱር እንስሳት መሰደድንና መጥፋትን፣ የአፈር መከላትን፣ የአፈር ለምነት መቀነስንና የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እጥረትን አስከትሏል:: ይህ አግባብ የሌለው የመሬት አጠቃቀም አጠቃላይ ውጤትም የምርት መጠንና ምርታማነት ከጊዜ ወደ ጊዜ እንዲቀንስ አድርጓል::

በተጨማሪም በተፈጥሮ ሀብት ላይ በተፈፀመውና እየተፈፀመ ባለው የአጠቃቀምና የአያያዝ ጉድለት የተነሳና በልዩ ልዩ የተፈጥሮ ክስተቶች ሳቢያ በአገራችን ከፍተኛ የኢኮሎጂ መዛባትና የመሬት መራቆት ደርሷል፡፡ በተለይም ከሕዝብ ብዛት መጨመር ጋር ተያይዞ የመጣው የብዝሀ ሕይዎት ሀብት መመናመን፣ ለእርሻ መዋል የማይገባው መሬት መታረስ፣ ለከፍተኛ አፈር መከላት እንዲሁም ለበረሀዎች መፈጠር ብሎም ለምርታማነት ማሽቆልቆልና ለበረሃማነት መስፋፋት ዋነኛ ምክኒያቶች በመሆናቸው በአፋጣኝ መገታት ያለባቸው ቁልፍ ችግሮች ሆነው ይገኛሉ፡፡ በሌላም በኩል ተገቢ ባልሆነ የመሬት አጠቃቀም በአደንና በመሳሰሉት ምክንያቶች የዱር እንስሳት መኖሪያዎቻቸው እየጠበቡና እጅግ ለከፋ አደጋ እየተጋለጡ መጥተዋል፡፡

የኢትዮጵያ ግብርና እንደ ዝናቡ ሁኔታ ከጊዜ ወደ ጊዜ የመለዋወጥ ባሕሪይ አለው፡፡ በአጠቃላይ የኢኮኖሚው ክንውን ከግብርናው ክንውን ጋር ጥብቅ ዝምድና አለው፡፡ ግብርና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ መሠረት ነው፡፡ በመሆኑም ከጠቅላላው የአገሪቱ ሕዝብ 85 በመቶ የሚሆነው የሚተዳደርበት፣ ከአጠቃላይ ዓመታዊ የአገር ምርት ውስጥ 50 በመቶ አስተዋጽኦ የሚያደርግ፣ 90 በመቶ ለውጭ ምንዛሪ ግኝትና 70 በመቶ ለአገር ውስጥ ኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ የሚያበረክት ከፍተኛ ድርሻ ያለው ወሳኝ ክፍለ ኢኮኖሚ ነው፡፡

የሰብል ልማት ዘርፍ የምግብ ሰብሎች፣ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃዎችንና የውጭ ምንዛሪን በማፍራት ጉልህ ድርሻ ያለውና ከአጠቃላይ ዓመታዊ የግብርና ምርት ውስጥ ከ60 በመቶ በላይ በማበርከት ሠፊ አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ የሚገኝ ነው፡፡ የሰብል ልማቱ በአብዛኛው በተፈጥሮ ተፅእኖ ሥር የሚካሄድ እንቅስቃሴ ነው፡፡ እስከ 95 ከመቶ የሚሆነው የእርሻ እንቅስቃሴ በመኸር ወራት የሚካሄድ ሆኖ በመስኖ ሥራ በሠፊው የሚታገዝ አይደለም፡፡ በወንዞች ተፋሰስ ላይ በተደረገው ጥናት መሠረት በመስኖ ሥራ ዘዴ ሊለማ ይችላል ተብሎ ከሚገመተው 3.5 ሚሊዮን ሄክታር መሬት ውስጥ እስካሁን በጥቅም ላይ የዋለው ከሶስት በመቶ አይበልጥም፡፡ በሌላ በኩልም በአገሪቱ በዓመት ለሰብል ልማት ከሚውለው ጠቅላላ መሬት ውስጥ በአብዛኛው የሚታረሰው በአማካይ ከአንድ ሄክታር በታችና የተበጣጠሰ ይዞታ ባላቸው አርሶ አደሮች ነው፡፡

ዋና ዋናዎቹ የምግብ ሰብሎች ጤፍ፣ ስንዴ፣ ገብስ፣ በቆሎ፣ ማሽላ/ዘንጋዳ፣ ሥራሥር/ግንድ ዓይነት ናቸው፡፡ ዋና ዋና የገበያ ሰብሎችም ቡና፣ ጥጥ፣ ስኳር፣ ሻይ፣ ትንባሆ፣ ጫትና የተለያዩ የጓሮ አትክልት ናቸው፡፡

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የእንስሳት ሀብት ክምችት፣ ለእርባታ አመቺ የሆነ ሠፊ መሬትና ተስማሚ የአየር ንብረት እንዳላት ይታመናል፡፡ የእንስሳት እርባታ ከግብርናው ጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ሲሶውን ያህል፣ ከጠቅላላ ብሔራዊ ምርት ደግሞ 15 በመቶ ያህሉን እንደሚያበረክት ይገመታል፡፡ ይህ አሃዝ ከእንስሳት እርባታ ውጤቶች የፍግን አገልግሎት (ማዳበሪያና ነዳጅ የመሳሰሉትን) እና በመጓጓዣነት የሚሰጡትን አገልግሎት ከግምት ያስገባ አይደለም፡፡

የከብት ርቢ በምርት ሥርዓት ውስጥ ልዩ ልዩ አገልግሎቶች አሉዋቸው፡፡ በወተት፣ በሥጋና በልዩ ልዩ የእንስሳት ተዋፅኦ መልክ የሚቀርቡ ምግቦች ከእንስሳት እርባታ ዋነኛ የምግብ ምርቶች ናቸው፡፡ በአነስተኛ ድብልቅ የእርሻ ይዞታዎች ከእንስሳት እርባታ የሚገኘው ምርት ሩብ ያህሉ ለምግብ ፍጆታ ይውላል፡፡ በከብት ርባታ በሚተዳደሩ ማሕበረሰቦች ዘንድ ለምግብ ፍጆታ የሚውለው የእንስሳት ውጤት መጠን ወደ 60 ከመቶ ይደርሳል፡፡ ለምግብ አገልግሎት ከማይውሉት የእንስሳት እርባታ ውጤቶች መካከል ደግሞ ለእርሻ፣ ለመጓጓዣ እንዲሁም ለፍግ ማዳበሪያ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ ቆዳና ሌጦ እንዲሁም ሱፍና ጠጉር የእንስሳት እርባታው ዘርፍ ተጓዳኝ ውጤቶች ተደርገው የሚቆጠሩ ጠቃሚ ውጤቶች ናቸው፡፡

የአገሪቱ የእንስሳት ሀብት ብዛት ከፍተኛ ቢሆንም ከእነዚህ እንስሳት የሚገኘው የምርት መጠን እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ ለዚህም ከሚጠቀሱት ውስጥ የእንስሳት መኖ በጥራትና በመጠን ተሟልቶ አለመገኘት፣ የእንስሳት በሽታ መስፋፋትና የጤና ቁጥጥር አገልግሎት ማነስ፣ የተሻሻሉ የምርት ግብአቶች አቅርቦት ውስን መሆን፣ የብድር፣ የገበያና ሌሎች መሠረተ ልማት አውታሮች አለመስፋፋት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## 1.2 በግብርናው ዘርፍ የሚታዩ ችግሮች

የኢትዮጵያ ግብርና በልማዳዊ የአስተራረስ ዘዴዎች የሚከናወን ነው። ለአፈር ጥበቃና እንክብካቤ ብዙም ትኩረት ሳይሰጥ ይህ ዓይነቱ የአስተራረስ ዘዴ ለረጅም ዘመናት በመቆየቱም የመሬቱ ለምነት ስለተመናመነ በአሁኑ ወቅት የግብርናው ውጤት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህ ጥንቃቄ የጎደለው የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም፣ በተለይም ለማገዶና ለግንባታ እንዲሁም የእርሻ መሬት ለማግኘት ዛፎችን መቁረጥና መጨፍጨፍ እያደገ ከመጣው በግብርና ከሚተዳደረው ሕዝብ ቁጥር ጋር ተደምሮ የከፋ ችግር አስከትሏል። ስለዚህም በምርት እጥረት ለተደጋጋሚ እርሃብ የሚጋለጡት የአገሪቱ ክፍሎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመሩ መጥተዋል። በዚህም ምክኒያት በየጊዜው ብዙው የሀገሪቱ ሕዝብ በረሃብ ስለሚጠቃ ከጊዜ ወደ ጊዜ ከዓለም አቀፍ በጎ አድራጊ ድርጅቶች ለሚገኝ የምግብ ሰብል ጥገኛ አድርጎታል።

የኢትዮጵያ ግብርና ዝቅተኛ ክንዋኔ ያስከተለው ዋና ጦስ የምግብ ዋስትና እጅግ አስጊ ደረጃ ላይ መድረስ ነው። ከጠቅላላው የሀገሪቱ ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሚሆነው የሚበላው የሌለው ወይም ከአስከፊ ድህነት ወለል በታች የሚኖር እንደሆነ ይገመታል። የአገር ውስጥ የምግብ አቅርቦት አገሪቱ የሚያስፈልጋትን መሠረታዊ የምግብ መጠን ለማሟላት አልቻለም።

ኢትዮጵያ ውስጥ በከፍተኛ የመሬት መፈራረስ ሳቢያ የእርሻና የግጦሽ መሬቶች እተጎዱ ነው። በደጋው አካባቢ በቂ መሬት አለመኖር ከህዝብ ቁጥር ግፊት ጋር በመደመር የኮረብታ ተዳፋቶችን ሳይቀር ለማረስ አስገዳጅ ሁኔታዎችን ፈጥሯል። ገደላማና ተዳፋት መሬቶች በአፈር መሸርሸርና መታጠብ ምክኒያት በከፍተኛ ደረጃ ፈራርሰዋል። ከመሬቱ አቀማመጥ በተጨማሪ የመሬት መፈራረስን ችግር ያባባሰው የአፈር ጥበቃ ዘዴዎችን ከግምት ያላስገባው የአስተራረስ ባሕል ነው።

የምግብ ሰብል እጥረትን ስር የሰደደና አላፊ ብሎ ለሁለት መክፈል ይቻላል። በገጠሩ አካባቢ ስር ሰደድ የምግብ ችግር የሚገኘው ምርት ለቀለብ የማይበቃ የሚሆንባቸውን ከግማሽ ሄክታር ያነሰ የእርሻ ይዞታ ያላቸውን በገጠር ከሚኖረው ቤተሰብ አንድ ሦስተኛ ያህል የሚሆነውን ሕዝብ ይመለከታል። የእርሻ በሬና የዘር መግዣ ገንዘብ የሚቸግራቸው ቤተሰቦችም ምድባቸው ከእነዚህ ወገኖች ነው። በተጨማሪም መሬት የሌላቸው፣ በዕድሜ የገፉ፣ የአካል ጉዳተኞች፣ አባወራ የሌላቸው፣ ከብት አርቢዎችና አራሽ ያልሆኑ እንዲሁም አዲስ ተጋቢ ቤተሰቦች በስር ሰደድ የምግብ ችግር ይሰቃያሉ። አላፊ የምግብ ችግር በድርቅ፣ በመፈናቀልና በስደት ምክኒያት የሚመጣ ነው። በተደጋጋሚ በርሃብ የሚጠቁ አካባቢዎች የምግብ ችግር ከፊል አላፊ እና ከፊል ስር ሰደድ ነው። ከብት አርቢዎች በአጠቃላይ በአላፊ የምግብ ችግር ይሰቃያሉ።

እንደማንኛውም የምርት ዘርፍ ሁሉ ብቃት ያለው የግብርና ምርት መሬት፣ ጉልበት፣ ካፒታልና እውቀት የመሳሰሉት ለምርት እድገት አስፈላጊ ሁኔታዎችን መገኘትንና በተገቢው ሁኔታ መጠቀም መቻልን ይጠይቃል። በአገሪቱ ያለውን የእርሻ መሬት የነፍስ ወከፍ ድርሻ በእርሻ ሥራ ከተሰማራው ሕዝብ ቁጥር አንፃር ስንመለከት በኢትዮጵያ ላለው የግብርና ክንዋኔ ዝቅ ማለት የሠራተኛ ኃይል ቁጥር ማነስ ዋና ምክኒያት ሊሆን አይችልም። የመሬት ባለቤትነት ችግርና የአጠቃቀም ብቃት ማነስ ግን በእርግጥም ዋና ምክኒያቶች ናቸው። በኢትዮጵያ ግብርና ውስጥ በተለይ የካፒታልና የእውቀት አቅርቦት መጠን ዝቅተኛ ነው። በኢትዮጵያ በግብርናው ዘርፍ የካፒታልና የእውቀት ግብዓት ዝቅ ማለት ዋና ችግሮች ናቸው። የመሬትን ምርታማነትና የሠራተኛውን ምርታማነት ማሳደግ እስካልተቻለ ድረስ የግብርናውን ዘርፍ ውጤታማ ማድረግ አይቻልም።

በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል እያደገ የመጣው ግፊት-ሕዝብ እና ጠቅላላ የእርሻ መሬትን ለማስፋፋት ያለው ዕድል ውስን መሆን የእርሻ መሬት የነፍስ-ወከፍ ድርሻ መጠንን እንዲቀንስ አድርጎታል። ትንንሽ የእርሻ ይዞታ ያላቸው ቤተሰቦች የምግብ ፍጆታ ፍላጎት የሚያሟላ ምርት አያመርቱም። ስለዚህም እነዚህ ቤተሰቦች ከእርሻም ሆነ ከእርሻ ሥራ ውጭ የሚያገኙትን ማንኛ ውም ገቢ ለምግብ ያውላሉ። የሚተርፋቸውና ለእርሻ ግብዓቶች መግዣ የሚውል ምንም ነገር የላቸውም። ኑሯቸው በሕይወት ለመቆየት የሚደረግ የእለት ከእለት ትግል ነው።

*ለኢትዮጵያ የግብርና እንቅስቃሴ ማነስ ዋና ዋና ምክኒያቶች የእርሻ መሬት ይዞታ መቀነስ፣ የመሬት መንሸራተት፣ የዝናብ እጥረትና ተለዋዋጭነት፣ የመሬት ባለቤትነት መብት አስተማማኝ አለመሆን፣ የተሟላ የእርሻ ምርት ገበያ አለመኖርና የመሠረተ ልማት አውታሮች በዝቅተኛ ደረጃ መገኘት ናቸው፡፡ ከተዘረዘሩት ምክኒያቶች አንዳንዶቹ ከፖሊሲ ቀራጮች ችሎታ ውጭ ናቸው፡፡ ይህም ሆኖ የግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ዝቅ ማለት የነበሩትና ያለው መንግሥታት ፖሊሲዎች ጋር በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተያያዘ ነው፡፡*

## 1.3 ከመሬት ይዞታ ጋር የተያያዙ ችግሮች

*አሁን ያለው የመሬት ፖሊሲ ሕዝብ ሳይመክርበትና ውይይት ሳይደረግበት በሕገ-መንግሥት እንዲካተት ተደርጓል፡፡ ከርዕዮተ-ዓለም ግፊት የመነጨው የመሬት ፖሊሲ በግብርናው ዘርፍ ብዙ ጦሶች አስከትሏል፡፡ የመሬት ፖሊሲው ዋነኛው ጦስ የመሬት ባለቤትነት አስተማማኝ አለመሆን ነው፡፡ የመሬት ይዞታ ባለቤትነት ዋስትና በሌለበት ሁኔታ ገበሬዎች መሬት ለማሻሻል ገንዘብ ወጭ ለማድረግ አይደፍሩም፣ በገንዘባቸው ምርት የሚያሳድጉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም አይበረታቱም፡፡ አሁን ላለው ፖሊሲ መሬት በመንግሥት ይዞታ ስር እንዲቆይ ለመወሰን ምክኒያት ሆነው የሚቀርቡት ነጥቦች ገበሬዎች መሬታቸውን ለመሸጥ ተገደው መሬት በጥቂት ሀብታሞች ይዞታ ሥር ይገባል፣ በውጤቱም ድሃ ገበሬዎች ከይዞታቸው ይፈናቀላሉ የሚል ነው፡፡ ባለፉት ዓመታት የታዩት ገጠመኞች እንደሚያሳዩት ይህ ፖሊሲ ከእያንዳንዱ ቤተሰብ ይዞታ ላይ በመሸረፍ ለሌላው ማካፈል የእያንዳንዱን ቤተሰብ ይዞታ እንዲቀንስና ሁሉም ሰው ተያይዞ እንዲደኸይ ከማድረግ የተሻለ ፋይዳ አላመጣም፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ይዞታን በሕጋዊ መንገድ ማስተላለፍ መከልከሉ መሬት በማይሠሩ ሰዎችም ይዞታነት እንዲቆይ አድርጓል፡፡ ይህም ሁኔታ በጣም ውጤታማ የሆኑ ገበሬዎች በሌሎች ይዞታ የሚገኘውን መሬት ማልማት እንዳይችሉ አድርጓል፡፡*

*የመሬት ይዞታው ያስከተለው ሌላው ጦስ በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ የሚሄድ ግፊተ-ሕዝብ እንዲኖር ማድረጉ ነው፡፡ ሰዎች ከቀበሌያቸው ወጥተው ረዘም ላለ ጊዜ ቢቆዩ ይዞታቸው ስለሚወሰድባቸው አሁን ያለው የመሬት ሥርዓት ሰዎች ከቀያቸው እንዳይፈልሱ አስሮ ይዟቸዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ከፍተኛ ግፊተ-ሕዝብ እንዲኖር አድርጓል፡፡*

*የምርት መጨመር ወይም ሊለማ የሚችል ተጨማሪ የእርሻ መሬት ለማስፋፋት ተስፋ በሌለበት ሁኔታ፣ ሰዎች ወደ ከተማ እንዳይሰደዱ በታገዱበትና የሀብት ምንጮች በጎሣ ተከፋፍለው ብዙ ሰው ወደማይኖርባቸው አካባቢዎች ሄዶ መሬት ማልማት በማይቻልበት ሁኔታ አሁን ያለው የመሬት ፖሊሲ ወደፊት ታላቅ ቀውስ ማስከተሉ አይቀሬ ነው፡፡ ከፍ ብለው ከተገለፁት ጉዳዮች ጋር ዝምድና ያለው ሌላ ጉዳይ የግጦሽ መሬት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣትና ይህም ሁኔታ በአገሪቱ የቤት እንስሳት ሀብት ላይ የሚያስከትለው ችግር ነው፡፡ በሰሜኑ ክፍል እየጨመረ የመጣውን የሕዝብ ቁጥርና የእርሻ መሬት ፍላጎት ለማሟላት የግጦሽ መሬት ለእርሻ እንዲያውሉት ለገበሬዎች ተከፋፍሏል፡፡ ይህም ሁኔታ የእንስሳት መኖ በእጅጉ እንዲቀንስ ስላደረገ ብዙ ቤተሰቦች የከብቶቻቸውን ብዛት ለመቀነስ ተገደዋል፡፡ ለዚህ ግፊተ-ህዝብ መሰረታዊ መፍትሄ ሊሆን የሚችለው በቂ ጥናትንና ፈቃደኛነትን መሰረት ያደረገ የሰፈራ ፕሮግራም ቢሆንም ገዢው ፓርቲ ያለፈውን ሥርዓት ለማጥላላት ብቻ ሲል የሰፈራ ፕሮግራምን በጥቅሉ የሚያጥላላ ሰፊ ፕሮፓጋንዳ በማራመዱና ቋንቋንና ጎሣን መሰረት አድርጎ ተግባራዊ የሆነው የፌዴራል አደረጃጀት ትልቅ እንቅፋት ሆኗል፡፡ ገዥው ፓርቲ ደረጃ በደረጃ የሰፈራ ፕሮግራም ተግባራዊ እንዲሆን ሙከራ እያደረገ ቢሆንም በቅድሚያ በሕዝቡ መካከል አስተማማኝ ብሔራዊ ስሜት ተፈጥሮ ህዝቡ በክልሉ ብቻ ሳይሆን በመላው አገሪቱ ተዘዋውሮ የመስፈር እድል ካላገኘ በስተቀር መሰረታዊ ለውጥ ይመጣል ተብሎ አይታሰብም፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ የፕሮፓጋንዳ ሰለባ ሆኖ በአርሶ አደሩ እንዲጠላ የተደረገው የመንደር ምስረታና የህብረት ስራ ማህበራት ጉዳይ ወደትክክለኛው አቅጣጫ ተመልሶ ተግባራዊ የሚሆንበት ሁኔታ ካልተመቻቸ በስተቀር አርሶ አደሩን አሁን በሚገኝበት የተበታተነ አሰፋፈር የመሰረተ ልማት አገልግሎት ተጠቃሚ ማድረግ የማይቻል ነው፡፡*

*የመሬት ፖሊሲው በአስተራረስ ተግባራትና በአካባቢው ጥበቃ ላይም አሉታዊ ተጽእኖዎች አሉት፡፡ የመሬት ባለቤትነትና ይዞታ ዋስትና ማጣትና የይዞታ መጠን መቀነስ ብዙ ገበሬዎች*

ይገለገሉባቸው የነበሩትን እንደ ሰብል ማከር (እህል መለዋወጥ)፣ እዳሪ ማውጣት፣ መሬትን አሳርፎ ማክረም (ጦም ማሳደር)፣ የተፈጥሮ ማዳበሪያዎችን (አዛባ፣ ፍግ) መጨመር፣ ያሉትንና የመሳሰሉ አስተማማኝ ባሕላዊ የመሬት አያያዝና አስተዳደር ልማዶች መሬታችን ከለማ ይወሰድብናል ብለው በመስጋት እርግፍ አድርገው እንዲተው ምክኒያት ሆኗል:: በምትኩም የወደፊቱን ማሰብ ትተው የፊት ለፊታቸውንና የዛሬን ጥቅም ብቻ መመልከት ጀምረዋል:: እንዲህ ዓይነቱ ልማድ በቆየ መጠን፣ መሬቱ ያለእረፍት ስለሚታረስ ጠቃሚ ንጥረ ነገሮች እያለቁ ይሄዱና በመጨረሻም የመሬት ማርጀት ይከተላል:: ሌሎች የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ልማዶችም ፈፅሞ እየቀሩ ነው:: ገበሬዎች ውሎ አድሮ በአካባቢ ላይ የሚመጣውን አሉታዊ ውጤት ቢረዱም በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሽያጭ ከሚደርሱ ዛፎች በስተቀር ሌሎች አማራጭ ዛፎችን መትከል አቁመዋል:: ገበሬዎቹ ለማደግ ረጅም ጊዜ ለሚያስፈልጋቸው ዛፎች ትኩረት የማይሰጡት የባለቤትነት መብት ስለሌላቸውና መሬቱ የእነርሱ ይዞታ ሆኖ ስለመቆየቱ ዋስትና ስለሌላቸው ነው::

በመጨረሻም የመሬት ይዞታው ሥርዓት በተለይ ወጣቱን የሚጎዳ ማኅበራዊ ጣጣ አስከትሏል:: እጅግ ብዙ ወጣቶች መሬት ስለሌላቸው ዕድሜያቸው ከገፋ በኋላ እንኳን የወላጆቻቸው ጥገኛ ለመሆን ተገደዋል:: በገጠሩ ማኅበረሰብ መካከል ጉልህ የሆነ የሀብት መበላለጥ ባለመኖሩ ምክኒያትም በገበሬው ውስጥ ጥሪት አጠራቅሞ ባለኢንዱስትሪ የመሆን ግፊት ጠቅላላውን ሞቷል:: መንግሥት መሬት የመስጠትና የመንሳት፣ የመጨመር ወይም የመቀነስ ብቸኛ መብት ያለው የመሬት ከበርቴ በመሆኑም በገጠሩ የኢትዮጵያ ክፍል ተለማማጭ ገበሬ እንጂ፣ ነፃ፣ በራሱ የሚተማመንና ኃላፊነትን ለመውሰድ ፈቃደኝነት ያለው ገበሬ እየታጣ ነው::

## 1.4 የገጠር መሬት ባለቤትነት

ለግብርና ምርት እድገት አስተማማኝና ፍትሓዊ የመሬት ባለቤትነት መብት አስፈላጊ ነው:: አራሽ ገበሬዎች አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እስከመሸጥ መለወጥ የሚደርስ የባለቤትነት መብት ያላቸው መሆኑን ሲያረጋግጡ መሬቱን ለማሻሻል የሚያውሉት የመካከለኛና የረጅም ጊዜ ኢንቨስትመንት ይጨምራል:: ይህም ሁኔታ ለአፈር አጠባበቅና እንክብካቤ እንዲሁም ለዛፎችና ለሌሎች ጥሪቶች ከፍተኛ ግምት የሚሰጥ የግብርና ተግባር እንዲኖር ስለሚያደርግ የመሬት መፈራረስ እንዲገታ ይረዳል::

ከሰው ጉልበት በተጨማሪ ዋነኛው የምርት ምንጭ መሬት ነው:: የሕዝቡን የማምረት አቅም በማጎልበት ላይ የሚመሠረት ስትራቴጂ የመሬትን ምርታማነት በማሳደግም ላይ የግድ መረባረብ ይኖርበታል:: ስለመሬት ምርታማነት ከማንሳታችን በፊት ግን አሰቀድሞ መመለስ የሚገባው የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ አለ::

መሬት ከኢትዮጵያውያን ሕይወት ጋር በእጅጉ የተቆራኘ እንደመሆኑ፣ የመሬት ጥያቄ በአስተማማኝ መንገድ መመለስ ይኖርበታል:: በመሆኑም መሬት እንደ ፖለቲካ መሣሪያ ከሚያገለግልበት አብዮታዊ ዴሞክራሲ አሠራር ወጥቶ በአግባቡ ለኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ወደሚውልበት ወደ ግል ይዞታ መሸጋገር ይኖርበታል::

መሬትን በግል ባለቤትነት መያዝ የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ መሠረታዊ አስተሳሰብ ነው፣ በምዕራባዊያን አገሮችም በብዛት ይሠራበታል:: መሬት በግል ባለቤትነት በመያዝ ሥርዓት ውስጥ መሬት እንደማንኛውም ንብረት የሚሸጥ ወይም የሚገዛ ቢሆንም መጠንንም ሆነ አግባብነት ያለው የመሬት አጠቃቀምን በተመለከተ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ያገናዘበና በሕግና በሥርዓት የሚመራ ማድረግ ይቻላል:: ብዙውን ጊዜ እንደዚህ ያለውን የመሬት ይዞታ በጥቅም ላይ ለማዋል የቤተሰብ ጉልበት ብቻ በቂ ነው::

መሬት በግል ባለቤትነት ሲያዝ የሚከተለው ሁኔታ፣ በአካባቢው ሕብረተሰብ በጋራ (በወል) ባለቤትነት ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ስር ሲያዝ ወይም በሰፋፊ ኢዱስትሪያል እርሻ ሲያዝ ከሚታየው ሁኔታ ጋር ሲነፃፀር የጎላ ጠቀሜታ እንዳለው ተስተውሏል:: መሬት በግል ባለቤትነት ቢያዝ ከሚገኙት ጠቀሜታዎች ውስጥ፤ ከፍተኛ የመሬት ምርታማነት፣ ከፍተኛ የሰው ኃይል ምርታማነት፣ ከፍተኛ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ መሆን፣ የሰፋ የካፒታል አጠቃቀም መፈጠር፣ የሰው ኃይል በስፋት መጠቀም፣ ለገበያ የሚሆን ምርት ላይ ትኩረት መስጠት፣ የሚጠቀሱ ናቸው::

የመሬት በግል ባለቤትነት መያዝ በፖለቲካዊ፣ በኢኮኖሚ፣ በማኅበራዊና በሕጋዊ ሥርዓት በኩል በሚያስገኘው ጠቀሜታ ሲመዘንም ከሌሎች አማራጮች ሁሉ ብልጫ አለው፡፡ በተጨማሪም የአስተራረስ ዘዴዎችን ለማሻሻልና የተፈጥሮ ሃብትንም በአግባቡ ተንከባክቦ ለአሁኑም ሆነ ለመጪዎችም ትውልዶች ጠብቆ ማቆየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም በአገራችን እየተባባሰ የመጣውን የአፈር መሸርሸርና በርሃማነትን መግታት ይቻላል፡፡ ከዚህም አልፎ መሬት በግል ባለቤትነት ቢያዝ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ማደግን፣ የተፈጥሮ ሃብት መመናመንና በቂ ምግብ ማምረት አለመቻል ከመሳሰሉት ኢትዮጵያን ፊት ለፊት ከገጠሟት ዋነኛ ፈተናዎች መውጣት ይቻላል፡፡

አርሶ አደሩ የተሻለ ኑሮ ሊኖር ወደሚችልበት አካባቢ እንዳይንቀሳቀስ አሁን ያለችውን ብዙ የደከመባትና ያችኑ ያለችውን ጥሪት ያፈሰሰባትን መሬት ትቶ የተሻለ ኑሮ ሊኖር ወደሚችልበት ሰፊና ለም መሬት ወደሚገኝበት የገጠር አካባቢም ሆነ ወደ ከተሞች እንዳይዘዋወር እንቅፋት ሆኖበታል፡፡ ገበሬው አካባቢውን ቀይሮ ለመኖር የሚያስችለውንና መሬቱን በመሸጥ ማግኘት የሚችለውን መቋቋሚያ ገንዘብ ማጣት ብቻ ሳይሆን ኢሕአዴግ የሚከተለው የጎሳ ወይም የብሔረሰብ ልዩነትን የማራገብ ተግባር ዜጎች በሚመርጡትና በሚመቻቸው የአገራችን አካባቢዎች ለመኖር እንዳይችሉ አስፈሪ ሁኔታ ፈጥሮባቸዋል፡፡

በአርሶ አደሩ እጅ ያለው መሬት እስከ መሸጥ ድረስ መብት በሚያጎናጽፍ መልኩ በግል ባለቤትነት መያዝ አለበት ሲባል ኢሕአዴግ ደግሞ ደጋግሞ የሚያቀርበው መከራከሪያ ገበሬው ሲቸገር መሬቱን ይሸጥና ይሰደዳል የሚል ነው፡፡ አርሶ አደሩ በችግር ምክኒያት መሰደድ ካለበት መሰደዱ አይቀርም፡፡ አሁንም እየተሰደደ ነው፡፡ ልዩነቱ ያለው መሬቱን ሽጦ ገንዘቡን ቋጥሮ ሌላ ቦታ የተሻለ መሬት ወይም ሌላ አማራጭ መተዳደሪያ ለማመቻቸት እንዳይችል መደረጉ ነው፡፡ ሌላው አርሶ አደሩ የሚበጀውን አማራጭ ለይቶ የማያውቅና በቀላሉ ሊታለልና መሬቱን ሊሸጠው ይችላል የሚለው አስነዋሪ አስተሳሰብ ነው፡፡ ሀቁ ግን አርሶ አደሩ በችጋር በሚጠበስበት ጊዜ እንኳን መሬቱን የመሸጥ ሁኔታ እንዳላሳየ ነው የታየው፡፡ አርሶ አደሩ አንዳንዶች ከሚገምቱት በላይ ለራሱ የሚበጀውን የሚያውቅ፣ ብልህና ታታሪ መሆኑን በተግባር ያሳየ ነው፡፡ መታፈኑ ይገታለት እንጂ ካለበት ችግር ተስፈንጥሮ መውጣት የሚያስችል እምቅ እውቀት እንዳለው መገንዘብ ይኖርብናል፡፡ የኢሕአዴግ ሰበብ ሁሉ የሚያጠነጥነው ገበሬውን የመንግሥት ጭሰኛ በማድረግ በቁጥጥር ስር በማዋል የፖለቲካ መጠቀሚያ ማድረጉ ላይ ብቻ ነው ማለት ይቻላል፡፡

በመሬት ፖሊሲ መዘዝ በገጠሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የሚመጡት ጣጣዎች እጅጉን አሳሳቢ ናቸው፡፡ ማንኛውም የሕዝብ ኃላፊነት ያለበት መንግሥትም እነዚህን ለመሰሉ ችግሮች የተሻሉና ተስማሚ አማራጮች ማግኜት ይቻል ዘንድ ጉዳዩን ለሕዝብ ውይይት ማቅረብ አለበት፡፡ በኢዴፓ እምነት የኢትዮጵያ ግብርና ያሉበት ችግሮች ከመሬት ባለቤትነትና ዋስትና ይዞታ ፖሊሲ ጋር የተያያዙ ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ ግብርና የወደፊት ብሩህ ተስፋ እንዲኖረው ከተፈለገ አሁን ያለውን የመሬት ፖሊሲ መለወጥ አስፈላጊ ነው፡፡ አርሶ አደሮችንና ሌሎችንም የሚመለከታቸውን አካሎች የሚያሳትፍ የመሬት ፖሊሲ ክለሳ አጅግ አንገብጋቢ የሆነ የወቅቱ ጥያቄ ነው፡፡

## 1.5 የአርብቶ አደሮች ልማት

በኢትዮጵያ ውስጥ አርብቶ አደሮች የሚኖሩበት አካባቢ በአብዛኛው ቆላማው የሀገሪቱ ክፍል ነው፡፡ ይኸም በፋኦ (FAO) ጥናት መሠረት የኢትዮጵያ እርሻ ሥነምህዳር ሁኔታ ሲታይ ደረቃማ (Arid) እና ከፊል ደረቃማ (Semi Arid) የሆነው አካባቢ የሚገኘው እነዚህ አርብቶ አደሮች ባሉበት ቀጠና ነው፡፡ ይህ ቀጠና ከሀገሪቱ የቆዳ ስፋት ውስጥ 42% የሚሆነውን መጠን የሚሸፍን ነው፡፡ ከፍተኛ የዝናብ እጥረት ያለበት ቀጠና ቢሆንም ለግጦሽ እንቅስቃሴ ደግሞ ተስማሚ ነው፡፡ ደረቃማና ከፊል ደረቃማ የሆነውን ጨምሮ ዝቅተኛ መሬት (low land) የሚባለው አካባቢ ከሀገሪቱ ጠቅላላ ቆዳ ስፋት ውስጥ ያለው ድርሻ 60% ገደማ ነው፡፡ ከፍተኛ መሬት (high land) የሚባለው ድርሻ ደግሞ 40% አካባቢ ነው፡፡ ከሀገሪቱ ሕዝብ ውስጥ 12% የሚሆነው የሰፈረው ዝቅተኛ መሬት በሚባለው አካባቢ ነው፡፡ ሀገሪቱ ካላት የእንስሳት ሀብት

*ውስጥ 26% የሚሆነው በዚህ አካባቢ የሚገኝ ነው፡፡ የሕዝቡ ቁጥር አነስተኛ ይሁን እንጂ የሰፈረበት አካባቢ ከፍተኛ የመስኖ ፖቴንሽያል የሚገኝበት ነው፡፡ ሀገሪቱ ካላት የመስኖ ፖቴንሽያል 95% የሚገኘው እዚህ አካባቢ ነው፡፡ ከመስኖ ፖቴንሽያል ሌላ የእንስሳት እርባታ በሰፊው የሚካሄድበት አካባቢ ነው፡፡*

*የአየሩ ሙቀት ከባድ ከመሆኑ በተጨማሪ የመሰረተ ልማት አገልግሎት ያልተስፋፋበት በመሆኑ ለኑሮ አስቸጋሪ የሆነ አካባቢ ነው፡፡ የጤና፣ የትምህርት፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ፣ የመንገድና የመሳሰሉት የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች ባለመሟላታቸው በዚህ ቀጠና የሚኖሩት ወገኖች ሕይወት ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ ነው፡፡ ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ2001 የአፋር ክልል የጤና አገልግሎት ሽፋን 29%፣ የሶማሌ 24% ብቻ ነው፡፡ የንፁህ መጠጥ ውሃ ሽፋን በ2002 በአፋር 10%፣ በሶማሌ 14% ነው፡፡ የትምህርት ሽፋን በ2002 በአፋር 10%፣ በሶማሌ 9% ብቻ ነው፡፡ በአለፉት ተከታታይ አመታት በአፋር፣ በቦረናና በሶማሌ በደረሰው ከፍተኛ ድርቅ አርብቶ አደሮች ካላቸው እንስሳት መካከል ከ90% በላይ የሚሆኑት አልቀውባቸዋል፡፡ ከድርቁ ጎን ለጎን የዋቢ ሸበሌ ወንዝ የሶማሌን፣ የባሮና አኮቦ ወንዝ ደግሞ የኑየርን፣ የኦሞ ወንዝ የደቡብ ኦሞን፣ የአዋሽ ወንዝ የአፋርና ከረዩን አርብቶ አደሮች ለጎርፍ አደጋ ስለሚያጋልጧቸው በሰው ሕይወት፣ በንብረትና በእንስሳት ሀብታቸው ላይ በተደጋጋሚ ጊዜ ከባድ ጉዳት ይደርስባቸዋል፡፡*

*የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች በተደጋጋሚ ከሚከሰተው ጎርፍ ጋር ተያይዞ በሚነሳ የወባ ወረርሽኝ በሚዘገንን ሁኔታ በየአመቱ ያልቃሉ፡፡ ከአየሩ ፀባይ መጥፎነት በተጨማሪ የአካባቢ መጎዳት በማየሉ እፅዋትና እንስሳት ሙሉ በሙሉ ወደመሟጠጡ ተቃርበዋል፡፡ የእንስሳት መኖና ሕክምና ችግር በዚህ ላይ ሲጨመርበት የአርብቶ አደሮች ሕይወት ምን ያህል አሳዛኝ እንደሆነ መገመት አያዳግትም፡፡*

*ቆላማው የሀገሪቱ ክፍል መጠነ ሰፊ የመስኖ ፖቴንሽያል ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ የኢነርጂና የማእድን ፖቴንሽያልም እንዳለው በተጨባጭ ጥናቶች የተረጋገጠ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ገና በዝርዝር ተጠንቶ ያላለቀ፣ ነገር ግን የሚያኮራ ሰፊ ባህላዊና ልማዳዊ ሀብት አላቸው፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ላለፉት 3000 እና 4000 ዓመታት የራሳቸው የሆነ የአካባቢ ማኔጅሜንት ስርዓት ዘርግተው የኖሩ ከመሆናቸውም በላይ የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች የዘረጉት የአስተዳደር ስርዓት በአንዳንድ ገጽታው ከማንኛውም ዘመናዊ የሚባል የአስተዳደር ሥርዓት የማይተናነስ ነው፡፡*

*ከላይ እንደተገለፀው የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች ቁጥር ቀላል አይደለም፡፡ የሚኖሩበት አካባቢ ያለው የተፈጥሮ ሀብትና ፖቴንሽያል ከፍተኛ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ሕዝቡ ተረስቶ የቆየና አካባቢውም ከፍተኛ የመሰረተ ልማት ችግር ያለበት ነው፡፡ ለዚህ ዋነኛው ምክንያት በሀገሪቱ ውስጥ የነበሩትና አሁንም ያለው አገዛዝ ለአርብቶ አደሮች ያለው ግምትና ትኩረት ዝቅተኛ መሆኑ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ በየዘመኑ ስልጣን ላይ የሚወጡ አገዛዞች የአርብቶ አደሩን አካባቢ ሕይወት ከመሰረቱ የሚቀይር የልማት አጀንዳ አልነበራቸውም፡፡ አልፎ አልፎ የተደረጉ ሙከራዎች ካሉም አርብቶ አደሮችን በቀጥታ የሚያሳትፉና የሚያለሙ ሳይሆኑ አነስተኛ የሰው ጉልበት የሚፈልጉና ምርታቸውንም ወደ ሌላ ገበያ ሸጠው ትርፍ ለማግኘት የሚሰማሩ ኮመርሽያል እርሻዎች ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በማዕከላዊ መንግስት ቁጥጥር ስር የሆኑና በቱሪስት ገቢ ማስገኛነት የሚያገለግሉ ብሔራዊ ፓርኮችና ጥብቅ ክልሎች ናቸው፡፡ እነዚህ ልማቶች ለአርብቶ አደሩ ሕይወት መሻሻል ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ በማድረግ ፋንታ ለአርብቶ አደሮች ሰፈራና ለከብቶቻቸው ግጦሽ አመቺ ከሆኑት የወንዝ ተፋሰሶች ተፈናቅለው እንዲወጡ በማድረጋቸው ሕይወታቸውን ይበልጥ አወሳስበውታል፡፡*

*አሁንም ያለው ሁኔታ ከፕሮፓጋንዳው ጋጋታ ባሻገር ከበፊቱ የተለየ ነው ሊባል የሚችል አይደለም፡፡ የአርብቶ አደሮችን ሕይወት በቀጥታ የሚመለከት ሰፊ ልማት አልተካሄደም፡፡ እንዳውም ከቀድሞው በከፋ ደረጃ አርብቶ አደሮች የሚኖሩባቸውንና ታዳጊ ክልሎች የሚላቸውን አካባቢዎች የአሁኑ መንግስት የሚገዛቸው ከማዕከል እየመደበ በሚልካቸው*

ሞግዚቶች አማካይነት ነው:: በእነዚህ አካባቢዎች የቆየውንና በተወሰነ ደረጃ ዴሞክራሲያዊ ገጽታ የነበረውን ባህላዊና ልማዳዊ የአስተዳደር ዘይቤ ጨርሶ እያጠፋው ነው::

በእነዚህ አካባቢዎች የመንግስት ስልጣን እንዲይዙ አገዛዙ እየመረጠ የሚያስማራቸው ሰዎች በአርብቶ አደሮች ዘንድ የማይፈለጉትን፣ እምነት የማይጣልባቸውንና እንዲያውም የአካባቢውን ወግና ባህል በሚገባ የማያውቁትን ካድሬዎች ነው:: እነዚህ የአገዛዙ ካድሬዎች በአርብቶ አደሮች መካከል የጎሳ ግጭቶች እንዲስፋፉ በማድረግ አካባቢዎቹን ሰላምና መረጋጋት የሌላቸው የጦርነት ቀጠናዎች አድርገዋቸዋል:: የእርስ በርስ ግጭቶችን የሚያስወግዱበትን ባህላዊ ስርዓት አገዛዙ እንደጠቃሚ ነገር አድርጎ ስለማይቆጥረው በዚህ ምትክ በራሱ ፍላጎት የሚቀርፀውን አጀንዳ በላያቸው ላይ መጫን «የሰላም፣ የዴሞክራሲና የልማት ኮንፈረንስ» የሚል መድረክ እየከፈተ ውጤት የሌለው አሰልቺ ስብሰባ በተደጋጋሚ ጊዜ ያካሂዳል:: ተሰብሳቢዎቹ ከስብሰባ መድረኩ ሳይወጡ አካባቢዎቹ ተመልሰው በግጭትና የእርስ በርስ ጦርነት ይናጣሉ::

የታዳጊ ክልሎች ማዕከል የሆኑትን ቦታዎች ከአርብቶ አደሮቹ ፈቃድና ፍላጎት ውጭ አገዛዙ ራሱ የመረጣቸው በመሆኑ በእነዚህ ማዕከሎች የሚካሄዱትን የቢሮ ግንባታዎች አርብቶ አደሮቹ በበጎ አይን አይመለከቷቸውም:: በእነዚህ ማዕከሎች ዙሪያ ለአገዛዙ ካድሬዎች የሚያገለግሉ የመሰረተ ልማት እንቅስቃሴዎችን ከማድረግ ባሻገር አርብቶ አደሮችን በቀጥታ በሚመለከቱ የልማት ስራዎች ረገድ የተደረገና ትርጉም ያለው ውጤት ያስገኘ እንቅስቃሴ የለም:: አሁንም አርብቶ አደሩ ከወባ ወረርሽኝ፣ ከጎርፍ፣ ከድርቅ፣ ከግጦሽ ችግር፣ ከግጭትና ከመንከራተት አልዳነም:: በራሱ ጉዳይ ላይ ሀሳቡን የመስጠትና መሪዎቹን በነፃነት መርጦ የመወከል መብት የለውም:: በሀገር ደረጃ በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች ቀረፃና አፈፃፀም ላይ ተሳትፎ ስለማያደርግ ከፖሊሲ አውጭዎች እይታ እንደራቀ ነው::

የአርብቶ አደሮች ጉዳይ የአለምን ትኩረት በሳበበት በአሁኑ ዘመን የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች እንደተረሱ ናቸው:: እ.ኤ.አ በ1992 በሪዮ ዲ. ጀኔሮ የተካሄደው አለም አቀፍ ጉባኤ የአካባቢ ጥበቃን በሚመለከት የደረሰበት ስምምነት የአርብቶ አደሮችን መብት ያካተተ ነው:: የአለም ባንክና አለም አቀፍ የስራ ድርጅት ለፓስቶራል ልማት የተወሰኑ ፕሮግራሞችን ቀይሰዋል:: እነዚህ ተቋሞች ከረጅም ጊዜ በፊት አንስቶ በኢትዮጵያ ላሉት አርብቶ አደሮች ልማት ድጋፍ የማድረግ ፍላጎትና ዝግጅት ቢያሳዩም ውጤታማ ስራ የሚሰሩበት ሁኔታ ባለመመቻቸቱ የአርብቶ አደሮች ሕይወት በየጊዜው አስከፊ እየሆነ ነው::

የአርብቶ አደሮች ጉዳይ ተገቢ ትኩረት ስለማይሰጠው የአሁኑ አገዛዝ በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ውስጥ አንድ መምሪያ ከማቋቋምና ሞግዚቶችን እየላከ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ቁጥጥር ከማድረግ በስተቀር የሚጨበጥ ነገር አላደረገም:: በፌዴራል መንግስት ውስጥ ያላቸው ውክልና ለይስሙላ የሚደረግና ለዚያውም ሕዝቡ የማይፈልጋቸውንና ውክልና ያልሰጣቸውን ሰዎች አገዛዙ ራሱ እየመረጠ የሚመድብበትን አሰራር የተከተለ ነው::

ስለዚህ የአርብቶ አደሮችን ሕይወት ለመለወጥ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ መሰረታዊ ጉዳዮች በሚገባ ተለይተው ዘላቂና አስተማማኝ ልማት በአካባቢው መሰራት ይኖርበታል:: ከሁሉ በፊት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ አርብቶ አደሮች የራሳቸውንና የአካባቢያቸውን ጉዳይ በሚመለከት ሀሳብ እንዲሰጡ፣ በፌዴራል መዋቅር ያላቸው ተሳትፎ እንዲጨምር፣ በፖሊሲ ቀረፃና አፈፃፀም ሰፊ ተሳትፎ እንዲኖራቸውና በእነዚህ አካባቢዎች የሚካሄዱ የልማት ፕሮግራሞች የእነርሱን ፍላጎት ጥቅም ያገናዘቡ እንዲሆኑ ማድረግ ነው::

ከዚህ ጎን ለጎን ሰፊ የመሰረተ ልማት ፕሮግራሞች ተቀይሰው አርብቶ አደሮች ሰፊ የትምህርት፣ የጤና፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ፣ የኤሌክትሪክ፣ የስልክ፣ የትራንስፖርትና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች እንዲያገኙ መደረግ አለበት:: የመሰረተ ልማት ግንባታዎችን ተከትሎ አርብቶ አደሮች የተረጋጋ ኑሮ መመስረት የሚያስችላቸው ሰፈራ እንዲካሄድና ከመንከራተት የሚድኑበት ዘላቂ የሕይወት አቅጣጫ እንዲይዙ የሚያበቃ ስራ መሰራት አለበት:: ራሳቸው መክረው የሚወስኑት የመሬት ፖሊሲ በማውጣት ለመኖሪያ፣ ለእርሻ፣ ለግጦሽና ለሌላም አገልግሎት የሚውለው በሚገባ ተለይቶ የአርብቶ አደሮች ሕይወት የተረጋጋ እንዲሆን ሰፊ ስራ መሰራት አለበት:: በእንስሳት እርባታ ያላቸው ባህላዊ ልምድ በዘመናዊ

አሰራር እንዲተካ በማድረግ ለገበያ የሚሆን እርባታ እንዲያካሂዱ፣ ከእርባታው ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዲያገኙና ከድካማቸው ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ገቢ እንዲኖራቸው የሚያስችል ፕሮግራም ተዘርግቶ በስራ ላይ መዋል አለበት፡፡

የአርብቶ አደሮች አንዱ መሰረታዊ ችግር የእንስሳት መኖና ሕክምና እጥረት እንደመሆኑ በእነዚህ አካባቢዎች የሚቀየስ የልማት ፕሮግራም ለእነዚህ ችግሮች መፍትሔ የሚያስገኝ ሆኖ መዘጋጀት አለበት፡፡ የመሬትና የውሃ አጠቃቀም ስርዓቱን በማሻሻል የአካባቢ ጉዳትን በሚያስቀርና ነገር ግን የእንስሳቱን የውሃና የመኖ ፍላጎት በሚያሟላ መንገድ እንዲያገለግል ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ለእንስሳቱ ውሃና መኖ ከማሟላት ጎን ለጎን የተጎዳውን አካባቢ እንዲያለሙና እንዲንከባከቡ የሚያደርግ አሰራር ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡

የኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች እንስሳት ለማርባት ከአንዱ ጫፍ ወደ ሌላው ጫፍ ከአመት እስከ አመት ሲባክኑ ቢኖሩም ከእንስሳት እርባታ የሚያገኙት ጥቅም ከድካማቸው ጋር የተመጣጠነ አይደለም፡፡ ለዚህም ዋነኛው ምክንያት እርባታው ለገበያ ተብሎ የማይካሄድ መሆኑና ገበያ ቢፈልጉም እንኳ የመረጃ ችግር ያለባቸው መሆኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ ለክፉ ቀን መጠባበቂያ የሚሆን ጥሪት ሳያስቀሩ ድርቅ በመጣ ቁጥር በስንት ድካም ያረቧቸው እንስሳት ሙሉ በሙሉ እያለቁ ድካማቸው ሁሉ መና ይቀራል፡፡ ስለዚህ የእንስሳት እርባታው የዕለት ከዕለት ፍላጎት ከማሟላት ባሻገር ለጥሪት ማፍሪያና ለካፒታል ምስረታ የሚጠቅም ቁጠባ እንዲካሄድበት ለገበያ በሚሆን መንገድ መቃኘት ይገባዋል፡፡ በመንግስት በኩል የገበያ መረጃ አገልግሎት የሚሟላበት መንገድ መመቻቸት ይኖርበታል፡፡ ሌሎች ገበያውን የሚያሰፉ የልማትና የኢንቨስትሜንት እንቅስሴዎች አርብቶ አደሩ በሚኖርበት አካባቢ ቀረብ ብለው እንዲስፋፉ የግል ባለሀብቶችን የሚያደፋፍሩ የፖሊሲ እርምጃዎች መውሰድ ይገባል፡፡

በአርብቶ አደሩ አካባቢ በእንስሳትና በእንስሳት ተዋፅኦ ልማት ኢንቨስት ለሚያደርጉ የግል ባለሀብቶች ለተወሰነ ጊዜ ከግብር ነፃ የሚያደርግ፣ ለኢንቨስትሜንት ስራቸው ከውጭ የሚያስገቧቸውን ማሽነሪዎችና የመገልገያ መሣሪያዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲያስገቡ የሚያስችል፣ የምክርና የብድር ድጋፍ ለማሟላት የሚረዳ ማበረታቻ በመንግስት በኩል ሊደረግላቸው ያስፈልጋል፡፡ መንግስት ይኸንን በማድረግ ከሚያወጣው ወጪ ይልቅ ይኸንን ባለማድረጉ የሚደርስበት ኪሣራ የበለጠ መሆኑን በማመን ልዩ ትኩረት መስጠት አለበት፡፡ የአርብቶ አደሮችን ሕይወት ከመለወጥና የተረጋጋ ዘላቂ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ከማድረግ አኳያ መንግስት የሚያደርገው ልዩ ልዩ ድጋፍ ትልቅ አስተዋፅኦ እንደሚኖረው በማመን በዚህ መስክ ለሚሰማሩ የግል ባለሀብቶች ማበረታቻ ማቅረብ አለበት፡፡

በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚገኙ የቱሪስት መስህቦች ከሚያስገኙት ጥቅም የአካባቢው ሕዝብ ተቋዳሽ እንዲሆን ማድረግ የተጎዳውን የተፈጥሮ አካባቢ ደህንነት በመጠበቅ የኃላፊነትና የባለቤትነት መንፈስ እንዲዳብር ስለሚረዳ በአካባቢው የሚመሰረቱ የአስጎብኝ ድርጅቶች፣ የጉዞ ወኪሎች፣ የቱሪስቶች መቀበያና ማስተናገጃ ተቋሞች የአርብቶ አደሩን ቀጥተኛ ተጠቃሚነት ግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ እንዲቋቋሙና እንዲሰሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአርብቶ አደሮች አካባቢ የሚከሰቱ ግጭቶች እንዲወገዱ በአካባቢው የነበሩትን ጠቃሚ የግጭት አፈታት ልምዶችና ባህሎች ይበልጥ ውጤታማ በሆነ መንገድ ስራ ላይ እንዲውሉ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ከመደበኛው የመንግስት መዋቅር በተጓዳኝ ልማዳዊና ባህላዊ የአስተዳደር ዘይቤዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ በማድረግ ከዘመናዊው የአስተዳደር ስርዓት ጋር ቀስ በቀስ ለመለማመድ እንዲችሉ ማድረግ ከባህላዊው ሁኔታ ወደ ዘመናዊው አሰራር የሚደረገውን ሽግግር ጤናማና ውጤታማ ስለሚያደርገው የዚህ አይነቱን መንገድ መከተል ይገባል፡፡ ከዚህ በፊት አይተውና ሰምተው የማያውቁትን አዳዲስ አሰራር በአንድ ጊዜ በግድ መጫን ዘመናዊነትን በማስገኘት ፋንታ የባህል ወረራና የማንነት መደፈር በደል እንደተፈፀመባቸው አድርገው የሚመለከቱበትን ጎጂ ውጤት ሊያስከትል ስለሚችል መጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡ ለዚህ የተሻለው አማራጭ በልማት ፖሊሲ ቀረፃና አፈፃፀም ሂደት አርብቶ አደሮች በቀጥታ ወይንም በሚያከብሯቸውና ራሳቸው በሚወክሏቸው ሰዎች አማካይነት ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው፡፡ ጠቃሚ የሆኑትን ባህላዊ የማኔጅሜንት ስርዓቶችን የምክክር ጉባኤዎችንና የግጭት አፈታት ዘይቤዎችን ከመደበኛው ዘመናዊ አሰራር ጎን ለጎን በስራ ላይ እንዲያውሏቸው በማድረግ ወደመደበኛው ዘመናዊ ስርዓት የሚደረገው ሽግግር በእርጋታ እንዲካሄድ ማስቻል በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

# 1.6 የውሃ ሀብት ልማት

## 1.6.1 የውሃ ሀብት ልማት ያለበት ሁኔታ

ኢትዮጵያ ባላት መልክዓ-ምድራዊ አቀማመጥና ተስማሚ የአየር ጠባይ በአካባቢው ካሉት አገሮች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ መጠን ያለው ዝናብ ታገኛለች፡፡ ይሁን እንጂ ይህ መጠን ከፍተኛ ቢሆንም አብዛኛው ማለትም በዓመት 110 ቢሊዮን ሜትር ኩዩብ ገደማ የሚገመት ውሃ በወሰን ተሻጋሪ ወንዞቿ አማካኝነት ወደ ጎረቤት አገሮች የሚፈስ ነው፡፡ ከ80 እስከ 90 በመቶ የኢትዮጵያ ውሃ ሀብት የሚገኘው በአባይ፣ በተከዜ፣ በባሮ-አኮቦና በኦሞ-ጊቤ ተፋሰሶች ውስጥ ነው፡፡ የኢትዮጵያ የውሃ ሀብት ትልቁና ዋናው ችግር የውሃ ቦታውና ወቅታዊ ግኝቱ የተዛባ መሆኑ ነው፡፡

እስከ አሁን በተደረገው የውሃ ሀብት ልማት እንቅስቃሴ ከጠቅላላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የንፁሕ ውሃ አቅርቦት አገልግሎት ተጠቃሚ ከ20 ከመቶ አይበልጥም፡፡ እዚህ ላይ አገልግሎቱን ያገኛል ተብሎ የተጠቀሰው መጠን ከውሃው አቅርቦት አስተማማኝነትና ዘላቂነት አኳያ ሲታይ የሽፋኑን መጠንና አቅርቦቱን አስተማማኝነት በከፍተኛ ደረጃ እንደሚያሳንሰው ግምት ውስጥ መግባት ይኖርበታል፡፡ ይህም የኢትዮጵያ ሕዝብ ጤንነትና ምርታማነት ምን ያህል ችግር እንዳለበት ግልጽ ያደርገዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ኢትዮጵያ ከፍተኛ ግምት ያለው ለመስኖ ልማት ተስማሚ የሆነ መሬት ያላት ቢሆንም፣ እስካሁን የለማው ግን ከሦስት በመቶ አይበልጥም፡፡ ይህም እስካሁን ድረስ የውሃ ሀብታችን ለመስኖ እርሻ ልማት ዘርፍ ያደረገው አስተዋጽኦ እጅግ አነስተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

በውሃ ሀብት ረገድ ሌላውና ትልቁ የኢትዮጵያ ሀብት ከውሃ የሚመነጭ ኃይል ነው፡፡ ኢትዮጵያ ተፈጥሮ በለገሳት ተራራማ የገፀ ምድር አቀማመጥ የተነሳ ዝቅተኛ በሆነ ወጪ የውሃ ኃይል ማመንጨት ትችላለች፡፡ ሆኖም ከዚህ ዘርፍ እስካሁን ለምቶ ጥቅም ላይ የዋለው እጅግ በጣም አነስተኛ ነው፡፡ ይህ ሀብት ባግባቡ ቢለማ የአገር ውስጥ የኃይል አቅርቦትን በቀላሉ ከመሸፈን አልፎ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ምንጭ ሊሆን ይችላል፡፡

## 1.6.2 አንፃራዊ የመስኖ ልማት

ድርቅ በየትኛውም አገር በተደጋጋሚ የታየ ወደፊትም በተደጋጋሚ የሚታይ ተፈጥሮአዊ ክስተት ነው፡፡ ድርቅ ዓለም አቀፋዊ ሥርጭት ያለው ተፈጥሮአዊ ክስተት መሆኑን ለማሳየት ያህል በየአህጉሮች ከተከሰቱ ድርቆች ጥቂት ምሳሌዎች ማቅረብ ይቻላል፡፡

በአፍሪካ ውስጥ እ.ኤ.አ በ1885 የነበረው ድርቅ ኢትዮጵያን ጨምሮ 24 አገሮችን ለከፍተኛ ችግር ያጋለጠ ነበር፤ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን ለሞት ተዳርገዋል፡፡ ከ1769-70 በሕንድ 7 ሚሊዮን፣ ከ1876-79 በቻይና 11 ሚሊዮን፣ ከ1920-21 በሩሲያ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ፣ ሰዎች ለሞት ተዳርገዋል፤ ከዚህ በተጨማሪ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ለስደት ተዳርገዋል፡፡ ብራዚል ውስጥ በ1983 ድርቅ የተነሳ 17 ሚሊዮን ሰዎች አካባቢያቸውን ለቀው ተሰደው ነበር፡፡ እ.ኤ.አ 1982-83 አውስትራሊያ ውስጥ የስንዴ ምርት በ3.5 ሚሊዮን ቶን ወይም 58 በመቶ ቀንሶ ነበር፡፡ እ.ኤ.አ. በ1930 በካናዳ የደረሰው ድርቅ 7.3 ሚሊዮን ሄክታር የእርሻ መሬት ላይ ጉዳት ሲያስከትል ሩብ ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች ቤታቸውን ጥለው እንዲሰደዱ አድርጓል፡፡ ከ1937-45 በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ ከሜክሲኮ እስከ ካናዳ ባሉ አካባቢዎች የምግብ እጥረትና የውሃ ኃይል እጥረት ተፈጥሮ ነበር፡፡ በእንግሊዝና በፈረንሳይ ኢኮኖሚም ላይ ከፍተኛ ጉዳት ያስከተሉ የድርቅ ክስተቶች ተመዝግበዋል፡፡

ድርቅ በተለያዩ አገሮች ከፍተኛ ጉዳት ያደርስ እንደነበር ቢታወቅም አሁን ግን በእድገታቸው ወደ ኋላ ከቀሩ አገሮች በስተቀር ድርቅ ቢከሰትም የሚያደርሰው ጉዳት አነስተኛ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ድርቅ ርሃብን አስከትሎ በሕይወት ላይ አደጋ የሚያስከትለው እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ድሃ አገሮች ላይ ብቻ ነው፡፡

ቀደም ብለው በድርቅ ሳቢያ ሲሰቃዩ ከነበሩ አገሮች ብዙዎቹ አሁን ተመሳሳይ ድርቅ ቢከሰትም የከፋ ችግር እንዳያስከትል ማድረግ ችለዋል:: ችግር ፈቺ የሆነ ተስማሚ የአፈር ጥበቃ የግብርና ዘዴችን ዘርግተዋል:: በተለይም የመስኖ እርሻ ማስፋፋትን እንደ ዋነኛ ለችግሩ መፍትሔ አቅጣጫ በማድረጋቸው ከፍተኛ ውጤት አግኝተውበታል:: ወቅታዊ የሆነ የምግብ እጥረት ሲያጋጥማቸውም መሸመት የሚያስችል ሁለንተናዊ አቅም ገንብተዋል:: የድርቅ መከሰት የምርት መጠንን ቢቀንስ እንጂ እንደ ጥንቱ ረሃብና የሰው እልቂት ሊከሰት ከማይችልበት ደረጃ ደርሰዋል:: እድገታቸው አበረታች የሆኑ አገሮች ድርቅን ይኸ ነው የሚባል ጥፋት ሳያደርስ በአስደናቂ ሁኔታ ለመቋቋም ችለዋል::

በአሜሪካና በኢራቅ ገበሬዎች በአማካይ 4.5 ሄክታር የሚሆን በመስኖ የለማ መሬት ሲኖራቸው በእስራኤል፣ በአውስትራሊያ፣ በፈረንሳይ፣ በቆጵሮስ፣ በጣሊያን፣ በስፔይን፣ እና በቺሊ ደግሞ በአማካይ 2.5 ሄክታር አላቸው:: እንዲሁም በፖርቱጋል፣ በቡልጋሪያ፣ በደንማርክ፣ በሩሲያ፣ በጃፓን፣ በካናዳ፣ እና በአርጀንቲና ያሉ ገበሬዎች በአማካይ 1.0 ሄክታር በመስኖ የሚለማ መሬት አላቸው:: በሊቢያ፣ በግሪክ፣ በፓኪስታን፣ በሀንጋሪ፣ በኢራን፣ በሊባኖስ፣ እና በጆርዳን ያሉ ገበሬዎች ደግሞ በአማካይ 0.7 ሄክታር ሲኖራቸው፤ በግብፅ፣ በኒውዝላንድ፣ በኩባ፣ በጃማይካ፣ በዛምቢያ፣ በሕንድ፣ በቻይና፣ እና በደቡብ ኮሪያ ያሉ ገበሬዎች በአማካይ 0.3 ሄክታር በመስኖ የሚለማ መሬት አላቸው:: እንዲሁም በአልጀሪያ፣ በቱኒዚያ፣ በደቡብ አፍሪቃ፣ እና በሱዳን ያሉ ገበሬዎች በአማካይ ከ0.1 ሄክታር ያላነሰ በመስኖ የለማ መሬት አላቸው::

የገበሬዎች ብዛት ከጠቅላላው ሕዝብ ብዛት ከሦስት ከመቶ ያነሱ ከሆኑባቸው አገሮች ውስጥ ፈረንሳይ፣ ጣሊያን፣ ዴንማርክ፣ ኢራቅ፣ እስራኤል፣ ሊባኖስ፣ ጆርዳን፣ ጃፓን፣ አውስትራሊያ፣ አሜሪካ፣ ካናዳና አርጀንቲና ይገኙበታል:: የገበሬዎች ብዛት ከ3-5 ከመቶ ከሆኑኑባቸው አገሮች ውስጥ ደግሞ ሊቢያ፣ ቆጵሮስ፣ ስፔን፣ ፖርቹጋል፣ ሀንጋሪ፣ ኒውዚላንድ፣ እና ቺሊ ይገኙበታል:: የገበሬዎች ብዛት ከ6-10 ከመቶ የሆኑባቸው አገሮች ውስጥ አልጀሪያ፣ ቱኒዚያ፣ ሩስያ፣ ደቡብ ኮርያ፣ ኢራን፣ ግሪክ፣ ሜክሲኮ፣ ኩባ፣ ጃማይካ፣ ግብፅ፣ እና ደቡብ አፍሪካ ይገኙበታል:: በተጨማሪም ቡልጋሪያና በፓኪስታን ደግሞ 12 ከመቶ ይሆናል:: እንዲሁም በዛምቢያ፣ ሱዳን፣ ሕንድ፣ ቻይና ከ20 በመቶ በላይ ነው:: በዚህ እረገድ ኢትዮጵያ ያለችበትን ሁኔታ ለንፅፅር ለማቅረብም ያስቸግራል::

ከዚህ ጋር የኢትዮጵያን የመስኖ ልማት ስንመለከተው በጣም ከሚያሳዝን እጅግ ዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው:: በኢትዮጵያ የተደረሰበት የመስኖ ልማት ደረጃ በተመሳሳይ መለኪያ ሲለካ፣ በአማካይ የአንድ ገበሬ ድርሻ ከ0.01 ሄክታር ያነሰ ሆኖ እናገኘዋለን:: ከቻይናና ከሕንድ ጋር እንኳን ተመጣጣኝ ለማድረግ ብንፈልግ አሁን ያለውን ሁኔታ በትንሹ 30 ጊዜ ማሳደግ ይኖርብናል::

በአማካይ የአንድ ገበሬን ዓመታዊ ምርት ብንመለከት በአሜሪካና በካናዳ ከ2000 ኩንታል በላይ ሲሆን፣ በፈረንሳይ 800 ኩንታል፣ በሩሲያ 110 ኩንታል፣ በቻይና 40 ኩንታል በህንድ 27 ኩንታል ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ አራት ኩንታል ገደማ ነው:: የአንድ ኢትዮጵያዊው ገበሬ ዓመታዊ ምርት የቻይናዊ ገበሬን ያህል እንዲያድግ ብንፈልግ አሁን ካለበት 10 ጊዜ ማደግ አለበት ማለት ነው:: ይህንን ማድረግ ከተፈለገ ደግሞ በመስኖ ልማት፣ በከፍተኛ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም፣ በምርጥ ዘር አጠቃቀም፣ በማዳበሪያ አጠቃቀም፣ በአካባቢ ጥበቃ፣ እና በመሳሰሉት ማደግ እንደሚጠበቅብን መገመት አያስቸግርም::

በኢትዮጵያ ካሉ ሠራተኞች ውስጥ 85 በመቶዎቹ የተሠማሩት በግብርናው ዘርፍ ሲሆን በኢንዱስትሪው ዘርፍ የተሠማሩት ስምንት ከመቶ ብቻ ናቸው:: በአንፃሩ ደግሞ በቻይና ደግሞ ከጠቅላላ ሠራተኞች ውስጥ 50 በመቶዎቹ በግብርና 25 ከመቶዎቹ በኢንዱስትሪው ዘርፍ ይገኛሉ:: ከዚህ የምንረዳው ቻይና ከኢትዮጵያ የምትለየው የዝናብ እርሻ ጥገኛነቷ አነስተኛ ከመሆኑም በላይ በእርሻው ዘርፍ ጥገኛ የሆኑት ሰዎች ከጠቅላላው ግማሽ ብቻ መሆናቸውና ሩብ የሚሆኑት በኢንዱስትሪው ዘርፍ መሠማራታቸውን ነው::

## 1.6.3 የመስኖ ልማትን ማስፋፋት

በመሠረቱ በአገራችን ያለው የርሃብ አደጋ ወቅታዊ ብቻ ሳይሆን በጣም ሥር የሰደደ ነው:: ድርቅ ሳይከሰት እንኳን አማካይ የምግብ ፍጆታችን ለተሟላ ጤናና አካላዊ ብቃት ከሚያስፈልገው ሁለት ሦስተኛ ብቻ ነው:: ይህም ሊሟላ የቻለው በለጋሾች በሚደረገው ለብዙ

ዓመታት ያላቋረጠ የምግብ ርዳታ ነው:: አሁን ባማካይ የሚመረተውን ግማሹን ያህል ተጨማሪ ምግብ ማምረት ብንችል በምግብ እራሳችንን ቻልን ማለት ይቻል ነበር:: በተለይም አብዛኛው የኢትዮጵያ ገበሬ በቂ ምግብ ስለሌለው የሚኖረው በሞትና በሽረት መካከል ነው - ከሞቱት በላይ፣ ከሚኖሩት በታች ሆኗል:: ረሃቡ የሚጠናው በአምራቹ ገበሬ ላይ መሆኑ ደግሞ የሚያሳዝን ጉዳይ ነው::

በአገራችንም በተደጋጋሚ እየተከሰተ ብዙ ወገኖቻችንን ለእልቂት ለዳረገው ድርቅ መፍትሔ ማግኘት አለብን:: የእርሻ መሬት ጥበት ባላቸው አካባቢዎች በተወሰነ የእርሻ መሬት ላይ የተሻለና ከፍተኛ የሰብል ምርት የሚያስገኝ የልማት አቅጣጫን መከተል አስፈላጊ ነው:: በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የሚገኙትን ለእርሻ ተስማሚ የሆኑ ድንግል መሬቶችም መጠቀም የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል:: ከሁሉም በላይ ግን የመስኖ እርሻ ልዩ ትኩረት መሰጠት አለበት::

በኢትዮጵያ ውስጥ የዝናብ እርሻ አስተማማኝ ሊሆን የሚችልባቸው አካባቢዎች ውስን ናቸው:: የሕዝብ ቁጥር እያደገ በሄደ መጠን እርሻም መስፋፋት ይኖርበታል:: ከኢትዮጵያ የቆዳ ስፋት አብዛኛውን እየተጠቀምንበት አይደለም:: አሁን እየታረሰ ካለው የበለጠ መሬት ለእርሻ መዋል አለበት:: ይህ የሚቻለው ደግሞ በዋነኛነት በመስኖ ነው:: በዝናብ ብቻ የምንተማመን ከሆነ በምግብ እጥረት በኩል የሚያጋጥመን ችግር እየተባባሰ ይሄዳል:: አሁንም ሆነ ወደፊት ዝናብ ብቻውን የትም አያደርሰንም:: ለምግብ እጥረትና ችጋር የተጋለጥነው የዝናብ ጥገኛ በመሆናችን ነው:: ኢኮኖሚያችን በዝናብ ላይ የተመሠረተ ግብርና ጥገኛ መሆኑ ከቀጠለ ከድርቅና ርሃብ መላቀቅ አንችልም:: በመሆኑም ችግራችንን መቀነስ ከፈለግን የመስኖን አማራጭ መጨመር አለብን:: በመስኖ ከተጠቀምን በአንድ ማሳ ላይ በዓመት ሁለት ሦስት ጊዜ ማምረት ስለምንችል የመሬት መጣበብ ችግር ይቀንሳል፣ የመሬቱም ምርታማነት ይጨምራል:: የመስኖ መስፋፋት የምግብ ዋስትና ከማስገኘቱም በላይ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች የሥራ ዕድል መፍጠር ያስችላል::

የመስኖ እርሻ ግድ ለምግብ ሰብል ምርት ይዋል ማለት አይደለም:: የመስኖ እርሻ የበለጠ አዋጭነት የሚኖረው በዝናብ ብቻ ሊመረቱ በማይችሉት ለኢንዱስትሪ ግብዓትነት ተፈላጊ ለሆኑ በተለይም ዓመታዊ የፋይበር፣ የስኳርና የምግብ ሰብሎች ቢውል ነው:: የመስኖ እርሻና ኢንዱስትሪ በተሳሰረ መልኩ ከተስፋፉ ውጤታማ ይሆናሉ::

በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ በመስኖ ለማልማት ከሚቻለው ውስጥ የለማው ከሦስት በመቶ ያነሰ ነው:: የዛሬ 35 ዓመት ገደማ ሠፋፊ የመስኖ እርሻዎች በተለይም በአዋሽ ሸለቆ በጥሩ ሁኔታ ማልማትና ማስፋፋት ተጀምሮ ነበር:: በዚያ ወቅት የለሙት የመስኖ እርሻዎች እስካሁን ድረስ ለስኳር ምርት የሚሆን ሸንኮራ አገዳ፣ ለልብስ የሚሆን ጥጥና የተለያዩ ፍራ-ፍሬዎች እንድናመርት አስችለውናል:: ከዚያ በኋላ የመስኖ እርሻ ማስፋፋት እንቅስቃሴያችን ስለቀዘቀዘ አሁን ለደረስንበት የምርት እጥረትና የሥራ አጥነት ደረጃ በቅተናል:: በመስኖ እርሻ የሚገኘው ምርት በአብዛኛው በቀጥታ ለአምራቹ ለምግብ ፍጆታ ባይውልም ተሽጦ ተለውጦ ወይም ገቢ የሚያስገኝ ሥራ በመፍጠር በተዘዋዋሪ ምግብ ለመሸመት የሚያስችል ገቢ ያስገኛል ማለት ነው::

የመስኖ እርሻ ሥራ ከዝናብ እርሻ ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ የገንዘብና የቴክኒክ አቅም የሚጠይቅ ቢሆንም ባለሀብቶችን በመስኖ ሥራ እንዲሰማሩ ምቹ ሁኔታ በመፍጠርና በማበረታታት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል:: ለመስኖ እርሻ አገልግሎት የሚውሉ በወንዞች ላይ የሚሠሩ መጥለፊያዎች፣ ግድቦች፣ ማጠራቀሚያዎች፣ ከፍተኛ ቦዮች እና ሌሎች ከፍተኛ ወጪ የሚጠይቁ ውሃ ጋር የተያያዙ መሠረተ ልማቶችን በመንግሥት በኩል እንዲሠሩና እንዲተዳደሩ በማድረግ ውሃን ለተገልጋዮች በመሸጥ የዋጋ መመለስ ሥልትን መከተል አግባብነት አለው::

በበርካታ የግብርና ባለሙያዎችና መሐንዲሶች ዘንድ በመስኖ የሚለማ የመሬት መጠንና የውሃ ማከማቻ መጠንን የማደበላለቅ ሁኔታ ይታያል:: አንድ ከፍተኛ የውሃ ማቋቻ ለብዙ አነስተኛ መጠን ላላቸው እርሻዎች ወይም ለጥቂት መካከለኛና ሠፋፊ እርሻዎች መጠቀም እንደሚቻል ይዘነጋል:: ስለሆነም የውሃ ሥራዎችን ከእርሻዎች መጠንና ብዛት ጋር አንድ አድርጎ የማየት አካሄድ ደጋግሞ ያጋጥማል:: እውነታው ግን አመቺና ተስማሚ ቦታዎች ላይ ግድብ በመገንባት የክረምቱን ውሃ በመቋጠር በበጋ ወቅት ለበርካታ አነስተኛ፣ መካከለኛና ሠፋፊ የመስኖ እርሻዎች ማዋል ይቻላል::

*ለዚህም የአዋሽ ሸለቆን ሁኔታ እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል። በአሁኑ ጊዜ በአዋሽ ወንዝ ላይ የተገነባው ግድብ ቆቃ ብቻ ነው። ከ50 ሜትር ያነሰ ከፍታ ባለው በቆቃ ግድብ አማካይነት ገሊላ የሚባል ብዙ ውሃ የሚይዝ ሰው ሠራሽ ሐይቅ መፍጠር ተችሏል። በዚህ ሐይቅ በተከማቸው ውሃ በሦስት የኃይል ማመንጫዎች አማካይነት 110 ሜጋ ዋት የኤሌክትሪክ ሃይል ማመንጨት ከመቻሉም በላይ በወንጂ፣ በመተሃራ፣ በአሚባራ፣ በዱብቲና በሌሎች አካባቢዎች በድምሩ 70 ሺህ ሄክታር ያህል ስፋት ያላቸው በርካታ አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ መጠን ያላቸው የመስኖ እርሻዎችን ማልማት ተችሏል። የአዋሽ ሸለቆ ውሃ አጠቃቀም ለሌሎችም ተፋሰሶች ትምህርት ሰጪ ነው።*

*በሌላ በኩል ደግሞ በተሟላ ሁኔታ ያልተጠቀምንባቸውን ፕሮጀክቶች በምሳሌነት ማቅረብ ይቻላል። አሥር ሺህ ሄክታር ለማልማት ታስቦ በባሮ አኮቦ ተፋሰስ በአልዌሮ ወንዝ ላይ የተገነባው ግድብ ያለአገልግሎት መና ሲቀር፣ የመልካ ዋከና ግድብ ውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል እያመነጨ ቢሆንም በዚያው ውሃ ለማልማት የታሰበው በታችኛው ዋቢ ሸበሌ አካባቢ ሊለሙ የታሰቡ የመስኖ እርሻዎች እስካሁን በተሟላ ሁኔታ ሊለሙ አልቻሉም።*

*የውሃ ሀብታችንን በተገቢው መንገድ ለመጠቀም የሚያስችሉ ቅድመ ሁኔታዎችም መመቻቸት አለባቸው። አቅምን አቀናጅቶ በልማት ለመሠማራት በኅብረት የመሥራት ባሕል መዳበር አለበት። ሁኔታዎች ከተመቻቹ በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የምንገኝ ኢትዮጵያውያን ራሳችን ዕውቀታችንን፣ ገንዘባችንና ጉልበታችንን በአግባቡ አቀናጅተን ከተንቀሳቀስን በውሃ ሀብታችን ተጠቃሚዎች መሆን እንችላለን። ይህ ይሳካ ዘንድ ሁሉም ዜጋ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል።*

## 1.6.4 ወሰን ተሻጋሪ ወንዞች

*ታሪካችን እንደሚነግረን ግብፃዊያን በአሥራ ዘጠነኛው መቶ ክፍለ ዘመን ብቻ 18 ጊዜ የወረራ ሙከራ አድርገውብናል። የሙከራቸው ዋነኛ ምክኒያት የናይልን ተፋሰስ ከምንጩ ጀምሮ በባለቤትነት ለመያዝ መሆኑ ግልጽ ነው። ለዚህ ምኞታቸው መሳካት ይረዳቸው ዘንድ ቀይ ባሕርን በቁጥጥር ሥር ማድረግና አመቺ የመጓጓዣ መስመር ማግኘት የማይታለፍ ስትራቴጂካዊ ጠቀሜታ ነበረው። የሆነው ሆኖ በሁሉም አቅጣጫዎች ማለትም፣ በምዕራብ፣ በሰሜንና በምሥራቅ በተደጋጋሚ ያደረጓቸው ሙከራዎች ሁሉ በጀግኖች አባቶቻችን ተጨናግፈዋል። ይህም ሊሳካ የቻለው በዘመኑ የነበሩት ኢትዮጵያውያን በወቅቱ የሚፈለገውን መስዋእትነት በመክፈላቸው ነው። ግብፅ ከዚያም ወዲህ ማለትም ከሃያኛው መቶ ክፍለ ዘመን ወዲህ ቀጥተኛ ወረራ ለማድረግ ባትሞክርም የናይልን ውሃ በብቸኝነት ለመጠቀም ያላትን ፍላጎት ደጋግማ አሳይታለች። በተለይም ኢትዮጵያ አንዳንድ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያላቸውን ፕሮጀክቶች ለመሥራት ጥረት ባደረገችባቸው ጊዜያት ጦርነት እከፍታለሁ የሚል ተደጋጋሚ ዛቻና ማስፈራራት ፈጽማለች።*

*ኢትዮጵያ በወንዞቿ ምክኒያት ጠላት ያፈራችው በናይል ገባሮቿ ማለትም በአባይ፣ በባሮ-አኮቦና በተከዜ ብቻ አይደለም። በዋቢ-ሸበሌና በገናሌ-ዳዋ በኩልም እንደዚሁ ቀደም ብሎ በጣሊያን ሁለት ጊዜ፣ በኋላም በሶማሊያ ሁለት ጊዜ የወረራ ሙከራ ተቃጥቶባታል። በሶማሊያ በኩል የተደረጉት ወረራዎች የዋቢ-ሸበሌንና የገናሌ-ዳዋን ተፋሰሶች ለመቆጣጠር መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ያመለክታሉ።*

*የኢትዮጵያን ድንበር አቋርጠው የሚፈሱት የናይል ገባሮች ማለትም አባይ፣ ተከዜና ባሮ-አኮቦ ወንዞች ለናይል ወንዝ 86 ከመቶውን ያዋጣሉ። ሆኖም እስከ አሁን ድረስ የዚህ ውሃ ተጠቃሚዎች አንደኛ ግብፅ ስትሆን በሁለተኛነት ሱዳን ትከተላለች። በአሁኑ ጊዜ ከናል ውሃ 88 ከመቶው ለመስኖ አገልግሎት ውሏል። ከዚህ ውስጥ 71 ከመቶውን ግብፅ፣ 23 ከመቶውን ሱዳን ሲጠቀሙበት ቀሪውን 6 ከመቶውን ደግሞ ኢትዮጵያን ጨምሮ ሌሎች ስምንት የተፋሰሱ አገሮች ይጠቀሙበታል። ግብፅና ሱዳን ከናይል በሚያገኙት ውሃ በጠቅላላው በመስኖ ሊለማ ከሚችለው መሬታቸው ውስጥ ሁለቱም 70 ከመቶውን ለማልማት ችለዋል። ኢትዮጵያ ግን በናይል ተፋሰስ ሊለማ ከሚችለው ሁለት ሚሊዮን ሄክታር ውስጥ አንድ ከመቶውን ብቻ ነው ያለማችው።*

ወንዞችን የመጠቀም ልዩነት የመነጨው አንደኛው ከሌላኛው አገር ጋር ሲነፃፀር ያላቸው ፍላጎት መለያየት ነው፡፡ ሌላው ምክኒያት ደግሞ ፍላጎትም ቢኖር ያንን ለማሟላት የሚያስችል የገንዘብ አቅም ማነስ ነው፡፡ በተጨማሪም በተለያዩ መንገዶች አንዱ ሌላውን በመጫኑ ነው፡፡ ለምሳሌ ግብፅንና ኢትዮጵያን ብናይ፣ ፍላጎትን በተመለከተ ግብፅ ከጥንት ጀምሮ ለእርሻ ሊውል የሚችል ዝናብ ስለሌላት የግድ የናይል ወንዝን ለመስኖ መጠቀም ነበረባት፡፡ ኢትዮጵያ ግን እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አብዛኛውን የውሃ ፍላጎትዋን በዝናብ ማሟላት ትችል ስለነበር በወንዝ የመጠቀም ፍላጎትዋ አነስተኛ ነበር፡፡ በአሁኑ ጊዜ ግን በኢትዮጵያ በኩል ሁኔታው ተለውጧል፡፡ በወንዞቻችን ተጠቅመን በሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለውን የርሃብ አደጋ ማሸነፍ አለብን፣ ነገር ግን የገንዘብ አቅም የለንም፡፡

ግብፅ አሁን ከአባይ፣ ባሮ-አኮቦና ተከዜ የምታገኘው ውሃ እንዲቀንስ አትፈልግም፡፡ በአሁኑ ወቅት ከእኛ ይልቅ ግብፅ በኢኮኖሚዋ ጠንካራ በመሆንዋና በአንፃራዊነት በፖለቲካዋም የተረጋጋች በመሆንዋ ባለገንዘቦች ለግብፅ ያደላሉ፡፡ በግብፅ በኩል በሚደረግብን ዲፕሎማሲዊ ተፅእኖ ምክኒያት ከሌላ ወገኖች ማለትም ከዓለም-አቀፍ የፋይናንስ ተቋማትም ሆነ የተለያዩ አገሮች በእርዳታም ሆነ በብድር የሚያስፈልገንን ገንዘብ ማግኜት አልቻልንም፡፡

የድንበር አቋራጭ ወንዞችን አጠቃቀም በተመለከተ ከግብፅ፣ ከሱዳንና ከሱማሊያ ጋር ከፍተኛ ፉክክር ውስጥ እንገኛለን፡፡ በሁሉም አገሮች የሕዝብ ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ስለሚሄድ በውሃ የመጠቀም ፍላጎት እየጨመረ መጥቷል፡፡ ወደፊትም እጅግ በሚያሳስብ ሁኔታ ይጨምራል፡፡ ስለሆነም በድርሻ ወይም በክፍፍል ምክኒያት ውጥረት ይከተላል፡፡ ለዚህ ውጥረት ዋነኛ መፍትሔው ችግሮችን በሰላማዊና ዘመናዊ ግጭት ማስወገጃ መንገድ በውውይትና ስምምነት መፍታት መቻል ነው፡፡ ይህ መንገድ ለታሰበው ውጤት አማራጭ የሌለው ከመሆኑም በላይ ዘለቄታዊነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ግን የውይይት፣ የድርድርና ብሎም የስምምነት መንገድ ቀላልና ልፋት የሌለበት ነው ማለት አይደለም፡፡ ምክኒያቱም ብሔራዊ ጥቅሙን በቀላሉ አሳልፎ የሚሰጥ አገር አይገኝምና ነው፡፡ አንዱ ከሌላው የበለጠ ተጠቃሚ ሊሆን የሚችለው ደካማ አገር ሲገኝና አንዱ ሌላውን ሊያምታታና ሊጫን ሲችል ነው፡፡ አጥጋቢ ስምምነት ላይ ለመድረስ የሚያስችል ድርድር ለማካሄድ በሁሉም ወገኖች ተገቢና ብቁ ዝግጅት መኖር አለበት፡፡ ይህ ካልሆነ የሚደረስበት ስምምነት ዘለቄታዊና ሚዛናዊ ሊሆን አይችልም፡፡ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ በአሁኑ ጊዜ ስለ ናይል ውሃ አጠቃቀም በቂ ዕውቀትና ግንዛቤ ያላት አገር ግብፅ ናት፡፡ በዚህ በኩል ኢትዮጵያ ገና ብዙ ይቀራታል፡፡ በመሆኑም ማንኛውንም ዓይነት የውሃ አጠቃቀም ስምምነት ከማድረጋችን በፊት የተጠናከረ የአቅም ግንባታ ፕሮግራም ማካሄድ ይጠበቅብናል፡፡ በውሃ አጠቃቀም ላይ ሁላችንም የተቀራረበ ግንዛቤ ኖሮን በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ ለብሔራዊ ጥቅማችን ተሟጋች ልንሆን እንችል ዘንድ ብሔራዊ መድረክ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡

# 2. ኢንዱስትሪ

## 2.1 መግቢያ

በግብርናው ዘርፍ በኩል የታወቁ ችግሮች በርካታ ናቸው፡፡ በተለይም በፍጥነት እያደገ ከሚሄደው የሕዝብ ብዛት ጋር የተያያዘው የነፍስ-ወከፍ የእርሻ መሬት መጠን ማነስ ዋነኛ ችግር ነው፡፡ አብዛኛው የገጠር ነዋሪ የሥራ መስክ በመክፈት ካለበት የተጎሳቆለ ኑሮ ለመላቀቅ የሚያስፈልገውን ገቢ ለማግኜት የሚያስችለውን ሁኔታ ለመፍጠር አልተቻለም፡፡ የእርሻ ምርትና ከእርሱም ጋር ተያይዞ የሚገኘው የገጠሩ ነዋሪ ገቢ ከፍ እንዲል ከተፈለገ በሕዝብ ብዛት ምክኒያት የተጨናነቀው የገጠሩ ሁኔታ መተንፈሻ ሊበጅለት ይገባል፡፡

እርሻ-ነክ ያልሆነው የኢኮኖሚ ዘርፍ በተለይም የኢንዱስትሪው ዘርፍ በፍጥነት ማደግና መስፋፋት አለበት፡፡ ይህ ደግሞ መደረግ ያለበት በከተማ ላለው ሥራ-አጥ የሰው ኃይል የሥራ መስክ ለመክፈት ብቻ ሳይሆን ከገጠር ወደከተማ እየፈለሰ ወይም እየተሰደደ የሚመጣውን የሰው ኃይል እንዳመጣጡ ለማስተናገድ አስፈላጊ ስለሆነ ነው፡፡ በሌላ አባባል የግብርናው ዘርፍ ችግሮች ሊቃለሉ የሚችሉት የኢንዱስትሪ መስፋፋትንም አብሮ ለማከናወን እስከተቻለ ድረስ ብቻ ነው፡፡ ይህ ከተሳካ ገበሬዎች ከግብርና ውጭ ባሉ ሌሎች ሥራዎች ላይ ተሠማርተው ተጨማሪ ገቢ ማግኜት ይችላሉ፡፡

በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪው ዘርፍ መስፋፋት ያለበት ከላይ የተጠቀሰው ምክንያት ብቻ አይደለም። የሌሎች አገሮች ልምድ እንደሚመሰክረው የኢንዱስትሪው መስክ በሆነ መንገድ እንዲያድግ ባልተደረገበት ሁኔታ የተሟላ እድገት ሊኖር አይችልም። ይልቁንም አሁን ባለንበት ዘመን የኢኮኖሚ እድገት ሲነሳ የኢንዱስትሪ መስፋፋት ማለት ሆኗል። ስለሆነም ዛሬ ብዙ ዜጎችን እያዳሸቀ ያለውን ድህነት ለመቀነስ፣ ሥራ አጥተው ለሚባክኑ ወጣቶች የሞት የሽረት ጉዳይ የሆነውን የሥራ መስክ ለመክፈት፣ የሠራተኛውን የገቢ መጠን ከፍ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይህንንም ዘላቂነት እንዲኖረው ማድረግ ካስፈለገ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ አሁን ካለበት ደረጃ በላቀ ሁኔታ ከማሳደግና ከማስፋፋት ሌላ የተለየ ምርጫ የለም።

ዘመናዊ ኢንዱስትሪ ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ውስጥ መብቀል የጀመረው በ19ኛው ምዕተ-ዓመት መጨረሻ ገደማ ነው። የኢትዮ-ጅቡቲ የባቡር መስመር መዘርጋቱ ለዘርፉ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። በተጨማሪም ከአርመን፣ ከጣሊያንና ከሕንድ እየመጡ በኢትዮጵያ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ግለሰቦች ለንግድ ሥራ የነበራቸው ዝንባሌና ችሎታ ለዘርፉ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በኋላም የኢትዮጵያ መንግሥት ከአሜሪካና ከእንግሊዝ መንግሥታት ጋር የመሠረተው የቅርብ ግንኙነት ለኢንዱስትሪው ዘርፍ አንፃራዊ እድገት ከፍተኛ ድርሻ አለው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የፋብሪካው ዘርፍ ብቻ ለጠቅላላው የአገሪቱ ምርት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በዓለም ውስጥ እጅግ ዝቅተኛ ከሚባለው ደረጃ ላይ ነው። ለምሳሌ ከጠቅላላው የዓመት ምርት ውስጥ የፋብሪካው ዘርፍ አስተዋጽኦ በግብፅ 15 በመቶና በኬኒያ 11 በመቶ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ 3 በመቶ ብቻ ነው። በፋብሪካው ዘርፍ እንደሚታየው ሁሉ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ለጠቅላላው የየአገሮቹ ምርት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በግብፅ 30 በመቶና በኬኒያ 20 በመቶ ሲሆን በኢትዮጵያ ደግሞ 12 በመቶ ብቻ ነው።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ ለጠቅላላው ምርት የሚያደርገው አስተዋጽኦ አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ከጊዜ ወደ ጊዜ እየቀነሰ መምጣቱ የበለጠ አሳሳቢ ነው። ከ1975 እስከ 1983 ዓ.ም የነበረው አስተዋጽኦ በአማካይ 12.4 በመቶ ሲሆን ከ1984 አስከ 1992 ዓ.ም በአማካይ 10.8 በመቶ ብቻ ነበር። ይህም ማለት የ1984-92 ጊዜ ከ1975-83 ጊዜ ጋር ሲነፃፀር 13 በመቶ ቀንሷል ማለት ነው።

እአስከ 1988 ዓ.ም የነበሩት ጠቅላላ የኢንዱስትሪ ተቋማት ቁጥር 1.2 ሚሊየን ሲሆን፣ ከእነዚህ ውስጥ ከ10 ሠራተኞች በላይ ቀጥረው በማሠራትና በኤሌክትሪክ ኃይል በሚሠሩ መሣሪያዎች በመጠቀም የሚንቀሳቀሱት 642 ብቻ ናቸው።የ1990 ዓ.ም 10 እና ከ10 ሠራተኞች በላይ ያሏቸው መካከለኛና ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው ፋብሪካዎች የምርት ውጤት ዋጋ 6.3 ቢሊዮን ሲሆን፣ ከጠቅላላው የኢንዱስትሪ ምርት ዋጋ 67.4 በመቶ የሚሆን ድርሻ አለው። ከጠቅላላው ኢንዱስትሪ 76 በመቶ የሚሆኑት የጎጆ (የእደ-ጥበብ) ኢንዱስትሪዎች ናቸው። የግብርናው ዘርፍ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው ገበሬዎች የሚካሄድ እንደሆነው ሁሉ የኢንዱስትሪውም ዘርፍ በብዛት የሚካሄደው እንዲሁ አነስተኛ ይዞታ ባላቸው የጎጆና የእደ ጥበብ ተቋማት ባለንብረቶች ነው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ አብዛኛው በግብርና ላይ የተመሠረተ ስለሆነ፣ አገሪቱ ወደውጭ ከምትልካቸው ሸቀጦች የሚበዙት ከዚሁ ዘርፍ የሚገኙ መሆናቸው አግባብ ያለው ነገር ነው። ሆኖም መጠኑ ይነስ እንጂ፣ የኢንዱስትሪው ዘርፍም ቢሆን አገራችን ለሚያስፈልጋት የውጭ ምንዛሪ ገቢ የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ፣ የቆዳ ውጤቶች፣ የታሸገ ሥጋና፣ ጨርቃጨርቅ፣ ወደውጭ የሚላኩ የፋብሪካ ውጤቶች ናቸው። ነገር ግን በዚህ ከሚመረቱት ሸቀጦች ወደውጭ ገበያ ሊላኩ የሚችሉ ዕቃዎች ቁጥራቸው አነስተኛ፣ መጠናቸው ጥቂት ሲሆን፣ በዓይነትም በከፊል በፋብሪካ የተዘጋጁ የግብርና ውጤቶችን ያቀላቀሉ ናቸው።

የኢትዮጵያ አጠቃላይ ኢኮኖሚ ኋላ ቀር በመሆኑ ወደውጭ የሚላኩ የኢንዱስትሪ ምርቶች በጥቂት ሸቀጦች ተወስነው የቀሩ ናቸው። በዘርፉ የሚመረቱት ሸቀጦች በጥራት በጣም ዝቅተኛ ከመሆናቸው ሌላ ብዛታቸውም አነስተኛ ነው። ስለዚህም ለውጭ ንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን የሚያመርቱ አምራቾች የቀረበላቸውን ዋጋ ዝም ብለው የሚቀበሉና ለዓለም-አቀፉ ገበያ ዋጋ

መዋዠቅም የተጋለጡ ናቸው። የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በሚመለከት ግልጽ የሆነ ሥልት አለመኖሩና የዘርፉ ትኩረት የአገር ውስጥ ሸማቹን ፍላጎት ወደማሟላቱ ያዘነበለ ነው። ወደውጭ የሚላኩ የፋብሪካ ምርቶች የተሳካ ውጤት እንዲያስገኙ ያሉት የኢንዱስትሪ ተቋማት የማምረት ደረጃቸውን ከፍ ለማድረግና በዓለም-አቀፉ ገበያ ላይ ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸውንና አስፈላጊ የሆነውን የቴክኖሎጂ ለውጥ ማድረግ አለባቸው። ትኩረታቸው ለውጭ ንግድ የሚሆኑ ምርቶችን ማዘጋጀት የሆነውን ተቋማት ለማበረታታት የሚበጅ አገር-አቀፍ ሥልት መኖር አለበት። የተቋማቱን ቅልጥፍና ለማሳደግና የምርቶቻቸውን ጥራት ከፍ አድርገው ወደውጭ የሚላኩትን ምርቶች በሚፈለገው መጠን ለማምረት እንዲችሉ ተገቢው እገዛና ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል።

የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ሁኔታ በተመለከተ ዋና ዋና ነጥቦችን በጥቅሉ ማስቀመጥ ይቻላል። የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለአገሪቱ አጠቃላይ ብሔራዊ ምርት ያደረገው አስተዋጽኦ (12 በመቶ) ዝቅተኛ ብቻ ሳይሆን የተጓዘበትን ፈለግ ስንመለከት የማሽቆልቆል አለዚያም ባለበት የመርገጥ አዝማሚያ ሲያሳይ ቆይቷል።የዘርፉ የምርት ዘርፎች አካባቢያዊ ሥርጭት የተዛባ ነው። የፋብሪካ ምርት እንቅስቃሴ በአብዛኛው የሚካሄደው በአዲስ አበባና አካባቢው ነው። የባለቤትነት ይዞታ ስብጥርንም ስንመለከት (በተቋማት ብዛትም ሆነ በምርት ውጤቶች ረገድ) ያልተመጣጠነ ወይም ያልተደላደለ መሆኑን እንረዳለን። የምርት ተቋማትን ፈርጆች ስንመለከት በአብዛኛው የምናየው ምግብ፣ መጠጥ፣ ጨርቃጨርቅና ብረት-ነክ ያልሆኑ ንጥረ-ነገሮችን የሚያመርቱ የጎጆ፣ የእደ-ጥበብና ኢ-መደበኛ ፋብሪካዎችን ነው። የቴክኒክ ለውጥ በዘርፉ የምርት እድገት ላይ ያመጣው ለውጥ ይህን ያህል አይደለም። የምርት ግብዓቶችን ጠቅላላ ምርታማነት በሚመለከትም ዘርፉ ካለፈው ሊማር የቻለ ሆኖ አልተገኘም፣ ያሉትንም የምርት ማመንጫ ንብረቶችንም በቅልጥፍና የመጠቀሙ ችሎታ እያሽቆለቆለ ነው የሄደው። በፋብሪካው ንዑስ-ዘርፍም ሆነ በኢንዱስትሪው ዘርፍና በሌሎች የኢኮኖሚ ዘርፎች መካከል ያለው ግንኙነት ዝቅተኛ ነው።

## 2.2 የኢንዱስትሪው ቴክኖሎጂ ያለበት ሁኔታ

### 2.2.1 ቴክኖሎጂ-ነክ ሁኔታዎች

የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ለራሱ፣ ለግብርናውና ለሌሎችም ክፍላተ ኢኮኖሚ በግብዓትነት የሚያስፈልጉ ጥሬ ዕቃዎችን፣ የመገልገያ መሣሪዎችን፣ የእጅ መሣሪዎችን፣ የመለዋወጫ ዕቃዎችን፣ የማሽነሪ አካሎችን፣ የግንባታ ማቴሪያሎችን በማቅረብ መሠረተ ልማትን በማስፋፋት የተለያዩ ቴክኒካዊ አግልግሎቶችን በመስጠት ረገድ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ አስተዋጽኦ አለው። በተጨማሪም በአገሪቱ የኢኮኖሚ ልማት ውስጥ ሊኖር የሚገባውን ውስጣዊ ትስስርና መደጋገፍ ለማጎልበትና የተመጣጠነም አካባቢዊ ልማት እንዲኖር ለማድረግ የኢንዱስትሪው አስተዋጽኦ ወሳኝነት አለው።

ይህንንም እውን ለማድረግ ተስማሚ የሆኑ ቴክኖሎጂዎችን ማፍለቅ፣ እየመረጡ ማስገባት፣ አስቀድሞ የገቡትንና የሚገቡትንም ቴክኖሎጂዎች ለመጠቀም አቅምን መገንባት ያስፈልጋል። ይህ መገንባት ያለበት አቅም የሚያካትተው በመስኩ ወሳኝ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት፣ የምህንድስና ዲዛይንና የማማከር አገልግሎት ቴክኖሎጂን አሻሽሎ ማበጀት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ የሰው ኃይል ሥልጠና ልማት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ አሰባሰብ፣ አደረጃጀትና አሰረጫጨት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ አቅርቦት፣ እንደ አስፈላጊነቱ በብቃት መገኘት ነው።

የኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ ለአንድ አገር አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት እንቅስቃሴ ስኬታማነት የሚያደርገው አስተዋፅኦ ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል። የአንድን አገር የማኅበራዊ፣ የኢኮኖሚና የቴክኖሎጂ ልማት ደረጃ ከሚጠቁሙት ዋነኛ መሥፈርቶች አንዱ የዚህ ክፍለ ኢኮኖሚ የእድገት ደረጃ ከፍተኛነት ነው። ከዚህ አኳያ ሲታይ በአሁኑ ወቅት የኢንዱስትሪው የዕድገት ደረጃ ከሌሎች ታዳጊ አገሮች ጋር እንኳን ሲነፃፀር አነስተኛ ሆኖ ይገኛል።

የኢንዱስትሪው ዘርፍ በአሁኑ ወቅት እንደሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚና አገልግሎቶች ሁሉ ጉልህ የሆኑ ችግሮች ይታዩበታል። በአጠቃላይ ሁኔታ ሲታይ ቴክኖሎጂን ከውጭ አገር በማስገባት የምርትና የአገልግሎት እንቅስቃሴን የማካሄድና ጊዜያዊ የቴክኒክ ችግሮችን የመቅረፍ አዝማሚያ

እንጂ ተስማሚ ቴክኖሎጂ በአገር ውስጥ የማመንጨት፣ የማዳበርና የመጠቀም እንዲሁም ተስማሚ ቴክኖሎጂን የማሸጋገርና የማልማት፣ እንደዚሁም ለቀጣዩ ኢንዱስትሪያዊ ልማት አስተማማኝ የሆነ የቴክኖሎጂ መሠረት ገና አልተገነባም።

አሁን ያለው የፋብሪካ ኢንዱስትሪ የእድገት ደረጃ የሚያመለክተው በአብዛኛው በቀጥታ ለፍጆታ የሚሆኑ ዕቃዎችን አምራች፣ ከሌሎች ክፍላተ ኢኮኖሚ ጋር ያለው መደጋገፍ ያልዳበረ፣ የአገር ውስጥ አቅርቦትን በሰፊው የማይጠቀምና ለኢንዱስትሪውም ሆነ ለሌሎች የኢኮኖሚ ክፍሎች እድገት የሚያገለግሉ የማምረቻ መሣሪያዎችን በማምረት በኩል የሚጫወተው ሚና አናሳ መሆኑን ነው። የእደ ጥበባት ልማትንም ለማፋጠን የሚውሉ ግብዓቶችንና የምርት መሣሪያዎችን ለማሻሻልና ለመጠቀም የሚደረገው እንቅስቃሴ በዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው።

በትራንስፖርትና መገናኛ ኢንዱስትሪ መስክም ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን በአግባቡ ለማሸጋገርና ለመጠቀም የሚደረጉ ጥረቶች በአነስተኛ ደረጃ ላይ ይገኛሉ። የትራንስፖርትና መገናኛ ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች መፈብረኪያና መገጣጠሚያ ተቋሞችም አቅም ውሱን ሆኖ ይገኛል።

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ሁኔታ ሲታይ በኮንስትራክሽን ማቴሪያል ላይ ከሚደረግ አነስተኛ ምርምር ሌላ ጎልቶ የሚታይ እንቅስቃሴ የለም። በአጠቃላይ የዚህ ክፍል ዋና ዋና የሳይንስና ቴክኖሎጂ ችግሮች የምርምርና ሥርፀት አቅም አናሳነት፣ የመረጃ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና አሠረጫጨት ሥርዓት ምቹ አለመሆን፣ የከፍተኛ ግንባታ ፕሮጀክቶች ዲዛይንና የሥራ ክትትል አቅም ዝቅተኛ መሆን፣ ለአገር-በቀልና ባሕላዊ የኮንስትራክሽን ቴክኖሎጂ መሻሻልና ዕድገት ተገቢው ትኩረት አለመሰጠት እና በአብዛኛው በሰው ኃይል የመጠቀም የኮንስትራክሽን ዘዴዎች ዕድገት ዝቅተኛነት፣ ጥራት ያላቸው የእጅ መሣሪያዎችን በአገር ውስጥ ለማምረት አለመቻሉ፣ የዲዛይን ስታንዳርድ ኮድ በተጠናከረ መልክ አለመኖር ናቸው።

## 2.2.2 ቴክኖሎጂ-ነክ ችግሮች

ለዘርፉ እድገት ስለሚያስፈልገው ተገቢ ቴክኖሎጂ በቂ እውቀትና መረጃ አለመኖሩ አሁን ላሉት የምርት ተቋማትም ሆነ ወደፊት በዘርፉ እንቅስቃሴ ውስጥ ኢንቬስት ለማድረግ ለሚፈልጉ ባለሀብቶች እንቅፋት ነው። በብዙ ሁኔታዎች የምርት ተቋማት የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተስማሚነት ለማወቅ ኢንፎርሜሽን ፍለጋ የሚሄዱት ኢ-መደበኛ ወደሆኑ ምንጮች ነው። የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ለመሸመት የሚደረገው ውሳኔ ተጨባጭ መረጃዎችን መሠረት አድርጎ አይደለም። ቴክኖሎጂዎች ሲመረጡ ተቋማቱ ከሚጠቀሙባቸው ጥሬ ዕቃዎች፣ ከሠራተኞች ክሂልና ከሌሎች የአገር ውስጥ ሁኔታዎች ጋር የሚጣጣም መሆን አለመሆኑን በሚያረጋግጥ ጥናት ላይ ተመሥርቶ አይደለም። በብዙ ሁኔታዎች የምርት ተቋማት የሚያደርጉት በሌሎች ሥፍራዎች በተመሳሳይ እንቅስቃሴ የተሠማሩ ተቋማት የሚጠቀሙባቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች እንደተገኙ በመግዛት ነው።

ለቴክኖሎጂ የሚያስፈልገው የቴክኒክ ድጋፍ አለመኖር ከአገሪቱ ጠቅላላ የልማት ደረጃ ዝቅተኛ ነትና ከኢንዱስትሪ ተቋማት ብዛት ማነስ ጋር የተያያዘ ነው። ይህ ሁኔታ፣ አገራችን አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብላ የራሷ ለማድረግ የሚያስችላት ብቃት ዝቅተኛ መሆኑንም ይጠቁማል። አሁን ያሉት የኢንዱስትሪ ተቋማት ብዛት ውሱን በመሆናቸው የውጭ ቴክኖሎጂ ባለቤቶች አስፈላጊውን የማሻሻያ አገልግሎቶች እንዳያደርጉ ጥረቱ ትርፍ የለሽ ስለሚሆን ፍላጎት አያሳዩም። እነዚህ የቴክኖሎጂ ውጤት አቀራቢዎች ለሌሎች ትላልቅ ገበያዎች የሚያቀርቡትን አገልግሎት እዚህም እንዳያቀርቡ የአገራችን የገበያ መጠንና አቅም አነስተኛ ነው። የቴክኒክ ሙያ እውቀት በወጉ ስላልዳበረ ለኢንዱስትሪ ተቋማት የሚያስፈልገውን የድጋፍ አገልግሎት ከዚሁ ለማቅረብ አልተቻለም። ይህ ዕውቀት በአገር ውስጥ ከሌለ ወይም ካልዳበረ ደግሞ ከውጭ የሚገቡትንም የቴክኖሎጂ ውጤቶች ፍሬያማ በሆነ መንገድ መጠቀምም አይቻልም። የምርት ተቋማቱ ራሳቸውም ቢሆኑ የቴክኖሎጂ ዕውቀትን ለመሸመት የሚያደርጉት ጥረት ውሱን ነው። ይህ በቴክኖሎጂ ረገድ ያለው ችግር አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ያሉትን የምርት ተቋማት ቅልጥፍና በእጅጉ ከመቀነሱ ሌላ ወደፊት በሚከፈቱት ተቋማትም ላይ ቢሆን ውጤቱ ከዚህ የተለየ አይሆንም።

## 2.3 ለዘርፉ እድገት እንቅፋት የሆኑ ተጨማሪ ምክኒያቶች

የኢንዱስትሪውን ዘርፍ እድገትና እንቅስቃሴ የገቱና እርስ በርሳቸው የተቆራኙ አያሌ ምክኒያቶች አሉ:: ከእነዚህ ምክኒያቶች እንዳንዶቹ ከዘርፉ ጠባይና ውስጣዊ አወቃቀር ጋር የተያያዙ ሲሆኑ ሌሎች ደግሞ በዘርፉ ላይ ከራሱ ከዘርፉ ውጭ ከሚፈጠሩ ችግሮች ጋር የተያያዙ ናቸው:: እነዚህም እንቅፋቶች ከቴክኖሎጂ-ነክ ችግሮች በተጨማሪ የገበያ ሁኔታ፣ የገንዘብ ይዞታ፣ የመሬት ይዞታ፣ የምርት ግብዓቶች አቅርቦት፣ የሰው ኃይል ችግርና አጠቃላዩ የፖለቲካ ሁኔታ ናቸው::

### 2.3.1 የገበያ ሁኔታ

አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ የነፍስ-ወከፍ ገቢ ደረጃ ዝቅተኛ በመሆኑ ከጠቅላላው ሕዝብ ብዛት ጋር ሲነፃፀር የኢንዱስትሪ ምርቶች ተፈላጊነት እጅግ አነስተኛ ነው:: በተጨማሪም አሁን ያሉት አብዛኛዎቹ የምርት ተቋማት እንቅስቃሴ የታለመው ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን በመተካት ላይ ነው:: ስለሆነም የሚያመርቷቸው ሸቀጦች በገበያ ላይ ሊገኙ የሚችሉ በመሆናቸው ተቋማቱ የግድ ከውጭ ከሚገቡት ሸቀጦች ጋር መወዳደር አለባቸው:: በቅርቡ የውጭ ንግድን ደንቦች ላላ ለማድረግ የወጣው ሕግና በብዙዎቹ ገቢ ሸቀጦች ላይ ከፍ ያለ የማስገቢያ ቀረጥ (ታሪፍ) ቅነሣ ተደርጓል:: በዚህም ምክኒያት የአገር ውስጥ የምርት ተቋማት የሚያመርቷቸው ሸቀጦች ከውጭ ከሚገቡት ርካሽ ሸቀጦች ጋር ሊወዳደሩ አልቻሉም:: ስለዚህም የአገር ውስጥ አምራቾች በዚህ ሁኔታ ከውጭ ከሚያስመጡት ነጋዴዎች መወዳደሩ ፍትሕ የጎደለው ነው ብለው ያምናሉ::

የአገራችን አምራቾች የንግድ ራዕይ ውሱን ነው:: በመሆኑም ካለውና ከሚታወቀው የንግድ እንቅስቃሴ ውጭ አርቆ ለማየት ይሳናቸዋል:: ይህም ኪሣራን ለማምለጥ በሚደረገው ጥረት የተነሣ በአንድ ዓይነት የኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ የመረባረቡ አዝማሚያ ሁኔታውን አባብሶታል:: ስለውጭ ገበያ በቂ ኢንፎርሜሽን አለመኖሩ፣ እንደአውሮፓ ማኅበር ባሉ ለውጭ ምንዛሪ ምንጭ ሊሆኑ በሚችሉ ኃይሎች ዘንድ የሚታየው ተከላካይነትና የአገራችን የኢንዱስትሪ ውጤት የጥራት ዝቅተኛነት ለውጭ ንግድ የሚሆኑ ሸቀጦችን ወደማምረት እንዳናተኩር ከፍተኛ ችግር ይፈጥራሉ:: ከዚህ በተጨማሪም በአገራችን ውስጥ የሚመረቱ የፋብሪካ ውጤቶች ከውጭ ከሚገቡት ጋር ተመጣጣኝ፣ አንዳንዴም የተሻሉ ሆነው በሚገኙበት ሁኔታ እንኳን የሸማቹ ምርጫ ወደውጪው ማድላቱ በተጨባጭ የሚታይ ችግር ነው::

### 2.3.2 የብድር ገንዘብ ሁኔታ

ብድር ፍለጋ የሚሄዱ ኢንቬስተሮች የሚጠየቁት የዋስትና ወይም የመያዣ ተመን ከፍተኛ መሆኑ የሚያሳየው በኢኮኖሚ መደበኛ የገንዘብ ልውውጥ ዘርፍ ያሉት አበዳሪዎች ያላቸውን የሞኖፖል ይዞታ ነው:: ለኢንዱስትሪ ተቋማት ብድር ፍለጋ የሚሄዱት በግሉ ዘርፍ የተሠማሩ ባለሀብቶች ከፍተኛ የዋስትና ወይም የመያዣ ተመን ይጠየቃሉ:: እስከ ቅርብ ጊዜ ያለምንም ተቀናቃኝ ሲሠሩ የቆዩት ባንኮች በተበዳሪዎች ላይ ያላቸው አመለካከት ብትፈልጉ ተቀበሉት ባትፈልጉ ተውት ዓይነት ነበር:: በሌላ በኩል ደግሞ አሁን ያለው የመሬት ይዞታ ፖሊሲ የምርት ተቋማቱ የተመሠረቱበትን ቦታ በወለድ-አግድ እንዲያሲዙ የሚፈቅድላቸው አይደለም:: በፋብሪካው ዘርፍ የተሠማሩ ባለሀብቶች በሊዝ ለገዙት ቦታ በቅድሚያ የከፈሉትን ቀብድ በወለድ-አግድ እንዲያሲዙ የሚፈቅድ ሥርዓት በቅርቡ የወጣ ቢሆንም ገና ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ አልዋለም:: ባንኮች በወለድ-አግድ መያዣነት የሚቀበሏቸው የንብረት ዓይነቶች ተበዳሪው የባለቤትነት ፈቃድ ሊያቀርብ የሚችልባቸው ብቻ መሆናቸው ሌላው እንቅፋት ነው:: እንዲህ ያሉት አሠራሮች ተበዳሪው በእጁ ያሉትን ዋጋ የሚያወጡ ንብረቶቹን በመያዣነት እንዳያቀርብ ያግዱታል:: ጥሩ የንግድ ዕውቀት እያላቸው ግን በወለድ አግድ ሊያሲዙ የሚችሉት ንብረት ለሌላቸውና ወደ ንግዱ ዘርፍ፣ በተለይም ወደ ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለመግባት ለሚፈልጉ ጀማሪዎች በሩን ይህ ችግር ዘግቶባቸዋል::

### 2.3.3 የመሬት ይዞታ

በንግዱ ዘርፍ የተሠማሩ ሰዎች ብዙውን ጊዜ አቤቱታቸውን የሚያሰሙበት ዋናው ፖሊሲ-ነክ ችግር የመሬት ይዞታን የሚመለከተው ነው:: የሊዝ ሥርዓት ከወጣ በኋላ ለኢንቬስትመንት የሚሆን ቦታ ማግኜት አስቸጋሪና ውጣ-ውረድ የበዛበት ብቻ ሳይሆን በጣም ብዙ ወጪ የሚጠይቅ ነው:: ይህ ችግር በፖሊሲም ሆነ በሥራ በመተርጎም ደረጃ ሊያተኩርባቸው ከሚገቡት ከፍተኛ ጉዳዮች አንዱ ነው::

*የመሬት ሊዝ ዋጋ ውድነት አሁን በመንቀሳቀስ ላይ ያሉ የምርት ተቋማት እንዳይስፋፉ እንቅፋት ከመሆኑም በላይ ወደፊትም በዘርፉ ለመሠማራት ለሚፈልጉ ባለሀብቶች በሩን ዘግቶባቸዋል:: ይህ ሁኔታ ደግሞ፣ የገበያው ሁኔታ ሰከን እስኪልና ተጫራቾችም ራሳቸው የመሬትን ዋጋ በመገመትና በማስገመት ረገድ ተጨባጩን ሁኔታ አጢነው የሚያዋጣና የማያዋጣውን መለየትን እስኪማሩ ድረስ ሊቀጥል ይችላል::*

## 2.3.4 ከውጭ የሚገቡ የምርት ግብዓት ቀረጥ

*የጉምሩክ ቀረጥና የታሪፍ ጉዳይም ብዙ ችግር ያለበት ነው:: ከውጭ ለሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች የማስገቢያ ቀረጥ ከነዚሁ ጥሬ ዕቃዎች ተመርተው ወደ አገር ውስጥ ለሚገቡት ያለቀላቸው ሸቀጦች ከሚከፈለው ቀረጥ ብዙውን ጊዜ ከፍ ያለ ነው:: በዚህ ሁኔታ ከፍተኛ ቀረጥ ተከፍሎባቸው ወደ አገር በሚገቡት የምርት ግብዓቶች በመጠቀም የሚመረቱት ሸቀጦች አልቆላቸው ከውጭ ከሚገቡት ሸቀጦች ጋር እኩል ለመወዳደር አቅም የላቸውም:: ያልተደላደለና በዘፈቀደ የሚሠራበት የሺያጭ ቀረጥ ክፍያ ደንብ በንግዱ ዘርፍ የተሠማሩ ሰዎች አጥብቀው ከሚያማርሩባቸው ችግሮች አንዱ ነው:: አሁን የተጣለው የ12 በመቶ የቀረጥ ተመን ከሚገባው በላይ ከፍ ያለ ነው የሚል ትችት አለ::*

*በዚህ ረገድ የአገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን በምርት ተቋማት በራሳቸው የተዘጋጁ የገንዘብ (የገቢ መጠን) ዘገባዎች በቀረጥ ማስሊያነት አይቀበልም:: እንዲህ ያለው መተማመን አለመኖር በንግዱ ዘርፍ የተሠማሩ ባለሀብቶችን በሙስና ተግባር እንዲሠማሩ ይገፋፋቸዋል የሚል እምነት አለ:: በአጠቃላይ ሲታይ፣ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ እድገት በሚመለከት ግልፅ የሆነና ለዘለቄታው የሚበጅ የፖሊሲ ዕቅድ አለመኖሩ የዘርፉን የእድገትና የመዳበር ዕድል ክፉኛ ወስኖታል::*

*ከውጭ የሚገቡ የምርት ግብዓቶች ዋጋ መወደድ፣ የአገራችን ብር የውጭ ምንዛሪ ዋጋ ያለማቋረጥ ዝቅ ማለቱ ያስከተለው ችግር ሊሆን ይችላል:: በሌላ አንፃር ግን፣ ለግምሩክ የሚከፈለው ቀረጥና ከውጭ በሚገቡ ሸቀጦች ላይ የተጣለው ከፍተኛ ታሪፍ ሌላው ምክኒያት ሊሆን ይችላል:: የአገር ውስጥ የምርት ግብዓት ምንጮች አስተማማኝ አለመሆናቸውና በጥራትም ዝቅ ያሉ መሆናቸው የአገር ውስጥ አምራቾች ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ ገበያ ልከው ለመሸጥ ለሚያደርጉት ጥረት ማነቆ ሆኖባቸዋል::*

## 2.3.5 የሰው ኃይል

*ችሎታና ብቃት ያለው የሠራተኛ ኃይል ማነስ ወይም አለመኖር ለአገራችን የኢንዱስትሪ ተቋማት ከፍተኛ ችግር ነው:: ለምሳሌ ከተግባረዕድ የሚመረቁ ተማሪዎች ወዲያው እንደተመረቁ ቴክኒክ-ነክ ሥራዎችን ለማካሄድ የሚያስችል በቂ ሥልጠና የላቸውም:: የዚህ ምክኒያቱ ለነዚህ ትምህርት ቤቶች የተቀረፀው ሥርዓተ-ትምህርት ለተማሪዎቹ በቂ ተግባር-ተኮር ሥልጠና ስለማይሰጣቸው ነው:: በተጨማሪም፣ በዘርፉ የተሠማራው አብዛኛው የሰው ኃይል የመነጨበት የሥራ መደብ ግብርና መሆኑና በዘመናዊ ሥልት የሚመራው የኢንዱስትሪ ዘርፍ ለሚጠይቀው ሥነ-ሥርዓትና የሥራ ሥነ-ምግባር እንግዳ መሆኑ የራሱን ተፅዕኖ እንደሚያደርግ መዘንጋት የለበትም:: ብዙውን ጊዜ የፋብሪካ ሠራተኞች የሥራ ችሎታና ክሂላቸውን የሚያካብቱት በለማጅነት ወይም በረዳትነት እየተሠማሩ ነው:: ይህም ማለት፣ ሠራተኞቹ በተለይ ከተወሰነላቸው ነጠላ የሥራ ድርሻ አልፈው በሠፊው እንዲማሩትና ሥራውም የግል የአእምሮና የስነ-ልቦና እድገታቸውን በማዳበር በኩል ያለውን ዋጋ እንዲገነዘቡ የሚያስችላቸውና ከሥራው ሥነ-ሥርዓት ጋር የሚያስተዋውቃቸው የመደበኛ ሥልጠና ጥብቅ አመራር ይጎላቸዋል ማለት ነው::*

## 2.3.6 ማኅበረ-ፖለቲካዊ ምክንያቶች

*አሁን ያለው በጎሣ/ብሔረሰብ ፈርጅ የተዘረጋው ክልላዊ አስተዳደር መዋቅር የካፒታልና የኢንቬስትመንት ክሂሎችን ከክልል ወደክልል በነፃ ማሸጋገርን የሚያበረታታ አይደለም:: ክልላዊ አስተዳደሮች የራሳቸውን ፖሊሲዎች እንዲያዋቅሩ ሰፋ ያለ ሥልጣን በተሰጠበት የፖለቲካ ሥርዓት ውስጥ በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ልዩነት መኖሩ የሚጠበቅ ቢሆንም ተያይዞ ማደግ የማያስችል አካሄድ ግን ለሁሉም አይበጅም::*

ከዚህ በላይ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ችግሮች ከፍተኛ የሆኑትንም ሆነ የእደጥበብ (የጎጆ) ኢንዱስትሪዎችንም ያጋጠሙ ናቸው:: ሁሉም ዓይነት ኢንዱስትሪዎች ሥራቸውን ለመጀመር ሲዘጋጁ ወይም ሥራቸውን ከጀመሩ በኋላ የገጠሟቸው ችግሮች ናቸው::

## 2.4 ግንዛቤ ማግኘት ያለባቸው ጉዳዮች

የኢትዮጵያን አጠቃላይ የኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት ከፍ ለማድረግ ጠንካራና እያደገ የሚሄድ የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያስፈልጋል:: ነገር ግን እስካሁን እንደታየው ከሆነ የኢንዱስትሪው ዘርፍ እንደሌሎቹ የኢኮኖሚ ዘርፎች ሁሉ በቡቃያነት ደረጃ ላይ ያለ ነው:: ዘርፉ ለአጠቃላይ ብሔራዊ ምርቱ የሚያደርገው አስተዋጽኦ ብቻ ሳይሆን የምርታማነቱም መጠን እያሽቆለቆለ ነው:: ይህም በፈንታው በገበያው ዘርፍ ያለውን ተወዳዳሪነት ብቃት ዝቅ እያደረገው ነው:: ዘርፉ መልክ ያለው፣ በሥርዓት የተቀናጀና ጠቀም ያለ የመንግሥት እርዳታና ድጋፍ የግድ ያስፈልገዋል:: ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመፍታት በዘርፉ የተለያዩ ገጽታዎች ላይ ያተኮረ ሠፊ እንቅስቃሴ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: በሥራ ላይ ለማዋልም እንዲቻል በዘርፉ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ የሆኑትን ወገኖች (መንግሥትን፣ የግል ዘርፍ ባለቤቶችንና ሠራተኞችን) የሚያቀናጅ ዘለቄታ ያለው ዕቅድ ማውጣት ያስፈልጋል:: እነዚህ ባለጥቅሞች አንድ ላይ ሆነው በምርት ተቋማት ደረጃ ተቋማቱ ያሉባቸውን የውስጥና የውጭ ችግሮች በመመርመር የመፍትሔ እርምጃ መወሰድ አለበት:: በፖሊሲ ደረጃም ችግሮችን ለመፍታት ብቃትና ኃላፊነቱ ያላቸውን ተቋማት መፍጠር ወይም ያሉትን ማጠናከር ይቻላል::

የቴክኖሎጂ «ተዋሽ» በመሆናችን ስለቴክኖሎጂ አጠቃቀም አስፈላጊውን እውቀት ማግኘት ተገቢ ነው:: ጥረቱ መጀመር ያለበትም በአጠቃላይ ስለኢንዱስትሪ ልማት ምንነት ንድፈ-ሃሳባዊ ዕውቀትን በማዳበር ነው:: ቀደም ያለውና ነባር የሆነው አስተሳሰብ ቴክኖሎጂን፣ የሚፈልጉት ሰዎች በፈለጉ ጊዜ አንስተው ባስፈለጋቸው ጊዜ በማንኛውም ሁኔታ ሊጠቀሙበት የሚችሉ አድርጎ ይመለከተው ነበር:: በአሁኑ ጊዜ ግን፣ በተጨባጭ ጥናት ላይ የተመሠረተ ማስረጃ እንደሚያመለክተው ቴክኖሎጂ የተለየ ባሕሪይና መልክ አለው:: አሁን ባለው አመለካከት መሠረት ቴክኖሎጂ ረቂቅ ነው:: የተገኘውን ዝም ብሎ መገልበጥም ቀላል አይደለም:: የተገኘ ውን ቴክኖሎጂ ለመገልበጥ የሚሞክረው የምርት ተቋም ብዙ ጥረት ማድረግ አለበት:: የማምረት ልምድ ወይም ተሞክሮ ደግሞ እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ነው:: ይህ ለአዲስ ጀማሪዎች ያለው እንድምታ ከፍ ያለ ነው:: አንደኛ፣ ምንም እንኳን በፋብሪካ ምርት ተሞክሮ ማካበት ጠቀሜታ ያለው ቢሆንም የቴክኖሎጂ እውቀትና ብቃትን ማካበት ብቻውን በቂ አይደለም:: ሁለተኛ፣ ትምህርት መቅሰም በሁሉም የምርት ተቋማት ያለ ነገር አይደለም:: ሦስተኛ፣ የቴክኖሎጂ ለውጥ፣ በምጣኔውም በአቅጣጫውም ቀጥ ብሎ የሚጓዝ ሳይሆን ተለዋዋጭ ነው:: እነዚህ ግኝቶች የኢትዮጵያ ሁኔታዎች ሲጠኑ ከተደረሰባቸው መደምደሚያዎች ጋር ይጣጣማሉ::

ከኢንዱስትሪ ጋር ዘግየት ብለው በተዋወቁት በአብዛኛዎቹ አገሮች የነበረው ሁኔታ አሁን በኢትዮጵያ ካለው ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነበር:: በመሆኑም አሁን ያለው ሁኔታ ተስፋ የሚያስቆርጥ አይደለም:: ይህ የሚያመለክተው አስፈላጊ የሆኑት ፖሊሲዎች ተቀርፀው በደንብ በሥራ ላይ እንዲውሉና የምርት ተቋማቱም ሆኑ መንግሥት ለዘርፉ እድገት ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያለባቸው መሆኑን ብቻ ነው:: በአንድ በኩል ተቋማቱ ራሳቸው አስፈላጊውን የቴክኖሎጂ ብቃት መገንባት አለባቸው:: በሌላ በኩል ደግሞ፣ መንግሥት ለአጠቃላይ ኢኮኖሚው እድገት የሚያመቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና በደንብ የተጠና የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ መቀየስ ይኖርበታል:: ይህ ዕቅድ ደግሞ፣ አገሪቱ ያላትን የተሻለ ዕድል በውል መረዳትን፣ ተገቢ የሆኑትን የማበረታቻ ሥርዓቶች ማዘጋጀትና እነዚህን በሥራ ላይ የሚያውሉ ተቋማትን ማዋቀርና ማቀናጀትን ያካትታል::

ትኩረት ሊሰጠው የሚያስፈልገው ጉዳይ የገበያ መውደቅ ብቻ ሳይሆን የምርት ሂደት አወቃቀር ጭምር ነው:: ያለው የምርት ሂደት አወቃቀር ስለሸቀጦች ዋጋ የሚሰጠው ምልክት የተሳሳተ ወይም ከሁኔታዎች ጋር አግባብ የሌለው ብቻ ሳይሆን፣ ከዋጋ ውጣ ውረድ ጋር የተጣጣመ አካሄድ ላይኖረው ይችላል:: በዚህ ሁኔታ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ የመዋቅር ማነቆዎች ባሉበት አገር «ትክክለኛውን ዋጋ ማወቅ» ብቻውን የቴክኖሎጂ ብቃቶችን በማሟላት ረገድ የትም አያደርስም:: ስለዚህም አስፈላጊው የመዋቅር ለውጥ እስኪደረግ ድረስ መንግሥት የአገር ውስጥ ምርትን

ከውጭ ፉክክር ለመከላከል ወይም የምርቱን ሂደት ለማዳበር በሚያስችል መንገድ ጣልቃ መግባት ይኖርበታል። ነገር ግን ደግሞ ለማያዋጡ የምርት ተቋማት ወይም ዘርፎች ድጋፍ በማድረግ ከስህተት ላይ እንዳይደረስ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

በተጨማሪም ምንም እንኳን የቴክኖሎጂ ብቃትን ለመሸመት አገር-ተኮር ፖሊሲዎች ቢያስፈልጉም፣ በአገር-ተኮርና በውጭ-ተኮር የፖሊሲ ቅኝት መካከል የሚደረገው ልዩነት ተገቢነት የለውም። በመጀመሪያ ሁለቱ ቅኚቶች አንዱ ሌላውን የሚያገል ወይም የሚጋፋ ሳይሆን ተደጋጋፊ ናቸው። ሁለተኛ፣ ሁለቱም ደረጃ በደረጃ በጥቅም ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ የአገሪቱ ኢኮኖሚ የገበያ ዋጋ ውጣ-ውረድን በሚመጥን መልክ እስኪያድግ ቅኝቱ አገር-ተኮር ሊሆን ይችላል፤ ወይም ደግሞ ሁለቱም በአንድ ጊዜ በሥራ ላይ ሊውሉ ይችላሉ። ሥር ለሰደዱ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ቅኚቱ ውጭ-ተኮር፣ ገና በመዳህ ላይ ላሉ ዘርፎች ደግሞ አገር-ተኮር ሊሆን ይችላል። ይህን ሥልት በሚመለከት በጥናት ላይ የተመሠረቱ ተጨባጭ መረጃዎች አሉ። የኢኮኖሚያቸውን የኢንዱስትሪ ዘርፍ ልማት በቅርቡ የጀመሩ አገሮች ሁሉ፣ የዘርፉን የምርት ሂደት ውጭ-ተኮር (ምርቶችን ወደ ውጭ መላክ) ከማድረጋቸው በፊት፣ በዘርፉ ያሉ ተቋሞቻቸው ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን ለመተካት እንዲችሉ አድርገው ቃኝተዋቸዋል። በዚህ መሠረት፣ ቁም ነገሩ በአገር-ተኮርና በውጭ-ተኮር ቅኚቶች መካከል ልዩነት መደረጉ አይደለም። ምክኒያቱም ሁለቱም የተፋጠነ የቴክኖሎጂ ብቃትን ለማካበትና በቴክኒክ ረገድ እድገት ለማምጣት አስፈላጊ ስለሆኑ ነው። በአንድ በኩል ከውጭ የሚገቡ ሸቀጦችን አገር ውስጥ በሚመረቱ ሸቀጦች ለመተካት የተራዘመ ዕቅድ መዘርጋቱ ጥሩ ውጤት ወደሚያመጣ ውጭ-ተኮር ወደሆነ ዕቃ ወደውጭ ወደመላክ ቅኚት ለመረማመድ ይረዳል ብቻ ሳይሆን አስፈላጊም ነው። በሌላ በኩል ከውጭ ገበያ ጋር ለሚደረግ ውድድር በሩን መክፈት፣ የአገር ውስጥ የምርት ቅልጥፍናን ለማፋጠን አስፈላጊ ነው። ወደ ውጭ በሚላኩ ሸቀጦች ላይ ያተኮረ የምርት ሂደትን ማዳበርም ሆነ ወደ አገር ለሚገቡ ሸቀጦች ገበያውን ለቀቅ ማድረግ ለምርት አስፈላጊ የሆነውን የቴክኒክ ብቃት ለማራመድ ይበጃል። ዋናው ቁም ነገር ግልጽ የሆነ የምርት ዕቅድ በመከተል ሁለቱንም ቅኚቶች በጥምረት መጠቀም ነው።

ከዚህም ሌላ በቁም ነገር መጤን ያለበት ጉዳይ የአገር ውስጥ ምርትን ከውጭ ፉክክር ለመከላከልም ሆነ በዓለም ገበያ ለማስተዋወቅ የሚቀየሰው ፖሊሲ የሚቆይበት ጊዜ ነው። ፖሊሲው በሥራ ላይ የሚውልበት ጊዜ ለሁሉም የኢንዱስትሪ ዘርፎች እኩል የሚሠራ መሆኑ ወይም እንደየኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚለያይ መሆኑ ተለይቶ መታወቅ አለበት። በዚህ ረገድ ልዩነት የሚደረግ ከሆነ፣ በተለይ የትኞቹ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ቅድሚያ ሊሰጣቸው እንደሚገባ መታወቅም አለበት።

የኢንዱስትሪ ተግባራት በቴክኖሎጂ፣ በአወቃቀርና በድርጅትና ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት አንፃር የተለያዩ ባሕሪያት ይኖሯቸዋል። በዚህም የተነሣ በክንውን መስካቸው ትምህርት ለመቅሰም የሚወስዱት የጊዜ መጠን ሊለያይ ይችላል። ስለዚህም ከውጭ ፉክክር የመከላከሉም ሆነ የአገር ውስጥ ምርትን ለውጭ ገበያ የማስተዋወቁ ፖሊሲ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ እንደየሁኔታው መለያየት አለበት ማለት ነው። በዚህ ረገድ ምንም እንኳን በግልጽ ተለይተው የተፈረጁ ደንቦች ባይኖሩም ትምህርት የመቅሰም አቅምና ጊዜ ቅድሚያ ሊሰጣቸው የሚገባቸው ዘርፎችና የመከላከሉ ፖሊሲ የሚቆይበትን የጊዜ ገደብ በመምረጥ ረገድ መልካም መጠቆሚያ ሊሆን ይችላል። ገና በማቆጥቆጥ ላይ ላሉ የኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚደረግላቸው ጥበቃ ትርጉም እንዲኖረው ከተፈለገ፣ የበለጠ ጥበቃ በሚደረግላቸው የኢንዱስትሪ ተቋማት ለአንድ ላለቀለት ምርት የሚያስፈልገው የምርት ግብዓት ፈጠን ባለ ምጣኔ እንዲደርስ መደረግ አለበት።

## 2.5 በምርት ተቋማት በኩል መደረግ ያለበት ጥረት

አገራችን የተሻለ ዕድል ያላት መሆኑ በግልጽ ተለይቶ ከታወቀ በኋላ፣ በምርት በኩል ያለውን ቅልጥፍና ተገቢውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሊሟላ ይችላል። የቴክኖሎጂ እውቀትን መቅሰም፣ ልምድን ወይም ተመክሮንና ዕውቀትን ለመሸመት የሚያስፈልገውን ገንዘብ መመደብ ይጠይቃል። እነዚህን ተፈላጊ ነገሮች ያሟሉ ተቋማት የሚያስፈልገው ብቃት ባለቤት ይሆናሉ። ከግል የምርምርና የልማት ካፒታል የሚገኝ ዕውቀት የአገር ዕውቀትን ለመፍጠር የሚያገለግል ነው። የምርት ተቋማት ደግሞ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ እንዲችሉ በዚህ የአገር ዕውቀት ሊጠቀሙ የሚያስችላቸውን የቴክኒክ ችሎታ ለመሸመት በግል ምርምርና ልማት ላይ ኢንቨስት

ማድረግ አለባቸው። የተከማቸውን አገራዊ ዕውቀት ፍሬያማ በሆነ መንገድ መጠቀም ከፍተኛ ወጪ አለበት። ነገር ግን በምርምርና ልማት ላይ ቀደም ሲል ኢንቬስት በማድረግ የቴክኖሎጂ ዕውቀት ላዳበሩ የምርት ተቋማት ወጪው አነስተኛ ነው።

የተሳካ የምርት ሂደት በሦስት የብቃት ማሳደጊያ ፈርጆች ይከናወናል። እነሱም፣ ማምረትን፣ ኢንቬስትመንትንና የቴክኖሎጂ ፈጠራን ይመለከታሉ። የማምረት ብቃትና የምርት ብቃትን ማዳበር ማለትም፣ የምርት ሂደትን መምራት፣ የምርት ክንውኖችን መከታተልና ማሻሻል፣ ኢንፎርሜሽን መሰብሰብና ክንውኖች ከፍተኛ ውጤት የሚያስገኙበትን መንገድና ዘዴ ማስላትን ያካትታል። በተጨማሪም፣ በምርት ሂደት ውስጥ ያሉ ችግሮችን ለመፍታትና ምርታማነትን ለማሳደግ የምርት ሂደቶችንና ውጤቶችን ከጊዜው ሁኔታ ጋር ለማጣጣም አስፈላጊውን ለውጥ ለማድረግና የምርት መሣሪዎችን ለመጠገን እንዲቻል አስፈላጊውን ክትትልና ምርመራ ማድረግን ይጠይቃል። ኢንፎርሜሽን መሰብሰብ ሲባል ጥሬ ዕቃ ስለሚገኝበት መንገድ፣ የምርት ክንውን የጊዜ ሰሌዳ ስለማውጣት፣ የምርትን ጥራት ስለመቆጣጠር የመሳሰሉትን ይመለከታል።

ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጉትን ችሎታዎች ወይም ብቃቶች ለማካበት፣ ከፋብሪካ የምርት ሂደት ሥርዓት አስፈላጊውን ኢንፎርሜሽንና መረጃ አሰባስቦ መተንተንና በቂ ጥናት ማድረግ ተገቢ ነው። ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ከሁኔታዎች ጋር እንዲጣጣሙ አድርጎ መጠቀምና ማሻሻል፣ አንዳንድ የምርት ሂደቶች ለምን ውጤት እንደሚያስገኙ፣ ሌሎች ደግሞ ለምን ውጤት አልባ እንደሚሆኑ መረዳት አስፈላጊ ነው። በመጨረሻም ይህን ሁሉ ያካተተውን ኢንፎርሜሽንና መረጃ በመዝገብ አስፍሮ ማቆየት ያስፈልጋል። ይህን ማድረግ ደግሞ፣ ያላሰለሰና በሥርዓት የተቀናጀ ጥረትን ይጠይቃል። እንዲህ ዓይነቱ ነገር በምርት ግብዓቶች ወይም በምርት ገበያ ላይ በሚመጣ ለውጥ በድንገት ነፍስ ዘርቶ የሚንቀሳቀስ አይሆንም። ሂደቱ በሙሉ አቅም እስኪሠራ እስከ ሃያ ዓመት ድረስ ሊወስድ ይችላል። ስለዚህም የረጅም ጊዜ የታለመ ዕቅድንና ኢንቨስትሜንትን ይጠይቃል።

የኢንቬስትሜንት ብቃት፣ ለዲዛይን የሚያስፈልገውን ቴክኖሎጂ ለይቶ የማወቅን፣ የማዘጋጀትንና በእጅ የማድረግን ክሂሎች፣ የካፒታልን ወጪ፣ የመጠነ-ስፋቱን ተገቢነት ማጤንን ይጠይቃል። በተጨማሪም የኢንቬስትሜንት ብቃት፣ የምርቱን ስብጥርና የምርት ተቋሙ በሚንቀሳቀስበት የቅልጥፍና መጠን ላይ ተፅእኖ የሚኖረውን ቴክኖሎጂና የማምረቻ መሣሪያዎችን መርምሮ የሚወስን የማስፋፊያ ዕቅድ አዋቅሮ ከአስፈላጊው መሣሪያና የሰው ኃይል ጋር የማዘጋጀት ክሂሎችን ያጠቃልላል።

የቴክኖሎጂ ፈጠራ ብቃት ደግሞ፣ ባለው ቴክኖሎጂ ላይ አነስተኛም ይሁኑ ሠፋ ያሉ ለውጦችንና ማሻሻሎችን የማድረግን ክሂሎችን ያጠቃልላል። በዚህ ረገድ ያለውን ብቃት ለማዳበር ደግሞ የመጀመሪያዎቹን ሁለት የብቃት ዓይነቶች ልምድ መቅሰምና ማካበት ያስፈልጋል።

እነዚህ ብቃቶች ተጠቃለው የተቋማቱን ክንውኖች ዓይነት ለማሰባጠርና በተቋማቱ ላይ ተገቢውን ለውጥ ለማምጣት አስፈላጊ ስለሆኑ ማንኛውም የምርት ተቋም እነዚህን ብቃቶች ለማሟላት ለሚደረገው ጥረት ተገቢውን ትኩረትና ክብር ሊሰጥ ይገባዋል። እነዚህን ብቃቶች ማሟላት የማይችል የምርት ተቋም ዓለም አቀፍ ፉክክር ባለበት የዛሬው ዓለም ህልውናውን ጠብቆ ሊኖር አይችልም። እነዚህን ብቃቶች ለማሟላት የሚደረገው ጥረት መጠንና ፍጥነት ኢኮኖሚው ባለበት የልማት ደረጃ፣ በቁሳቁሳዊና በሰብአዊ ካፒታል መጠንና ይዞታ፣ አገሪቱ በቴክኖሎጂ ረገድ በምታደርገው ጥረት፣ ለአምራቾች በሚደረገው ማበረታቻ፣ የዘርፉን እንቅስቃሴ በሚከታተሉ ተቋማት፣ በመንግሥት ፖሊሲዎችና በመሳሰሉት ነገሮች ይዞታ ይወሰናል። እነዚህ ሁሉ ነገሮች የምርት ተቋማቱ የግል ጉዳዮች ሳይሆኑ፣ ተቋማቱ ከሚንቀሳቀሱበት አጠቃላይ ሁኔታ ጋር የተቆራኙ ናቸው።

## 2.6 በመንግሥት በኩል የሚደረጉ ጥረቶች

የምርት ተቋማት ቴክኒካዊ ብቃቶች ሊሟሉ የሚችሉት በዘርፉ በቂ የሙያ ልምድ፣ ጥልቅ ተመክሮዎች፣ አስፈላጊ የሆኑት ማበረታቻዎችና የዘርፉን እንቅስቃሴ የሚከታተሉ በቂ ተቋማት ሲኖሩ ብቻ ነው። መንግሥት እነዚህን ዝግጅቶች በበቂ ማሟላት አለበት።

## 2.6.1 ብቃትን ማዳበር

በዚህ ረገድ የሚያስፈልጉት ብቃቶች ቁሳዊ ኢንቬስትሜንት መክፈትን፣ የሰው ኃይል ማቅረብንና ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት ጥረት ማድረግን ያካትታሉ። እነዚህ ሦስቱ የብቃት ዘርፎች እርስ በርስ በጣም የተቆራኙ በመሆናቸው አንዱን ነጥሎ አስተዋጽኦው ይህ ነው ብሎ ለመለየት ያስቸግራል፤ ነገር ግን ደግሞ ሦስቱም ሁልጊዜ ባንድ ላይ የሚዘልቁበት ሁኔታ የለም። አንደኛው ብቻውን ያለሌሎቹ በቂ ተጽእኖ ሊያደርግ አይችልም፣ ወይም ደግሞ በአንፃሩ የአንደኛው ብቻ መኖር ሌሎቹን ይስባል ወይም እንዲኖሩ ያደርጋል ማለት አይደለም። እርግጥ ቁሳዊ ኢንቨስትመንት በተቀዳሚ መሟላት ያለበት ነገር ነው። አንድ የፋብሪካ ምርት ተቋም ይኖር ዘንድ በተቀዳሚ ፋብሪካውና የፋብሪካው መሣሪያዎች ተሟልተው መቋቋም አለባቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ቁሳዊ ኢንቨስትሜንት እንዳይኖር እንቅፋት የሚሆነው የአገራዊ ኢንቨስትሜንት ብቃት ማነሱ ነው። የግል ዘርፉ የሚያደርገው ተሳትፎ መጠንና በኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ያለው ተሞክሮ በዘርፉ የሚያስፈልገውን የሙያ ብቃት ለማዳበር አስፈላጊ ይሆን ነበር።

የግል ዘርፉን መጠነ ስፋት (የሥምሪቱን ብዛት) ስንመለከት በአገሪቱ ውስጥ በዘርፉ ሙያ ለመሠማራት ባለው ፍላጎት ረገድ ምንም እጥረት የሌለ መስሎ ሊታየን ይችላል። ነገር ግን በተገኘው አጋጣሚ በዘርፉ ገብቶ ትርፍ ለመሰብሰብ ያለ ፍላጎት እንዲሁ በቁመናው ሲታይ ከባህላዊው የእደ ጥበብ ወይም ከጎጆ ኢንዱስትሪው ይበልጥ ሰፋ ያለ መጠንን፣ ረዘም ያለ የዘለቄታ ዕቅድን፣ ከዘመኑ ጋር የተራመደ ቴክኖሎጂንና የተወሳሰበ መዋቅርን የሚጠይቀውን ዘመናዊ ኢንዱስትሪ አዋቅሮና አቁሞ ለማንቀሳቀስ ከሚያስፈልገው የሙያ ብቃት ጋር አንድ አይደለም። እንዲህ ያለው ፍላጎት ትኩረቱ አነስተኛ ኪራይ ከፍሎ ቶሎ ትርፍ በሚያስገኙ የንግድ እንቅስቃሴዎች ላይ ነው። ሌላው ነጥብ ደግሞ የግል ዘርፉ በቁሳዊ ኢንቬስትሜንት ረገድ የታለሙ ዕቅዶችን በሥራ ላይ የማዋሉ ሂደት፣ ከመሬትና ከገንዘብ ጋር፣ ወዲያውም ግን ከመልካም አስተዳደር ማነስ (ማለትም፣ ከውጣ ውረድ መራዘም፣ ከግልፅ አሠራር ማነስና አስቸጋሪ ከሆነና ቅልጥፍና ከጎደለው ቢሮክራሲ መብዛት) ጋር በተያያዙ ምክ ንያቶች የተነሣ የመንቀርፈፍ ጠባይ ይታይበታል።

በመንግሥት በኩል ለግሉ ዘርፍ ልማት የሚያስፈልገውን አመቺ ሁኔታ ከመፍጠር ያለፈ ፈቃደኝነትን፣ በተለይም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ለሚያስፈልገው ሙያዊ ብቃት ማደግ እንቅፋት የሆኑትን ችግሮች ለይቶ ማወቅንና በተመረጡ የኢንዱስትሪ ክንውኖች ውስጥ ገብቶ አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠትን ይጠይቃል። ሌላው አስፈላጊ ጉዳይ መንግሥት በትምህርትና ሥልጠና ላይ ማተኮር ያለበት መሆኑ ነው። የትምህርትና የሥልጠና አስፈላጊነት በተቀዳሚ በዘርፉ ለሚያስፈልገው የሙያ ብቃት መዳበር በሚያደርገው አስተዋጽኦ ላይ የተመሠረተ ነው። ከፍተኛ መደበኛ ትምህርት ያለው ሰው ይህን ዓይነት ትምህርት ካላገኘ ሌላ ሰው ይልቅ ሃሳብ ለመቀበል፣ ለመረዳት፣ ለመማር፣ ለማፍለቅና በተገኙት ሃሳቦች በደንብ ለመጠቀም የተሻለ ዕድል አለው። ብዙ ጥረትና ችሎታን በሚጠይቁ ክንውኖች ዘርፍ መሰለፍ ከፍተኛ ደረጃ ያለውን የቴክኒክ እውቀትና ብቃትን ይጠይቃል።

የትምህርትና ሥልጠና ሥርዓት የቴክኒክን ትምህርት (የሙያ ሥልጠናን) እንዲያጠቃልል ሁኖ መቃኘቱ ለኢትዮጵያ አስፈላጊ ነው። በተቋማት ደረጃ ሥልጠናን መስጠት የግድ አስፈላጊ ሲሆን ሠራተኞችን ለማሰልጠንና አስፈላጊዎቹን ክሂሎች ለመፍጠር በተቋማት ደረጃ የሚደረግ ጥረት በሥራው ውጤት ላይ ልዩነት ሊያመጣ ይችላል። ነገር ግን የፋብሪካ ተቋማት ብዙውን ጊዜ ለሥልጠና የሚያስፈልገውን ወጪ ለመመደብ ፈቃደኞች አይደሉም።

በተቋማት ደረጃ ሠራተኞች ከቦታ ቦታ ከሥምሪት ወደ ሥምሪት በሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ የግል ኢንቨስተሮች ለሠራተኞች ሥልጠና ከሚያስፈልገው ገንዘብ በታች ኢንቨስት ሊያደርጉ የሚችሉበት ሥጋት አለ። የሰው ኃይልን ለማዳበርና ሠራተኞችን ለማሰልጠን የሚያስፈልገው ገንዘብ ጨመር ተደርጎ ኢንቨስት እንዲደረግ የሚያበረታታ እርምጃን መውሰድን ይጠይቃል። ይህ በተቋማቱ በራሳቸው በነጠላም ይሁን በጋራ ሊያደርጉት የሚችሉት ወይም የግል ባለሃብቶች በተደጋጋሚ ከሚገባው በታች ኢንቨስት በሚያደርጉበት ሁኔታ በመንግሥት እርዳታ ሊደረግ የሚችል ነው። በዚህ ረገድ የሚወሰዱት እርምጃዎች የዘርፉን ጠቅላላ የተግባር ሥምሪት

የሚያጠቃልሉ ወይም ደግሞ በምርጫ ላይ ተመሥርተው በማደግ ላይ ባሉ የተወሰኑ ዘርፎች ላይ የሚያተኩሩ መሆን ይችላሉ::

በዚህ ረገድ የሚወሰዱት እርምጃዎች ምን ምን እንደሚሆኑ ምን ጊዜና በምን ያህል መጠን እንደሚወሰዱ የሚወሰነው እንደዘርፉ ወይም እንደተቋማቱ የግል ሁኔታ ነው:: ሆኖም ግን የሰው ኃል እንዲሰለጥንና ኢንቨስትሜንት ቢደረግም፣ ይህ ሁሉ ተግባር ላይ ውሎ የተሳካ ውጤት ሊያመጣ የሚችለው በተቋማት ደረጃ የሚደረገውን ጥረት አቀጣጫ ለማስያዝና ክፍተት በተፈጠረ ቁጥርም ክፍተቱን ለመዝጋት መንግሥት ቴክኖሎጂን ለማስፋፋት ከሚያደርገው ጥረት ጋር የተቆራኘ እንደሆነ ነው::

## 2.6.2 የማበረታቻ ድጋፎች

የማበረታቻ እርምጃዎች በዘርፉ ወይም በተቋማት ውስጥ ያሉ ብቃቶች በምን ያህል ቅልጥፍና በጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይወስናሉ:: እነዚህ ድጋፎች በሚሸመተው የካፒታል ክምችት ምጣኔና በሚቀሰሙት የክሂል ዓይነቶች ላይ፣ እንዲሁም ለዘርፉ ወይም ለተቋማቱ የሚደረጉ የገንዘብም ሆነ የቁሳቁስ ድጋፎች ምርትን ለማሳደግ ከጥቅም ላይ በሚውሉበት መጠን ላይ ተጽእኖ አላቸው:: የማበረታቻ ድጋፎች ወደ ዘርፉ ወይም ወደ ተቋማት እንዲደርሱ የሚደረግበት አንዱ ዘዴ ውድድር ነው:: የምርትም ሆነ የምርት ግብዓቶች ገበያ ውድቀት (ክስረት) እስከሌለ ድረስ ውድድር (የአገር ውስጥም ሆነ የውጭ)፣ የሸቀጥ ዋጋ፣ የምርት ግብዓቶችን እጥረትም ሆነ የሚመረቱት ምርቶችና የሚቀርቡት አገልግሎቶች ያላቸውን ተፈላጊነትና እነሱን ለማቅረብ የሚያስፈልገውን ወጪ መጠን ያንፀባርቃል:: ነገር ግን በጉልበት፣ በሰው ኃይል፣ በካፒታል፣ በገንዘብና በምርት ገበያዎች ረገድ ውድቀት ሊከሰት ይችላል:: በዚህም የተነሳ መንግሥት ወይ የገበያን ውድቀት ለመወጣት ወይም ለዘርፉ በተለይም በማደግ ላይ ላሉ ዘርፎችና ተቋማት የማስተዋወቂያ ድጋፍ በመስጠት ጣልቃ መግባት ይኖርበታል::

የገበያ ይዞታ ሲወድቅና የምርት ተቋማት ከሚገባው በታች ኢንቨስት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ተቋማቱ ገበያውን የራስ (ኢንተርናላይዝ) ማድረግና ውድቀቱን ለመወጣት እንዲችሉ በቀጥታ ገንዘብ በማቅረብ መንግሥት ጣልቃ መግባት ይኖርበታል:: በሌላ አባባል መንግሥት በቀጥታ የውስጥ የገንዘብ ድጋፍ በማድረግ፣ ለሠራተኞች ሥልጠና የሚያስፈልገውን ወጪ በድጎማ በመስጠት፣ ብድር በመስጠት፣ ለምርምርና ልማት ድጎማ በማድረግ፣ በመሳሰሉት አካሄዶች ጣልቃ መግባት ይኖርበታል::

ይህ የመንግሥት ጣልቃ መግባት ዘርፉን በሙሉ ሊያጠቃልል ወይም ተለይተው በተመረጡ የተወሰኑ ዘርፎች ላይ ሊያተኩር ይችላል:: ነገር ግን የምርት ምንጮችና ኃይሎች የተወሰኑ በመሆናቸው የመንግሥት ጣልቃ ገብነት በተመረጡ ዘርፎች ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆን አለበት:: የዚህም ዓላማ፣ ከፍ ያለ ግንኙነትና የውጭ ትኩረት ኖሯቸው ትርፍ ምርት የሚያመነጩ፣ ባለው የተወሰነ የምርት ምንጭና ኃይል አንፃርም የሚያስፈልጉትን ብቃቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊያሟሉ የሚችሉ ዘርፎችን ወይም ተቋማትን ማሳደግና ማራመድ ነው::

## 2.6.3 የኢንዱስትሪዎች ጥበቃ

የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች አስፈላጊው ጥበቃና መንከባከብ ሲደረግላቸው የቴክኖሎጂ ብቃቶች በዚያው ልክ ሊዳብሩ እንደሚችሉ መገንዘብ ይገባል:: ይሁን እንጂ እንደዚህ ዓይነቱ ጥበቃ ወይም እንክብካቤ በቴክኖሎጂ ብቃቶችን ለማዳበር ሁልጊዜም አስፈላጊ ነው ማለት አይደለም:: ወይም ለኢንዱስትሪ ዘርፎች ጥበቃን ማድረግ የተሻሻለ የቴክኖሎጂ ብቃትን ያስከትላል ማለት አይደለም:: ስለዚህም ምንጊዜም ቢሆን የአገር ውስጥ ምርትን ከውጭ ፉክክር ለመጠበቅ ወይም ለዘርፉ ድጎማ ለማድረግ የሚያስፈልገውን ወጪ ለመቆጣጠር፣ የተወሰኑ ዘርፎችን መርጦ በእነሱ ላይ በማተኮርና ወዲያውም ደግሞ እንደየሁኔታው ረገብ ያለ ሥልትን በመከተል በወጪው መጠን ላይ ገደብ ወይም መጠባበቂያ ማኖር ያስፈልጋል:: በዚህ ረገድ የተሻለ አማራጭ የሚባለው የተወሰኑ ዘርፎችን በጊዜያዊነት ከውጭ ፉክክር መጠበቅን ወደውጭ ለሚላኩ ምርቶችና ለአገር ውስጥ ውድድር ከሚሰጡ ጠንካራ የማበረታቻ ድጎማዎች ጋር አቆራኝቶ ባንድነት መሥራት ነው:: የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ዕቅድም በዚህ አቅጣጫ እንዲጓዝ መደረግ አለበት:: ያለሱም ስለልማት ማሰብ አይቻልም:: ግን የአገሪቱን

የኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት በዘለቄታ ለማቆየት ሂደቱ ራሱ ለአገር ውስጥ ጥቅም የሚውሉ ምርቶችን ማመንጨት ብቻ ሳይሆን በዓለም ገበያ የውጭ ምንዛሪ የማግኘት አቅሙንም በአፋጣኝ ማሳደግ መቻል አለበት።

ወግ አጥባቂ የሚባሉ ተመራማሪዎች እንኳን የመንግሥት ጣልቃ መግባት በተመረጡና የፖሊሲው ዒላማ በሆኑ ዘርፎች ላይ ማተኮር እንዳለበት ያምናሉ። አዲስና ውስብስብ የሆኑ የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴዎችን ከፉክክር ለመጠበቅ የሚያስፈልገውን የወጪ መጠንና የጊዜ ገደብ፣ እንዲሁም በተለያዩ የቴክኖሎጂ ዓይነቶች መካከል ያለውንም ልዩነት ስንመለከት፣ ሁሉም ኢንዱስትሪዎች እኩል የሆነ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል ብሎ መከራከር አይቻልም። ከበድ ባለ ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ዘርፎች የበለጠ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። ከሌሎች የእንቅስቃሴ ዘርፎች ጋር ከፍተኛ ግንኙነት ያላቸው ዘርፎች ደግሞ በመማር ሂደት ላይ ያሉትን ተመሳሳይ ዘርፎች ለማጠቃለል የሚያስችል ሰፋ ያለ ጥበቃ ያስፈልጋቸዋል። እንዲሁም ለውጭ ፍጆታ የሚውሉ ምርቶችን የሚያመነጩ የምርት እንቅስቃሴዎች ከሌሎች የበለጠ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ምክኒያቱም የሚገኙትን ጥቅሞች በሙሉ ኢንቬስተሮች ብቻቸውን በግል ሊጠቀልሉ አይችሉም።

ገበያ ለማግኜት የሚደረገው ፉክክር አስፈላጊ፣ ወዲውም ግን በዚህ ረገድ የሚደረገው ፉክክር ሁለት ስለት እንዳለው ሰይፍ ነው። ፉክክር ፈሩን ከለቀቀ ለምርት ሂደት የሚያስፈልገውን ብቃት ለማሟላት የገንዘብ አቅሙ የሌላቸውን የምርት ተቋማት ጨርሶ ሊያጠፋቸው ይችላል። ስለዚህ በኢትዮጵያ በኩል መወሰድ ያለበት የመዋቅር ማስተካከል እርምጃ ከዘርፍ ዘርፍ እየመረጠ በተወሰኑት ላይ የማተኮርን ሥልት የተከተለና ለዚህም ይበጅ ዘንድ በበቂ መረጃዎች የተደገፈ መሆን ይኖርበታል። የሚመረጡት ዘርፎች ከሌሎች ጋር ሲነፃፀሩ የተሻለ የእድገት እርምጃ የሚያሳዩና የምርት ኃይሎችን በማደላደል ረገድ ጥሩ ተሞክሮ ያላቸውና ቢያንስ በኢንዱስትሪው መስፋፋት ላይ ዐቢይ ሚና ይጫወታሉ የሚባሉትን ዘርፎች በሚመለከት መሆን ይኖርበታል።

## 2.6.4 ድጋፍ ሰጪ ተቋማት

ቁሳዊ ኢንቨስትመንት በአፋጣኝ እንዲያድግና የምርት ሂደት ብቃቶች እንዲስፋፉ ለማድረግ የሚያስችሉ ድጋፍ-ሰጪ ተቋማት ኢትዮጵያ ውስጥ በብቃት የሉም። የተወሰኑ ዘርፎችን መርጦ በማዳበር (ለምሳሌ፤ የወለድ ምጣኔን መደጎም፣ ብድር በቀላሉ ለማግኜት ሁኔታዎችን ማመቻቸት) የኢኮኖሚውን አወቃቀር፣ ለሌሎቹ የሚበጅ ትርፍን ወይም ኪሣራን ማመንጨት ወደሚችለው የምርት ዘርፍ ለማሸጋሸግ «በትኩረት የተቃኘ የብድር ሥልት» አስፈላጊ ሆኖ ሳለ፣ ይህ ሥልት ግን በኢትዮጵያ አይሠራበትም። ኢንቬስተሮች ወይም ለብድር ዋስትና የሚሆን መያዣ ስለሌላቸው፣ ወይም ደግሞ የገንዘብ ገበያው ውድቀት ስለደረሰበት፣ ጥሩ የሚባሉ ኢንቨስትሜንተቶች የሚፈልጉትን ገንዘብ ሲነፈጉ፣ መጥፎ የሚባሉ አንዳንድ ኢንቬስትመንቶች ደግሞ የጠየቁትን ያገኛሉ። ልዩ ተቋማትን ፈጥሮ መንቀሳቀስ እንዲህ ባሉት ችግሮች ለተጠመዱ ኢንቬስተሮች የገንዘብ ድጋፍ ለመስጠት ይረዳል። እንዲህ ያሉትን ተቋማት መመሥረቱ፣ የተቋማትን ብቃት ከፍ ለማድረግ የሚረዳ ብቻ ሳይሆን፣ የአገር ውስጥ ፉክክርን በማበረታታት ለተቋማት የሚደረገውን ልዩ ድጋፍ ያሻሽላል።

የምርት ሂደት ብቃትና ኢንዱስትሪን የማበልፀግ ጥረት ገና በማቆጥቆጥ ላይ ባለበት በኢትዮጵያ ውስጥ የኢንዱስትሪ ርስቶችን (ኢስቴትስ) መትከልና ወደውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ማምረቻ አካባቢዎችን ፈጥሮ መከለል፣ በመሠረተ ልማት መዋቅር፣ በኢንፎርሜሽን ሥርጭትና በአገልግሎት በኩል ያሉ እንከኖችን ለማሟላት መንግሥት ጣልቃ ሊገባ የሚችልበት አንዱ መንገድ ነው። ወደውጭ የሚላኩ ሸቀጦችን ማምረቻ አካባቢዎችን መፍጠር፣ ለኢንቬስተሮችና ወደውጭ ለሚላኩ ሸቀጦች ንግድ የሚያመቹ ሕጋዊና የቁጥጥር ደንቦች የሚጠይቁትን ለማሟላት ይረዳል። የኢንዱስትሪ ርስቶችን ማቋቋሙ ደግሞ፣ የኢንቬስተሮችን ወጪ ከመቀነስ ሌላ፣ ያለው ገበያ ሊያቀርብ የማይችላቸውንና አለመኖራቸው ለአምራቾች ትልቅ ማነቆ የሆነውን፣ መሠረታዊ ምርት መዋቅሮችና የኢንዱስትሪ አገልግሎቶች ለማቅረብ ይረዳል። በተጨማሪም እነዚህን ተቋማት መመሥረቱ ብቃትን ለማዳበር ይረዳል። በመጨረሻም እነዚህ ሁሉ ነገሮች ግልፅ ሆኖ በተቀየሰ ዕቅድ ውስጥ መካተት አለባቸው። ይህ ዕቅድ፣ ተቋማትን መገንባትን፣ ተገቢውን የማበረታቻ ድጋፍ መስጠትን፣ ብቃትን ማዳበርንና ንፁሕ፣ ፈጣንና ቀልጣፋ የትግበራ ሥልትን ማካተት አለበት።

## 2.6.5 **ሀገር በቀል ቴክኒዎሎጂንና ውድድርን መደገፍ**

*በአሁኑ የዓለም ኢኮኖሚ ሁኔታ ውስጥ ተሳታፊ ለመሆን በውድድር ሁኔታ ውስጥ ለመስራት የሚያስችል ብቃት መገንባትን ይጠይቃል፡፡ ለውጭ ገቢያ የሚቀርበውን መጠን ብቻ ሳይሆን ጥራቱን የማሳደግ ስራ እስካልተከናወነ ድረስ ተወዳዳሪ መሆን አይታሰብም፡፡ በአሁኑ የዓለም ንግድ ሁኔታ ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል የምርትና የአገልግሎት ጥራት ሳይኖር መጠንን በመጨመር ብቻ ውጤታማ ነገር ለመስራት ከባድ ነው፡፡ ሌላው ተወዳዳሪነትን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መንገድ የአመራረትንና የአገልግሎት አሰጣጥን ብቃት ያለውና በቁጠባ የሚከናወን ማድረግ ነው፡፡ ጉልበት፣ ጊዜና ወጭን በሚቆጥብ ዘዴ የሚሰራ የምርትና የአገልግሎት ተግባር ማካሄድ ተወዳዳሪ ለመሆን አንዱ ዘዴ ነው፡፡ በማምረትና አገልግሎት በማቅረብ የተሰማሩ ኩባንያዎች ቴክኒካዊ ብቃትንና ፈጠራን የማሳደግ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ መንግስትም ብሔራዊ ጥቅምን የማሟላት ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ እዘኒህ ካምፓኒዎች ቴክኒካዊ ብቃትና ፈጠራን ለማሳደግ በሚያካሂዱት ተግባር ልዩ ልዩ ድጋፍ መስጠት ይገባዋል፡፡ በኢንዱስትሪና በምርምር ተቋሞች መካከል ትብብርና የስራ ቅንጅት እንዲኖር የሚያስችል ምቹ ሁኔታ መፍጠር አለበት፡፡ የዚህ ዓይነቱ ትብብር መኖር በተለይም አነስተኛና መካከለኛ ደረጃ ያላቸው የማምረቻና አገልግሎት መስጫ ተቋሞች ከአዳዲስ ቴክኒዎሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ፣ ፈጠራን እንዲያስፋፉና ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችል ብቃት እንዲገነቡ ምቹ ሁኔታን ይፈጥርላቸዋል፡፡ መንግስት ለምርምርና ለአዳዲስ ቴክኖዎሎጂ ፈጠራ በቂ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የፖሊሲ ድጋፍ ካደረገ በትናንሽ ኩባንያዎች ተግባራዊ ሊሆኑ የሚችሉ ፕሮጀክቶችን በሰፊው ዘርግቶ ስራ ላይ ለማዋል ይቻላል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የማምረት ዘዴያቸው እንዲሻሻል ይረዳል፡፡ የምርምር ግኝቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉና የቴክኒዎሎጂ ሽግግር እንዲኖር ምቹ ሁኔታ ይፈጠርላቸዋል፡፡ ስለአዳዲስ ቴክኒዎሎጂ መረጃ የማግኘት እድልም ይኖራቸዋል፡፡ ከዚህ ሌላ መንግስት የሰራተኛ ስልጠናና የስራ አመራር ብቃት ማሳደጊያ ድጋፍ መስጠት ይገባዋል፡፡*

*የእደ-ጥበብ ስራ በሀገሪቱ ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም እጅግ ዝቅተኛ በሆነ የጥራት ደረጃ የሚከናወንና በቂ ገበያም የሌለው በመሆኑ እድገት አላሳየም፡፡ እነዚህ በአነስተኛ የሰው ጉልበትና ወጪ የሚሰሩ የእደ ጥበብ ስራዎች በዘርፉ ለተሰማሩት ዜጎች የኑሮ መሰረት ከመሆናቸው ባሻገር ለኢንዱሰትሪ መስፋፋትም ድጋፍ በሚሰጡበት መንገድ ሲጠናከሩ ከፍተኛ ጥቅም ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ አናፂነት፣ ግንበኝነት፣ ብረት ስራ፣ የቆዳ ስራ፣ የሸክላ ስራ፣ የስፌት ስራ፣ የሽመና ስራ፣ የእንጨት ስራ ወዘተ. በተሻለ ሁኔታ እንዲደራጁ፣ እንዲስፋፉና ገበያም እንዲያገኙ ቢደረግ አሁን ከያዙት የሰው ኃይል በተጨማሪ የስራ እድል ሊያስገኙ ይችላሉ፡፡ የውጭ ምንዛሬን ለመቆጠብ፣ ለኢንዱስትሪ ግንባታ መነሻ የሚሆን የቴክኒክ ልምድና የስራ ዲስፕሊን ይፈጥራሉ፡፡ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማሟላት ከፍተኛ ድጋፍ ያደርጋሉ፡፡ በእነዚህ መስኮች የቴክኒክ ልምድ ያገኙ ሰዎች ወደሌሎች ኢንዱስትሪዎች ተዛውሮ ለመስራት እንዲችሉ የመሸጋገሪያ ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ፡፡*

*እነዚህን አነስተኛና ሌሎችም በመካከለኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተቋሞች መንግስት የታክስ እፎይታ እንዲያገኙ፣ የመረጃና የአመራር ምክር፣ አነስተኛ በሆነ ወለድ በረጅም ጊዜ የሚከፈል ብድር፣ ወዘተ. እንዲያገኙ በመደገፍ ተወዳዳሪነታቸው እንዲጨምር ማድረግ አለበት፡፡ እንቅስቃሴያቸውን የሚደግፍ ራሱን የቻለ ተቋም እስከታች ማደራጀት፣ በራሳቸው ጉዳይ ላይ የሚመክርና ዘላቂ ጥቅማቸው እንዲጠበቅ የሚረዳ ነፃ ማህበር እንዲያቋቁሙ ማድረግ፣ ለምርታቸውና አገልግሎታቸው ማስፋፊያ በቂ ቦታ፣ የማስተዋወቂያና የመረጃ ማሰራጫ ማዕከል እንዲያገኙ መርዳት ተወዳዳሪነታቸውን የሚያጠናክር ስለሚሆን መንግስት ሊያተኩርበት ይገባል፡፡*

## 2.6.6 **ነፃ የጉልበት ገበያ መፍጠር**

*ሰፊ የስራ እድል እንዲኖር በቅድሚያ ሰፊ ኢንቨስትሜንት መኖር አለበት፡፡ የተሣካ ኢንቨስትሜንት እንዲኖር ነፃ የጉልበት ዝውውር መኖር አለበት፡፡ በሀገሪቱ ምቹ የኢኮኖሚ ሁኔታ ባለመኖሩና ፈጣን የልማት ግስጋሴ ባለመጀመሩ የስራ እድል መፍጠር አልተቻለም፡፡*

በየጊዜው አዳዲስ ስራ ፈላጊ እየተጨመረና እንዲያውም የተማረ (የሰለጠነ) ስራ አጥ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው፡፡ ሀገሪቱ አዳዲስ የስራ እድል የሚፈጥር ኢንቨስትሜንት ልታስፋፋ ባለመቻሏ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ሰርተው የመኖር መሰረታዊ መብታቸውን ሊጠቀሙ አልቻሉም፡፡ የመንግስት ፖሊሲ ለኢንቨስትሜንት ማደግና ለስራ እድል መከፈት የሚያግዝ ባለመሆኑ ችግሩ ከቁጥጥር ውጭ ወደመሆን እያመራ ነው፡፡ የመሬት ባለቤት መንግስት በመሆኑና አደገኛ የዘረኝነት ፖሊሲ በስራ ላይ በመዋሉ ተጨማሪ የስራ እድል መክፈት ቀርቶ ስራ የነበራቸውም ሳይወዱ በግድ ከስራ ቦታቸው እየተባረሩ ወደ ስራ አጥነቱ ጎራ ተቀላቅለዋል፡፡ እንዲህ አይነት ችግር ላጋጠማቸው ደግሞ የስራ መፈለጊያ፣ ካሣ ወይንም የማህበራዊ ደህንነት አገልግሎት እንዲያገኙ ባለመደረጉ ለከፋ ስቃይ የተጋለጡት ከሚያስተዳድሯቸው ቤተሰቦች ማለትም ከሚያሳድጓቸው ሕፃናትና ከሚጦሯቸው ወላጆች ጋር ነው፡፡ ከዚህ ችግር መውጣት የሚቻለው ነፃ የጉልበት ዝውውር እንዲኖር የሚያስችል ፖሊሲና አደረጃጀት በመፍጠር ነው፡፡ ማንም ባለሀብት ኢንቨስትሜንት ለማካሄድ በሚፈልግበት ጊዜ ከካፒታል ሌላ መሬትና ጉልበት ማግኘት ይኖርበታል፡፡ እነዚህን ለኢንቨስትሜንት አስፈላጊ የሆኑ መሣሪያዎች ለማግኘት የሚያስችለው የነፃ ገበያ ስርዓት መኖር አለበት፡፡ ከገበያ ስርዓት ውጭ የሚጫኑበት የፖለቲካና የጎሣ እንቅፋቶች መወገድ አለባቸው፡፡

ማንም ዜጋ የሚከተለው ኃይማኖት፣ የሚናገረው ቋንቋ፣ የሚያራምደው የፖለቲካ እምነት ወዘተ. ሳያግደው ሰርቶ መኖር የሚችልበት፣ በየትኛውም የሀገሪቱ ክልል በነፃነት ተዘዋውሮ መስራት የሚያስችለውና ሁሉንም የሀገሪቱን አካባቢዎች «ሀገሬ» ብሎ ሊያስብ የሚያስችለው ብሔራዊ ስሜትና ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡

## 2.6.7 **የተጠቃሚዎች (የሸማቾች) ጥበቃ ስርዓት ማስፈን**

የምርትና አገልግሎት መጠን እንዲያድግና ጥራቱም እንዲሻሻል ከሚደረገው ጥረት ጎን ለጎን የተጠቃሚውንም መብት ማረጋገጥ ቸል ሊባል የሚገባው ነገር አይደለም፡፡ ምርትና አገልግሎት ሲስፋፋ ጥራቱንና ሊከፈል የሚገባውን ዋጋ ማመጣጠን ተገቢ ነው፡፡ የምርትና የአገልገሎት ማስታወቂያ ተጠቃሚው የሚገዛውን የምርትና አገልግሎት አይነት እንዲመርጥና እንዲወስን መረጃ የማቅረብ ስራ ቢሰሩም ዋነኛው አላማቸው ተጠቃሚዎች እንዲገዙ ማሳመን በመሆኑ የጥራቱንና የዋጋውን ተመጣጣኝነት የማሳየት አቅም የላቸውም፡፡ የተጠቃሚዎች ጥበቃ መኖር በጥራትና በዋጋ መካከል ሰፊ ክፍተት እንዳይፈጠርና ገዥዎች ጉዳት እንዳይደርስባቸው ይረዳል፡፡ ይህ ጥበቃ በተለያየ መንገድ ሊካሄድ ይችላል፡፡ መረጃ በማቅረብ፣ የማማከር አገልግሎትን በማስፋትና የጥበቃ ሕግ በማውጣት ሊሰራ ይችላል፡፡ የጥራት ደረጃ መቆጣጠሪያ ተቋሞችን አገልግሎት በማስፋት ማንኛውም ምርትና አገልግሎት ከመሸጡ በፊት የጥራት ደረጃው፣ ከአካባቢው ሁኔታ ጋር ያለው ተስማሚነትና የመሳሰሉት ሁኔታዎች ተፈትሸው ለሽያጭ የሚቀርብበትን ስርዓት ማበጀት ይቻላል፡፡ የጥራት ፍተሻ ውጤቶች በተለያዩ የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ለሕዝብ ይፋ እንዲሆኑ ማድረግ ለገዥው ብቻ ሳይሆን ለሻጩም ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡ በዚህ መንገድ የጥራት ማረጋገጫ የተሰጣቸው ምርትና አገልግሎት አቅራቢዎች በራስ የመተማመን መንፈስ እንዲያዳብሩና በርካታ ደንበኞችን እንዲያፈሩ ስለሚረዳቸው የጥራት ቁጥጥርን ደጋፊ ሆነው ይሰለፋሉ፡፡

ተገልጋዩ ሕዝብ ከሌሎችም በርካታ ድርጅቶች መረጃ ሊያገኝ ይችላል፡፡ ለምሳሌ የሸማቾች ማህበርን በማቋቋም ይኸንን አገልግሎት በተሻለ ሁኔታ የሚያገኝበት እድል መፍጠር ተገቢ ነው፡፡ ከመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጣቸው የምክር መስጫ ማዕከላትን በየቀበሌው በመክፈት ተጠቃሚው ሕዝብ የምርትና የአገልገሎቶችን ጥራትና ዋጋ የሚመለከቱ መረጃዎችን በነፃ እንዲያገኝ ማድረግ ይገባል፡፡ እነዚህ አካላት ሕግ አውጭው ለሸማቾች ጥበቃ ሕግ በሚያወጣበት ጊዜ በምክርና አስተያየት በማቅረብ ሊደግፉ ይችላሉ፡፡ ሕግ አውጭው አካል ለምግብነትና ለመድሃኒት የሚያገለግሉ ምርቶችና አገልግሎቶች የተሰሩበትንና ይዞታቸውን፣ በጥቅም ላይ የሚቆዩበትን ጊዜ፣ የተመረቱበትን ቦታና ዘመን የሚገልጽ መረጃ በላያቸው ላይ እንዲይዙና በእቃዎቹ ላይ እንዲለጠፍ የሚያስገድድ ሕግ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ በፀጉር ቤቶች፣ በምግብ ቤቶችና በሌሎችም አገልግሎት መስጫዎችም ተመሳሳይ ግዴታ እንዲኖር ማድረግ ይቻላል፡፡

## 2.6.8 **በኢንዱስትሪ ዘርፍ የእንደገና ግንባታ ማካሄድ**

በሕግና በኢኮኖሚ ባህርይ የተለየ መሰረት የነበረውን አንድ ሀገር ወደ አዲስ ስርዓት ለማስገባት የሚደረግ ስራ ቀላል አይደለም:: ኢኮኖሚውን ብቻ ሳይሆን የሕግና የአስተዳደር ስርዓቱንም መቀየርና በአዲስ መልክ ማዋቀር ያስፈልጋል:: አዲስ ሊገነባ በሚታሰበው ፍትሀዊ የካፒታሊዝም ስርዓት መርሆዎች መሰረት እንደገና መቃኘትና ማስተካከል ይጠይቃል:: ይህ ደግሞ ከጊዜ ጋር የሚደረግ ትግልንም የሚጨምር ከባድ ተግባር ነው:: በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረው የዕዝ ኢኮኖሚ ስርዓት የእያንዳንዱን ዜጋ የግል ተነሳሽነትና ኃላፊነት የገደለ ነበር:: ፈጠራና ምርት በአብዛኛው የተዳከሙ ስለነበሩ ምርታማነት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነበር:: ለማይረባ ጥቅም የተፈጥሮ ሀብትን የማመናመንና አካባቢን የሚጎዳ ብዙ ዓይነት እንቅስቃሴ ሲደረግ ከመቆየቱ በስተቀር ለወደፊቱ ልማት መነሻ የሚሆን ጥሩ መሰረት አልተፈጠረም ነበር:: አሁንም የቀጠለው ሁኔታ ተመሳሳይ ነው:: ቤቶች፣ የትራንስፖርትና መገናኛ አውታሮች፣ የትምህርትና የጤና፣ የንፁህ መጠጥና የኤሌክትሪክ ወዘተ. አገልግሎቶችና መሰረተ ልማቶች እጅግ የወደቁ ናቸው:: እንደገና ግንባታው እነዚህን ሁሉ የሚሸፍን መሆን ይገባዋል::

ይህ ኃላፊነት በመንግስት ብቻ የሚሰራ ሳይሆን የግል ባለሀብቶችም ሊሳተፉበት የሚገባ ተግባር ነው:: የወደቁትን የማምረቻና የአገልግሎት መስጫ አውታሮች እንዲያገግሙና ብቃት ያለው ስራ እንዲጀምሩ ከማስቻል በተጨማሪ በርካታ አዳዲስ የምርት ተቋሞችና አገልግሎት መስጫዎች መከፈት አለባቸው:: ይኸ ደግሞ ለልማት የሚመች ፖሊሲ፣ ከፍተኛ የገንዘብ ወጪ፣ ሰፊ ጊዜ፣ የስራ ተነሳሽነትና ፍላጎት ይጠይቃል:: የባለሀብቶችን ብቻ ሳይሆን የባለሙያዎችን እውቀትና የመላውን ሕዝብ ርብርብ ይጠይቃል:: ብቃት ያለው የፌዴራል፣ የክልልና የአካባቢ አስተዳደራዊ መዋቅርና አመራር፣ በአግባቡ የሚሰራ የፍትህ ስርዓት መገንባትን ይጠይቃል:: በመንግስት ቁጥጥር ስር የቆዩትን የምርትና አገልግሎት ተቋሞች የሰራተኞችን ሕይወት አደጋ ላይ በማይጥል፣ የባለሀብቶችን ትርፍ የማግኘት ፍላጎት በማይጎዳና ተጨማሪ የሰራተኛ ኃይል ለመቅጠርም ሆነ ተጨማሪ ምርትና አገልግሎት ለመፍጠር በሚያስችል መንገድ ወደግል ይዞታ በማዞር በገበያ ስርዓት እንዲሰሩ ማድረግን ይጠይቃል:: ይህ ስራ ሲጠቃለል መንግስት ከሂደቱ እጁን ለማውጣትና ባለሀብቶች በገበያ ሕግ እንዲሰሩ እድሉን ለመስጠት የተዘጋጀ መሆን አለበት::

## **2.6.9 ማጠቃለያ**

በአጠቃላይ በአሁኑ ወቅት በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የምርምርና ሥርፀት፣ የምህንድስናና የማማከር አገልግሎቶች፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና የልማት አቅምን ከጥገኝነት በሚያላቅቅና ደረጃ በደረጃም በራስ መተማመንን ለመፍጠር በሚያስችል መልኩ ገና አልተገነባም:: ከውጭ የሚገቡትን የኢንዱስትሪ ግብዓቶች በአገር ውስጥ በሚገኙት ለመተካት የሚደረጉ የቴክኖሎጂ ተግባራት፣ ማሽነሪዎችንና የእጅ መሣሪያዎችን የመሥራት፣ የመለዋወጫ ዕቃዎች በአገር ውስጥ እንዲፈበረኩ የሚደረጉ ጥረቶች፣ ልዩ ሙያን በሚጠይቁ የቴክኒክ ሥራዎች ላይ የተሠማሩ ባለሙያዎችን የሙያ ብቃት ለማሻሻል የሚሰጡ ሥልጠናዎች፣ የዲዛይንና ኢንጂነሪንግ እንዲሁም የማማከር አግልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስችሉ ሥራዎችና ተቋማት ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ናቸው::

ዘርፉ ለአጠቃላይ ብሔራዊ ምርቱ የሚያደርገው አስተዋጽኦ አነስተኛ ብቻ ሳይሆን የምርታማነቱም መጠን እያሽቆለቆለ ነው:: ይህም በፊንታው በገበያው ዘርፍ ያለውን ተወዳዳሪነት ብቃት ዝቅ እያደረገው ነው:: ዘርፉ መልክ ያለው፣ በሥርዓት የተቀናጀና ጠቀም ያለ የመንግሥት እርዳታና ድጋፍ ያስፈልገዋል:: ከላይ የተዘረዘሩትን ችግሮች ለመፍታት፣ ሠፊ የሆነ፣ በዘርፉ የተለያዩ ገጽታዎች ላይ ያተኮረ ዕቅድ ማውጣት ያስፈልጋል:: በሥራ ላይ ለማዋልም እንዲቻል በዘርፉ እንቅስቃሴ ተጠቃሚ የሆኑትን ወገኖች፣ ማለትም መንግሥትን፣ የግል ዘርፍ ባለቤቶችንና ሠራተኞችን የሚያቀናጅ ዘለቄታዊ አካሄድ መከተል ያስፈልጋል:: እንዲህ ያለው ዕቅድ የአገሪቱን የምርት ንብረቶች በየዓይነታቸው ለይቶ ዝርዝር በማውጣትና ለአገሪቱ የተሻለ ጠቀሜታ ይሰጣሉ የሚባሉትን የኢንዱስትሪ ዘርፎችና የልማት ዕቅዶች ለይቶ በመፈረጅ መጀመር አለበት::

ይህ ከተደረገ በኋላ፣ ከፍ ሲል የተጠቀሱት ሦስቱ ባለጥቅሞች አንድ ላይ ሆነው፣ ወይ በምርት ተቋማት ደረጃ ተቋማቱ ያሉባቸውን የውስጥና የውጭ ችግሮች በመመርመር የመፍትሔ እርምጃ ይወስዳሉ፣ ወይም በፖሊሲ ደረጃ ችግሮቹን ለመፍታት ብቃትና ኃላፊነቱ ያላቸውን ተቋማት መፍጠር ወይም ያሉትን ማጠናከር ይቻላል።

በቴክኖሎጂ ረገድ ያለውን ችግር በተመለከተ መፍትሔ ለማቅረብ ሲታሰብ፡ ጥረቱ መጀመር ያለበት በአጠቃላይ ስለኢንዱስትሪ ልማት ምንነት ንድፈ-ሃሳባዊ ዕውቀትን በማዳበር፡ በተለይም ከሌላ አካባቢ የምናሸጋግራቸውን ቴክኖሎጂዎችን አጠቃቀም በተመለከተ አስፈላጊውን ዕውቀት ማግኘት አስፈላጊ ነው። በተጨባጭ ጥናት ላይ የተመሠረተ ማስረጃ እንደሚያመለክተው ቴክኖሎጂ የተለየ ባሕሪይና መልክ አለው። የሚገኘውን ቴክኖሎጂ ዝም ብሎ መገልበጥ ቀላል አይደለም። የተገኘውን ቴክኖሎጂ ለመገልበጥ የሚሞክረው የምርት ተቋም ብዙ ጥረት ማድረግ አለበት። የማምረት ልምድ ወይም ተመክሮ ደግሞ እጅግ አስፈላጊና መሠረታዊ ነው።

ከኢንዱስትሪ ጋር ዘግየት ብለው በተዋወቁት በአብዛኛዎቹ አገሮች የነበረው ሁኔታ ተመሳሳይ ስለነበር በኢትዮጵያም በዘርፉ ውጤት ማግኜት እንደሚቻል ግንዛቤ ማግኜት ይቻላል። አሁን ያለው ሁኔታ የሚያመለክተን፡ በዚህ ዘርፍ አስፈላጊ የሆኑ ፖሊሲዎች ተቀርፀው በሥራ ላይ አለመዋላቸውን ነው። ስለዚህም የምርት ተቋማቱም ሆኑ መንግሥት ዘርፉ በተወሰነ የእድገት ደረጃ እንዲራመድ ጥረት ማድረግ አለባቸው። በዚህ ረገድ በአንድ በኩል ተቋማቱ ራሳቸው አስፈላጊውን የቴክኖሎጂ ብቃት መገንባት አለባቸው። በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት ለአጠቃላይ ኢኮኖሚ ዕድገት የሚያመቹ ሁኔታዎችን መፍጠርና በደንብ የተጠና የኢንዱስትሪ ልማት ዕቅድ መቀየስ ይኖርበታል።

የማበረታቻ ድጋፎችም ሆኑ የምርት ሂደት ብቃት በተግባር ላይ ሊውሉና ሊሚሉ የሚችሉት በአስፈጻሚ ተቋማት መዋቅር አማካይነት ነው። እነዚህ ለገበያ እንቅስቃሴ አመቺ ሁኔታ ለመፍጠር የተቋቋሙት ተቋማት ደግሞ ደንቦችን ይወስናሉ። የእነዚህ ተቋማት አለመሟላት ለምርት ሂደቱ ቅልጥፍና ማጣትና በቂ ኢንቨስትመንት ላለመኖሩ ዋና ምክኒያት ነው። ስለዚህም የኢንዱስትሪ ልማት ፖሊሲ ሲወጣና በሥራ ላይ እንዲውል ሲደረግ፣ ለቴክኖሎጂ ብቃትና ለኢንዱስትሪው ዘርፍ መበልፀግ አመቺ ሁኔታዎችን የሚፈጥሩ ተቋማት መመሥረትና ማዳበር አብሮ ሊጤን የሚገባው ጉዳይ ነው። እንዲህ ያሉት ተቋማት፣ ገንዘብን፣ ኢንፎርሜሽንን፣ አገልግሎቶችን፣ የደረጃ ጥበቃን፣ የባለሙያዎችን እርዳታና የመሳሰሉትንም ድጋፎች ለአምራቾች በማቅረብ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ናቸው። የተሳካለት የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ ማካሄድ፣ ያሉትን የገበያ ኃይሎች ለመደገፍ ወይም በሌላ ለመተካት የሚችሉ ተቋማትን በተቀናጀ መልክ ማቋቋምን ይጠይቃል። በምርት ሂደት፣ በቴክኖሎጂ ወይም በሥልጠና ረገድ በተቋማት መካከል ግንኙነት እንዲዳብር የሚያደርጉ፣ አነስተኛ ለሆኑ ተቋማት አስፈላጊውን ድጋፍ የሚሰጡ፣ የምርት ተቋማት ራሳቸውን በአዲስ መልክ እንዲያዋቅሩና ከጊዜው ጋር አብረው እንዲራመዱ የሚያበረታቱ የኢንዱስትሪ ተቋማት መዋቀር አለባቸው።

## 2.7 የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኘው የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በማንኛውም አይነት መለኪያ ሲመዘን ዝቅተኛ ነው። ዘርፉ ለጠቅላላው የሀገር ውስጥ ምርትም ሆነ ለኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው ድርሻ አነስተኛ ነው። በኮንስትራክሽን ዘርፉ ሀገሪቱ የደረሰችበት የሳይንስና የቴክኒዎሎጂ ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ ነው። የኮንስትራክሽን ምርምርና ስርዓት አቅም አልተገነባም። በኮንስትራክሽን ማቴሪያል ላይ ከሚደረግ አነስተኛ ምርምር ሌላ ጎልቶ ሊጠቀስ የሚችል እንቅስቃሴ በዚህ ዘርፍ አልተደረገም። የከፍተኛ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ዲዛይን አቅም ደካማ ነው። የዲዛይን አቅም ብቻ ሳይሆን የከፍተኛ ኮንስትራክሽን ፕሮጀክቶችን ለመከተል የሚያስችል አቅምም በጣም ዝቅተኛ ነው። ለሀገር በቀልና ባህላዊ የኮንስትራክሽን ቴክኒዎሎጂ መሻሻልና ማደግ የሚገባው ትኩረት ስላልተሰጠው ከዘርፉ የሚጠበቀውን ውጤት ማምጣት አልተቻለም። ሌላው ቀርቶ በተነፃፃሪነት ዝቅተኛ በሆነ ወጪ ሊሟላ ይችል የነበረውና በብዛት የሰው ኃይል የሚጠቀም የኮንስትራክሽን ዘዴን ለማሳደግ የተደረገው ጥረት ውስን ነው። እንደዚሁም ጥራታቸውን የጠበቁና ለኮንስትራክሽን ተግባር የሚያገለግሉ የእጅ መሣሪያዎችን በሀገር ውስጥ ለማምረት ሳይቻል ቀይቷል። በተጠናከረ መልክ የሚከናወን የዲዛይን ስታንደርድ ኮድ የለም።

በኮንስትራክሽን ሞያ የሚሰማራው የሰው ኃይል የሚሰጠው ስልጠና ከሀገሪቱ ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ባለመሆኑ በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ሞያ የሰለጠኑ ብቁ ሞያተኞች በየመስኩ ማግኘት አይቻልም። በግድቦች፣ በሕንፃዎች፣ በመንገዶችና በመሳሰሉት የኮንስትራክሽን ዘርፎች የሚያስፈልጉት የኮንስትራክሽን ቴክኒዎሎጂዎችና ከፍተኛ ሞያተኞች በሀገር ውስጥ ስለሌሉ የዘርፉ እንቅስቃሴ በአብዛኛው የውጭ ጥገኛ ነው። ለኮንስትራክሽን ስራዎች በውጭ ሀገር አማካሪዎችና ኮንትራክተሮች የሚከናወኑ በመሆናቸው ጥገኝነቱ የሰፋና በብዙ መልክ የሚንፀባረቅ ነው። የዘረፋን እድገት ከሚጎትቱት መካከል አንዱ ነጥብ ይኸው የውጭ ጥገኝነቱ የሰፋ መሆኑ ነው። የራሳችን አቅም እስኪሟላ ቴክኖዎሎጂ፣ ፋይናንስና የምክር አገልግሎት ከውጭ ማምጣታችን ባልከፋ ነበር። ነገር ግን ከውጭ የምናገኘውን ልዩ ልዩ ግብዓት የራሳችንን አቅም ለማጠናከር የሚያስችል የሳይንስና ቴክኒዎሎጂ ሽግግር በሚያመጣ መልኩ በአግባቡ የመጠቀም ከፍተኛ ችግር መኖሩ ዘርፉን በቅርብ ጊዜ ውስጥ ወደሚፈለገው ደረጃ ለማድረስ ያለው ተስፋ የመነመነ ነው። በመስኩ የተሰማሩትን የተወሰኑ ሀገር በቀል ካምፓኒዎች የሚያደፋፍርና የሀገሪቱን ዘላቂ ጥቅም አርቆ የሚመለከት ግልፅ ፖሊሲ ባለመኖሩ የሀገሪቱ የኮንስትራክሽን አቅም ለረጅም ጊዜ እንደቀጨጨ መቆየት ግድ ሆኖበታል።

በመስኩ የተሰማሩ ባለሀብቶች ለኮንስትራክሽን ስራ የሚያስፈልጋቸውን ቴክኒዎሎጂ ከውጭ የሚያስገቡበት አሰራር ቀልጣፋና ቀላል እንዲሆን ማድረግ፣ በፋይናንስም ይሁን በቴክኒዎሎጂና በባለሞያ አቅማቸው ምክንያት ከፍተኛ የኮንስትራክሽን ስራ እንዲሰሩ ከውጭ የምናስገባቸው ተቋሞች ከሀገር ውስጥ ኩባንያዎች ጋር በሰብ ኮንትራት መልክ የሚተሳሰሩበትን ሁኔታ እየፈጠሩ የቴክኒዎሎጂና የማኔጅሜንት እውቀት ሽግግር እንዲኖር ማመቻቸት፣ የተሻለ አቅም ያላቸው ሀገር በቀል የኮንስትራክሽን ድርጅቶች ውጭ ሀገር በሚደረጉ የኮንስትራክሽን ጨረታዎች ተወዳድረው ለማሸነፍ እንዲችሉና በተለያየ መንገድ ብቃታቸውንም ሆነ እውቅናቸውን ለማሳደግ የሚረዳ ጠቀሜታ እንዲያገኙ መደገፍ፣ የብድር፣ የስልጠና፣ የታክስና የቀረጥ ቅነሳ፣ የማበረታቻ ሽልማትና የመሳሰሉትን ማደፋፈሪያዎች መስጠት ከመንግስት የሚጠበቅ ቢሆንም እስካሁን በዚህ ረገድ የሚደረገው ጥረት አነስተኛ ነው።

በግድቦችና በሕንፃዎች ግንባታ ያሉትን ልዩ ልዩ የኮንስትራክሽን ችግሮች ለጊዜው አቆይተን የመንገድ ኮንስትራክሽንን ብቻ እንኳ ለአብነት ያህል ብንመለከት ሀገሪቱ በዘርፉ ያለችበትን ዝቅተኛ ደረጃ በቀላሉ ለማየት ይቻላል። እ.ኤ.አ በ1994 ከወጣ የመንገድ ባለሥልጣን ሪፖርት እንደሚያሳየው በሀገሪቱ ውስጥ ያለው ጠቅላላ መንገድ ከ20 ሺህ ኪ.ሜ. ያነሰ ሲሆን ከዚህ ውስጥ የአስፓልት መንገድ 4109 ኪ.ሜ ብቻ ነበር። የጠጠር መንገድ ደግሞ 9287 ኪ.ሜ ብቻ ነበር። ሌላው የገጠር መንገድ ሲሆን በዝናብና በጎርፍ በየጊዜው እየተበላሸ አገልግሎቱ የሚያቋርጥ ስለሆነ ብዙም አስተማማኝነት የሌለው ነው። እ.ኤ.አ በ1997 የወጣ የመንገድ ባለሥልጣን ሪፖርት ደግሞ ጠቅላላ የሀገሪቱ መንገድ ወደ 30 ሺህ ኪ.ሜ እንዳደገ ቢያመለክትም ከዚህ ውስጥ አስፓልት የሆነው መጠን እ.ኤ.አ በ1994 ከነበረው ብዙ አልጨመረም። ቀደም ሲል አስፓልት የነበሩትንና የተበላሹትን የመጠገኑም ስራ ከሌሎች ዘርፎች ጋር ሲነፃፀር የተሻለ ቢሆንም በጣም አዝጋሚ ነው።

በጠጠርና በገጠር መንገድ ስራ ረገድ ከ1994 እ.ኤ.አ የተሻለ መጠን የተሰራ ቢሆንም ብዙም ሳይቆይ ከኤርትራ ጋር ጦርነት በመጀመሩ ለመንገድ ግንባታ ከውጭ የሚገኘው ብድርና እርዳታ ተስተጓጉሎ ስለነበር ሁኔታው መልሶ አዝጋሚ ሆኗል። ሀገር በቀል የመንገድ ስራ ኩባንያዎቻችንን የሚያጠናክር ፖሊሲ ቢኖር ኖሮ የውጭ ብድር በሚስተጓጎልበት ጊዜ ስራው ሁሉ ቀጥ ብሎ የሚቆምበት ችግር አይፈጠርም ነበር። በቅርብ ጊዜ ከወጡ መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው በሀገሪቱ ውስጥ ካለው ጠቅላላ የመንገድ አገልግሎት የሕዝቡ ድርሻ ለ1000 ሕዝብ ወደ 0.44 ኪ.ሜ ገደማ ብቻ ነው። ይህ መጠን ሌሎች ድሃ ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር ዝቅተኛ ነው።

በኮንስትራክሽን ዘርፍ ያለብንን ችግር ሳናቃልል በሀገሪቱ ውስጥ ዘላቂና አስተማማኝ ልማት መፍጠር አይቻልም። የዚህ ዘርፍ ደካማ መሆን በሌላም መስክ የሚደረገውን የኢንቨስትሜንት እንቅስቃሴ ስለሚጎትተው ተፅዕኖው ቀላል አይደለም። ስለዚህ የኮንስትራክሽን ዘርፍ እንዲጠ

ናከር ማድረግ ማለት ሌላውንም የልማትና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ማጠናከር ስለሚሆን ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልገው ዘርፍ ነው።

ይኸንን ዘርፍ በማጠናከር የምርትና የአገልግሎት እንቅስቃሴዎችን ማቀላጠፍ ይቻላል። ዜጎች የተቀላጠፈ ማህበራዊ አገልግሎት የሚያገኙበትን ሁኔታ መፍጠር ይቻላል። የገበያ ስርዓቱ ቀልጣፋ እንዲሆን በማድረግ የሻጭንና የገዥን ወጪና ድካም በከፍተኛ ደረጃ ማቃለል ይቻላል። ለበርካታ ዜጎች የስራ እድል መፍጠርም ይቻላል። በተለይ የሀገር በቀል የግል ኩባንያዎችን ጠቅላላ አቅም በማሳደግም ሆነ የሳይንስና ቴክኒዎሎጂ ሽግግር እንዲኖር በማድረግ የራሳችንን የኮንስትራክሽን ደረጃ ማሳደግ ይቻላል። በዚህ መንገድ የውጭ ምንዛሬ ለመቆጠብ፣ የውጭ ብድር ሸክምን ለመቀነስና የዘርፉን እድገት ዘላቂና አስተማማኝ ለማድረግ ይቻላል።

በመሆኑም በኮንስትራክሽን ዘርፍ የወደፊቱ ትኩረት በቅድሚያ ማረፍ ያለበት ለሀገር በቀል የግል ኩባንያዎች መጠናከር የሚረዱ ተጨባጭ እርምጃዎችን በመውሰዱ ጥረት ላይ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ለዘርፉ እድገት ቁልፍ ድርሻ ያለው የመረጃ አሰባሰብ፣ አሰረጫጨትና አጠቃቀም የሚጠናከርበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። የኮንስትራክሽን ቴክኒዎሎጂ በሀገር ውስጥ የሚያድግበትን መንገድ መቀየስና በሰው ኃይል የመጠቀም የኮስትራክሽን ዘዴ እንዲጠናከር ማድረግ ከፍተኛ ትኩረት ሊያገኝ የሚገባው ነጥብ ነው። በኮንስትራክሽን ዘርፍ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ሌላ ጉዳይ ደግሞ በዘርፉ የሚካሄዱ ስራዎች የአሁኑን ፍላጎታችንን ከማሟላት አልፎ ስትራቴጂያዊ ጥቅሞቻችንን በሚያረጋግጡበት መንገድ በሚገባ እየተጠኑ መሰራት ያለባቸው መሆኑ ነው። ለምርትና ለማህበራዊ አገልግሎት ማዕከል ለሆኑ ስትራቴጂያዊ አካባቢዎች ቅድሚያ መስጠት ያስፈልጋል። ስራው በተገቢው ጥራትና ደረጃ መሰራቱን የሚያረጋግጥ የጥራት ደረጃ ማረጋገጫ ስርዓት በማበጀት ለተደጋጋሚ ወጪና ለኪሳራ የማይጋብዝ አሰራር ማስፈን ይገባል። ከዚህ ሌላ የኮንስትራክሽን ስራችን የሕዝቡን ፍላጎት የጠበቀና በሕዝቡም የሚደገፍ እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል።

የኮንስትራክሽን ስራችን የዘርፉን አገልግሎት ፈፅሞ ማግኘት ሳይችሉ ለቆዩትና ለተረሱት አካባቢዎች፣ የተቀናጀ መሰረተ ልማትና ኢንቨስትሜንት ለማካሄድ ፖቴንሽያል ላላቸው አካባቢዎች ከፍተኛ ትኩረት መስጠት ይኖርበታል። አዳዲስ የኮንስትራክሽን ስራዎችን ከማስፋፋት በተጨማሪ በፊት የተሰሩትንም በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ ወቅታዊ ጥገናና የደረጃ ማሳደግ እንዲካሄድባቸው ማድረግ ይገባል። ለኮንስትራክሽን ስራ የሚያስፈልገውን የሪሶርስ አመዳደብ፣ አጠቃቀምና እንቅስቃሴ በየጊዜው ማሻሻል ያስፈልጋል።

## 2.8. የኢንዱስትሪ ሰላም (አሠሪና ሠራተኛ)

በጉልበት (በስራ) ገበያ ውስጥ ሻጭና ገዥ በነፃነት የሚጫወቱበት ሁኔታ መኖር አለበት። በሌላ አገላለፅ ነፃ የሆነ የጋራ ድርድርና ስምምነት መኖር አለበት። ሰራተኛና አሰሪ በክፍያ፣ በስራ ሰዓት፣ በእረፍት ጊዜ፣ በመዝናኛ በአጠቃላይ የስራ ሁኔታዎች ላይ በነፃ ተደራድረው መስማማት አለባቸው። በሁለቱም ወገን የሚካሄደውን ድርድርና ስምምነት የሚመሩት በሰራተኛው በኩል የሰራተኛ ማህበር ሲሆን በአሰሪዎች በኩል ደግሞ የአሰሪዎች ማህበር ናቸው። እነዚህ ማህበራዊ አጋሮች በኢኮኖሚው እንቅስቃሴ ውስጥ ጠቃሚ ሚና ይጫወታሉ። ምንም እንኳ ዋነኛ ተግባራቸው ሁሉም በየፊናቸው የሚወክሉትን አባላት ጥቅም ለማስጠበቅ ጠንካራ አቋም ይዞ መደራደር ቢሆንም በተመሳሳይ ሁኔታ ለጠቅላለው ኢኮኖሚ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። የሚደራደሩበት ስልትና ስርዓት የኢኮኖሚ ስርዓቱን እንቅስቃሴ ሊጎዳ ወይንም ሊጠቅም የሚችል ነው። ይኸንን ኃላፊነት የተገነዘበ ሰራተኛና አሰሪ እንዲኖር ያስፈልጋል። የኢኮኖሚው መረጋጋት በአብዛኛው የሚወሰነው በእነዚህ አካላት ነው። የሰራተኛ ማህበራት ጠንካራ እንዲሆኑ፣ በውስጣቸው ያሉ ልዩነቶችን እንዲያጠቡና የማህበራዊ መረጋጋት ዋልታ እንዲሆኑ ከተፈለገ አንድነት ሊኖራቸው ይገባል። ይኸንን ማድረግ ካልቻሉ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል ኃይል አይኖራቸውም። የተበታተኑና በቀላሉ ጥቅማቸውን ሊነጠቁ የሚችሉ ደካሞች ይሆናሉ። ይህ ሁኔታ ደግሞ የኢኮኖሚ አለመረጋጋትና ማህበራዊ ቀውስ እንዲፈጠር ያደርጋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ በግብርና ስራ የሚተዳደር ነው:: ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ በሌላ መስክ የተሰማራው ቁጥር አነስተኛ ነው:: በደሞዝና በሌላ ክፍያ የሚተዳደረው የስራ ኃይል አብዛኛው በመንግስት ስራ ውስጥ ገብቶ የሚኖር ነው:: የተወሰነ መጠን ያላቸው የራሳቸውን ስራ ፈጥረው የቤተሰብና ከዚያም ውጭ መጠነኛ የሰራተኛ ኃይል ጉልበት በመጠቀም የስራ እድል ያስገኙ የግል ተቋሞች ቢኖሩም ብዙው የስራ ኃይል በመንግስት መዋቅር ውስጥ የታቀፈ ነው:: በሀገሪቱ ውስጥ ዋነኛው የሰራተኛ ቀጣሪ መንግስት ሲሆን የግል ካምፓኒዎችም አስተዋፅኦ ያደርጋሉ:: መንግስት ሰራተኞችን የሚቀጥረው በሲቪል ሰርቪሱ መዋቅር ብቻ ሳይሆን በመንግስት የልማት ድርጅቶችና በመሳሰሉት ተቋሞችም ጭምር ነው:: እስካሁን ባለው አሰራር አሰሪዎችና ሰራተኞች በትብብርና በአጋርነት መርህ ተመስርተው የሚንቀሳቀሱበት ሁኔታ ደካማ ነው:: አሰሪና ሰራተኛ የጋራ ጥቅም ያላቸው መሆኑ ብዙም አይታወቅም:: ሁሉም የየራሱን ጥቅም ብቻ የመመልከት ዝንባሌ በሰፊው ይንፀባረቃል:: በእርግጥ አሰሪና ሰራተኛ የጋራ ጥቅም ያላቸው ቢሆንም አልፎ አልፎ የጥቅም ግጭትም እንደሚኖራቸው የታወቀ ነው:: ይኸንን የጥቅም ግጭት ማቻቻል ተገቢ የሚሆነው የጋራ ጥቅም በመኖሩ ነው:: አሰሪና ሰራተኛ ያሏቸውን የጥቅም ግጭቶች እያቻቻሉ የጋራ ጥቅማቸውን ማሳደግ የሚችሉት በነፃነት እየተደራደሩ የሕብረት ስምምነት ለመፍጠር ያላቸውን መብት በሚገባ ሲጠቀሙ ነው::

በአሰሪና ሰራተኛ መካከል በሚካሄድ ድርድርና በሚፈጠር የሕብረት ስምምነት ከጋራ ጥቅማቸው ወጪ የሌላ ወገን ጣልቃ ገብነት ሊታከልበት አይገባም:: በአሁኑ የሀገሪቱ ሁኔታ መንግስት አድራጊና ፈጣሪ መሆኑ ይታወቃል:: መንግስት አጠቃላይ ሁኔታዎችን ለሁለቱም ወገን በሚጠቅም መንገድ በሕጋዊ አግባብ አቅጣጫ ያስይዛል እንጂ ምን ያህል ሰራተኛ፣ በምን ያህል ደሞዝና ጥቅማ ጥቅም እንደሚቀጠር ሊወስን አይገባውም:: በሲቪል ሰርቪሱ መዋቅር ውስጥ ከሚታቀፉትና በመንግስት በጀት ከሚተዳደሩት በስተቀር ሌሎቹ ተቋሞች በውድድርና በራስ ቻይነት መርህ መመራት ስላለባቸው አብዛኞቹ የአሰሪና የሰራተኛ ጉዳዮች የሚወሰኑት በድርድርና በሕብረት ስምምነት መሆን አለበት::

አሰሪና ሰራተኛ ለሚያደርጉት ድርድርና ለሚደርሱበት የሕብረት ስምምነት የተደራጀ ስርዓት መኖር ይገባዋል:: በአንድ በኩል የሠራተኞችን ጥቅም የሚወክል የሠራተኛ ማህበር በሌላ በኩል የአሰሪዎችን ጥቅም የሚወክል የአሰሪች ማህበር መኖር አለበት:: በሁለቱም ወገን የሚመሰረቱ ማህበራት አባላት በፈቃደኝነትና በዴሞራሲያዊ መንገድ ያቋቋሟቸው መሆን ይገባቸዋል:: በነፃነት የተደራጁና በአባላት በተመረጡ አካላት የሚመሩ የጥቅም ማስጠበቂያ ዴሞክራሲያዊ ተቋማት መሆን አለባቸው:: የሰራተኛ ማህበራትም ሆኑ የአሰሪ ማህበራት የሚደራጁበትን አማራጭ መገምገምና መወሰን ለራሳቸው መተው የሚገባው ነው:: በዘርፍ፣ በፌዴሬሽን፣ በገጠር፣ በከተማ፣ በስራ ቦታ፣ በወረዳ፣ በክልል ደረጃ ባለው መዋቅር ሁሉ መምረጥና መወሰን የሚገባቸው ራሳቸው ናቸው:: ማንም ሰራተኛና አሰሪ በማህበራቱ ውስጥ እንዲገባ ወይንም እንዳይገባ በሌላ ውጫዊ ሀይል ሊገደድ አይገባውም:: መወሰን ያለበት ራሱ ብቻ ነው:: ማህበራቱ ለአባሎቻቸው ትምህርት፣ ስልጠና፣ ሕክምናና ሌላም አገልገሎት እንዲያገኙ ማድረግ፣ ውጤታማና አርአያ ሆነው ለሚገኙት ሽልማት፣ ልዩ ልዩ ማበረታቻና ጥቅማ ጥቅም መስጠት ትልቁ ስራቸው ነው:: በመንግስት የቀረጥ ወይም የኢኮኖሚ ፖሊሲ፣ የአሰሪና ሰራተኛ ፖሊሲ ወዘተ. በጋራና በተናጠል እየመከሩ የአባሎቻቸውን ጥቅሞች ለመከላከል ጥረት ማድረግ ግዴታቸው ነው::

በሕብረት ስምምነታቸው የሚካተቱ አጠቃላይ የስምምነት ስርዓቶች የስራ ሁኔታዎችን የሚወስኑ በመሆናቸው በጥንቃቄ፣ በጥናትና በመግባባት ሊፈፀሙ ይገባቸዋል:: የስራ ሰዓት፣ የእረፍት ጊዜ፣ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ የትርፍ ሰዓት ምጣኔ፣ ቦነስና የመሳሰሉት ስምምነቶች ለስንት ጊዜ እንደሚቆዩ ወይንም የደሞዝና የስራ ክፍያዎች ለስንት ጊዜ እንደሚያገለግሉ በስምምነቱ ውስጥ መወሰን ይኖርባቸዋል:: ልዩ ባህርይ ላላቸው ስራዎች ደግሞ እንደባህሪያቸው የተለየ ስምምነት ማድረግ ያስፈልጋል::

ሠራተኛና አስተዳደር በሕግ የተቀመጡ አነስተኛ ሁኔታዎችን ለማሟላት ነፃ ሆነው ሊደራደሩ ይገባቸዋል:: ለምሳሌ በሕግ የተወሰነው የሳምንት የስራ ሰዓት 40 ሰዓት ቢሆን ሰራተኛውና ማኔጅመንቱ ይኸንን አነስተኛ ሁኔታ ለማሟላት ሰምምነት ያደርጋሉ:: ከዚህ አነስተኛ ሰዓት

ያነሰ ወይንም የበለጠ መስራት ያስፈልግ ከሆነ መወሰን ያለባቸው በድርድርና በስምምነት ሊሆን ይገባል። ከክፍያ ጋር የሚሰጥ የ3 ሳምንታት እረፍት በሕግ የተወሰነ ከሆነ ከዚህ ለበለጠ ጊዜ ከክፍያ ጋር የሚሰጥ እረፍት እንዲኖር ከፈለጉ ተደራድረውና ተስማምተው መወሰን ይገባቸዋል። ለበዓል ጊዜ የሚሰጥ ተጨማሪ ክፍያ ወይም የዘመን መለወጫ ቦነስ ያስፈልግ ከሆነ በድርድር መፈፀም ያለበትና በሕብረት ስምምነት ውስጥ መካተት የሚገባው ነው።

በሕብረት ስምምነት የተካተቱ መብቶችና ጥቅሞች ሲጓደሉ ሰራተኞች የስራ ማቆም አድማ የሚያደርጉበት፣ አሰሪዎች ደግሞ ሰራተኞች ወደ ተቋሞቹ እንዳይገቡ በር የሚዘጉበት ስርዓት መፍቀድ ከዜጎች መብት ጋር በከፍተኛ ደረጃ የተያያዘ ነው። በእርግጥ ወደዚህ ደረጃ ከመድረሱ አስቀድሞ በሁለቱ ወገኖች መካከል ስምምነት እንዳይኖር ባደረጉ ጉዳዮች ላይ የግልግል ስርዓት እንዲኖር ማድረግ አንድ ጠቃሚ ነገር ነው። ከዚህ ሌላ የስራ ማቆም ለማድረግ ሰራተኞች እንዲወያዩበትና በአስፈላጊነቱ ላይ ውሳኔ እንዲሰጡበት ያስፈልጋል። ሰራተኞች የስራ ማቆም ለማድረግ መብት እንዳላቸው ሁሉ አሰሪዎችም በሰራተኞች ላይ ለተወሰነ ጊዜ በር ለመዝጋት መብት ይኖራቸዋል። እንዲህ ዓይነቶቹ እርምጃዎችና በሕገ መንግስታዊ ፍርድ ቤት ወይንም በአሰሪና ሰራተኛ ፍርድ ቤት ታይተው ውሳኔ ሊሰጥባቸው ቢችልም ከዚያ በፊት በግልግል መልክ ነገሮችን ማቃለል የሚቻልበት ስርዓት መከተል በሁለቱም ወገን ጠቃሚ ነው። መንግስት በአሰሪና ሰራተኛ ጥቅም ግጭቶች ላይ ጣልቃ ከመግባትና አንደኛውን ደግፎ ከመቆም መቆጠብ ወይም ገለልተኛ መሆን ይኖርበታል። በስራ ማቆም ወይም በበር መዘጋት ገቢ የተቋረጠባቸው ወገኖች ከመንግስት ካሳና የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን የሚያገኙበት ሁኔታም መኖር አይገባውም። ይልቁንም አንድም በራሳቸው ወጪ እንዲጠ ቀሙ አሊያም ከማህበራቸው ክፍያ እንዲያገኙ የሚችሉበትን አቅጣጫ መከተል የተሻለ ነው።

እዚህ ላይ መታወቅ የሚገባው ሰራተኞችና አሰሪዎች ተቀናቃኝ ብቻ ተደርገው መታየት የማይገባቸው መሆኑ ነው። የጥቅም ግጭቶች ሊያጋጥሟቸው ቢችሉም የሚያስተባብሯቸው ብዙ ዓይነት የጋራ ጥቅሞችም አሏቸው። የሁለቱም ማህበራት የሠራተኞችን የሞያ ስልጠና በመገምገም (በመመዘን)፣ የስራ ክርክር ዳኞችን በመወከል፣ ፖለቲከኞች በሚያዘጋጇቸው ስብሰባዎች በሀላፊነታቸው ስር በሚገኙ ጉዳዮች ላይ የጋራ አስተያየት በማቅረብ ወዘተ. ተባብረው ሊሰሩ ይችላሉ። በዚህም ልዩነታቸውን እያጠበቡ የጋራ መግባባት እንዲጠናከርና የኢንዱስትሪ ሰላም እንዲሰፍን ማድረግ ይችላሉ።

በሀገራችን ነፃ ሆኖ የተደራጀ ጠንካራ የሰራተኛ ማህበር ባለመኖሩ የሠራተኞችን መብት የሚያስጠብቅና ጥቅማቸውን የሚከላከል በቂ ዋስትና ተፈጥሯል ለማለት አይቻልም። በተለይ በአሁኑ አገዛዝ ዘመን የሠራተኞች ሁኔታና ማህበራዊ ደህንነት እጅግ አሳዛኝ ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። የአሠሪዎች ኃይል ገደብ የሌለው መስሎ የሚታይበት ሁኔታ በሰፊው ተንሰራፍቷል። ሰራተኛን ካለቅድሚያ ማስጠንቀቂያ፣ ካለአንዳች ካሣና የስራ መፈለጊያ ማባረር እንደቀላል ነገር የሚታይ ነው። አብዛኛው የሰራተኛ ኃይል የሚቀጠረው በመንግስት የልማት ድርጅቶች ውስጥ በመሆኑና በሰራተኛ ማህበር አመራር ላይ የሚቀመጡት አብዛኞቹ መሪዎች ስልጣን ላይ ያለው ፓርቲ ወገንተኞች በመሆናቸው በሰራተኛው ላይ የሚደርሰው ጉዳት የሚያስጨንቃቸው አይደሉም። እንዲያውም ሠራተኞች እንዲባረሩ ከማኔጅሜንቱ ጋር አብረው የሚወስኑና ጉዳት የደረሰበት ሰራተኛ የሚያነሳውን የመብት ጥያቄም ሆነ የሕግ ክርክር ለማፈን በግንባር ቀደምትነት የሚሰለፉ ናቸው።

በስራ ላይ ያለው የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ ለሠራተኞች መብት መከበር በቂ ዋስትና የማይሰጥ መሆኑ ብቻ ሳይሆን የስራ ክርክር ዳኝነት የሚታይበት ተቋም አደረጃጀትና የሰው ኃይል አመዳደብ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ ባለመሆኑ መብታቸውን የሚከላከል ሕጋዊ ስርዓት አለ ለማለት አይቻልም። በስራ ቦታ ላይ ያለውን የኢንዱስትሪ ግንኙነት የሚወስን፣ የሰራተኞችን ማህበራዊ ደህንነትና የግል ነፃነት የሚጠብቅ፣ በአሰሪ ኩባንያዎችና ተቋሞች ውሳኔ አሰጣጥ ላይ በሁሉም ጉዳዮች የሰራተኛ ማህበራትን ተሳትፎ የሚያረጋግጥ፣ ዴሞክራሲያዊ ሁኔታዎችን የሚፈጥርና በስራ ቦታ መኖር ለሚገባው የኢንዱስትሪ ሰላም የሚመች የአሰሪና ሰራተኛ ሕግ የለም።

እያንዳንዱ ሰራተኛ በግልፅ የተቀመጡ መብቶች እንዲኖሩት ያስፈልጋል፡፡ ከስራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ባላቸው ጉዳዮች ላይ መረጃ እንዲሰጠውና አስተያየቱን እንዲገልፅ መብት ሊኖረው ይገባል፡፡ አሰሪው ተቋም አዲስ ቴክኖዎሎጂ ጥቅም ላይ ቢያውል በስራው ላይ ምን ጉዳት ወይንም ምን ጥቅም እንደሚያስከትል ጠይቆ የመረዳት መብት ሊሰጠው ይገባል፡፡ የግል ማህደሩን ለማየት መብት እንዲኖረው ያስፈልጋል፡፡ የስራ አፈፃፀም ግምገማና የክፍያ ሰነዶችን በሚመለከት ማወቅ የሚፈልገውን ጉዳይ ለመጠየቅና መልስ ለማግኘት መብት ሊኖረው ይገባል፡፡

ከአሰሪዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ጥቅማቸውን የሚያስከብርና የሚወክል ነፃ የሰራተኛ ምክር ቤት የማቋቋም መብት ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የሰራተኛ ምክር ቤት አባላት በሰራተኞች ድምፅ በነፃ ምርጫ የሚወከሉ መሆን አለባቸው፡፡

የሠራተኛ ምክር ቤቱ ከብዙዎቹ ተግባሮቹ ውስጥ በሰራተኛው ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሕጎችና ደንቦች፣ የአደጋ መከላከያ ድንጋጌዎች፣ የሕብረት ስምምነቶች፣ የስራ ሁኔታዎች ወዘተ. በሕጉ መሰረት መሟላታቸውን ማረጋገጥ ዋነኞቹ ናቸው፡፡ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ በሚደረግ የሰራተኞች ጠቅላላ ስብሰባ ስለስራው ሪፖርት በማቅረብ፣ ውይይት እንዲካሄድ፣ በምክር ቤቱ ውሳኔ ላይ ትችት እንዲሰጥና ሰራተኞች የራሳቸውን አስተያየት እንዲያሰሙ ማድረግ ይኖርበታል፡፡

በርካታ ቁጥር ያላቸው ሰራተኞች በሚሰሩበት ተቋም በኢኮኖሚ ጉዳዮች ላይ ሰራተኞች መረጃ እንዲኖራቸው የሚያስችል የምክር አገለግሎት የሚሰጥ የኢኮኖሚ ጉዳይ ኮሚቴ ማደራጀት ያስፈልጋል፡፡ የዚህን ኮሚቴ አባላት የሰራተኛ ምክር ቤቱ እንዲመርጣቸው ማድረግ ይቻላል፡፡ የሰራተኛ ምክር ቤቱ አባላት ቁጥር በዛ ያለ ከሆነ የምክር ቤቱን የእለት ከዕለት ስራ የሚከታተሉ ሰዎች ያሉበት ኮሚቴ ማቋቋም ይቻላል፡፡ የሰራተኛ ምክር ቤቱ አባላት ውክልና እንደሰራተኞች ብዛት ተመጣጣኝ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ በተወሰኑ ጉዳዮች የሰራተኛ ማህበር ተወካዮች የበላይ አመራሮች የሰራተኛ ምክር ቤቱን ስብሰባ እንዲከታተሉ ማደረግ ይቻላል፡፡

ጠቃሚ ከሆኑት የጋራ ውሳኔዎች መካከል የኩባንያዎች አደረጃጀት፣ የስራ ሰዓት፣ የትርፍ ጊዜ ስራ፣ የበዓላት ሁኔታ፣ ለየስራ ዘርፉ ለካምፓኒው ወይም ለተለያዩ ምድቦች የተወሰኑ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ በስታፍ ባህርይና አፈፃፀም ላይ የሚደረግ ቴክኒካዊ ቁጥጥር፣ ከስራ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የጤና ችግሮችና በሕግ የተቀመጡ የጤና ዋስትናዎች፣ የሠራተኞች መኖሪያ ቤቶች፣ የክፍያ መዋቅር፣ የቁርጥ ስራና የቦነስ አሰጣጥ ወዘተ. የመሳሰሉት ይገኙበታል፡፡ ተቋሙ ስራውን ለመቀነስ፣ ለመዝጋት ወይም ወደሌላ ቦታ ለማዛወር ወዘተ. የሚያስችል የለውጥ ሀሳብ ካለው በዚህ ምክንያት የሰራተኞች ጥቅም ጉዳት የማይደርስበትን ተስማሚ ዘዴ በማቀድ የስራ ምክር ቤቱ ጠቃሚ ሚና መጫወት አለበት፡፡ እንደቅጥር ምደባና ዝውውር የመሳሰሉ ሰራተኛን የሚመለከቱ ጉዳዮች ሲፈፀሙ አሰሪዎች የስራ ምክር ቤቱን ይሁንታ በቅድሚያ የሚያገኙበት አሰራር መኖር አለበት፡፡ የስራ ምክር ቤቱን ይሁንታ ሳያገኙ ለመፈፀም ከፈለጉ በስራ ዳኝነትና ፍ/ቤት ማስወሰን ይገባቸዋል፡፡ ሰራተኛን ከማባረራቸው በፊትም የስራ ም/ቤቱን ይሁንታ ማግኘት አለባቸው፡፡ የስራ ምክር ቤቱ ካልተስማማ የተባረረው ሰራተኛ ወደስራ መመለስ ይኖርበታል፡፡ ጉዳዩ ለስራ ፍ/ቤት ቀርቦ መወሰን የሚገባው ሲሆን አሰሪዎች የፍርድ ቤቱ ውሳኔ እስኪያገኝ ድረስ ሰራተኛውን በስራ ላይ የማቆየት ግዴታ አለባቸው፡፡

የሰራተኞች የጋራ ውሳኔ የስምምነት (የድርድር) ዴሞክራሲ አካል ነው፡፡ ዴሞክራሲያዊ ሕጋዊነት በመንግስት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች መፈፀም ይገባቸዋል ከሚል መሰረተ ሀሳብ የሚነሳ ነው፡፡ የገበያ ጉዳይ ይሁን፣ ምርትን የማሳደግ ወይም ኢንቨስትሜንትን የማስፋፋት ወዘተ. ምንም ይሁን ምን ማንኛውም የስራ ተቋም ውሳኔ በሰራተኞቹ ላይ የተወሰነ ውጤት አለው፡፡ በመሆኑም ሰራተኞች በስራ ተቋሞች ውሳኔ ላይ በተወካዮቻቸው አማካይነት ሀሳባቸውን መስጠት አለባቸው፡፡ በዝቅተኛ፣ በመካከለኛና ከፍተኛ የስራ ተቋሞች በሚወጡ ፖሊሲዎች ላይ የሰራተኞች ተወካዮች ተፅዕኖ እንዲያደርጉ የሚያስችል አሰራር መኖር አለበት፡፡ የዚህ ዓይነቱ የጋራ ውሳኔ በማህበራዊ ጉዳዮች ብቻ የሚወሰን ሳይሆን

በሁሉም የተቋሞቹ እንስቅሳሴዎች ተግባራዊ መሆን አለባቸው፡፡ የዚህን ተግባራዊነት የቁጥጥር ቦርዱ ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡ የቁጥጥር (የግምገማ) ቦርዱ የስራ አመራር ቦርዱን መመደብ፣ ማባረር፣ ስለሁሉም የተቋሙ ጉዳዮች የመጠየቅ፣ ወሳኝ የሆኑ የኢንቨስትሜንትና የአፈፃፀም መለኪያዎችን የመወሰን (ይሁንታ መስጠት) የመሳሰሉ ኃላፊነቶች ያሉት ነው፡፡ የጋራ ውሳኔን የሚመለከት ሕግ ወጥቶ በስራ ላይ እንዲውል ማድረግ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው፡፡ የቁጥጥር (የግምገማ) ቦርድ ከአሰሪዎችና ከሠራተኞች በሚመረጡ አባላት የሚቋቋም ሲሆን ሁለቱም በእኩል ቁጥር እንዲወከሉ ያስፈልጋል፡፡ የቁጥጥር ቦርድ አባላትና የሰራተኛ ማህበር አባላት ምርጫ ሰራተኞች በሚወስኑት መሰረት በግልፅ ምርጫ ስርዓት እንደ አባሎቻቸው መጠን ተመጣጣኝ ውክልና በሚያስገኝ መንገድ መሰራት አለበት፡፡ በዚህ መልክ ያሰሪና የሠራተኛን ጥቅምና ፍላጎት በመግባባት መንፈስና ደንብን በተከተለ አሰራር በማቻቻል ለኢኮኖሚ እድገት ምቹ ሁኔታ የሚጥር የኢንዱስትሪ ሰላም መግኘት ይቻላል፡፡

# 3. ማዕድንና ኢነርጂ

አገራችን በርካታ የማዕድን ክምችት ያላት ቢሆንም የኢኮኖሚ አቅማችንና በሀገራችን አንዳንድ ቦታዎች ያለው የጂኦሎጂ አወቃቀር ይኸንን ክምችት ለማውጣት የሚያስችል አይደለም፡፡ ማዕድንን መፈለግ፣ ማውጣትና በጥቅም ላይ ማዋል እጅግ ውድ ከመሆኑ ሌላ ከፍተኛ የኢኮኖሚ አቅም፣ የእውቀት ደረጃ፣ የቴክኒዎሎጂ ብቃትና ረጅም ጊዜ ስለሚጠይቅ አሁን ላለብን አጣዳፊ ችግር ቶሎ የሚደርስ አይደለም፡፡ በጥቅም ላይ መዋል የጀመሩትንም ከፍተኛ የአየር ብክለት፣ የአካባቢ መጎዳትና የሰዎች መፈናቀል በማያስከትል መንገድ ከመጠቀም በተጨማሪ ጥራት ያላቸውና ተወዳዳሪ ሆነው እንዲመረቱ ከፍተኛ ጥንቃቄና አቅም ስለሚጠ ይቁ ወጪያቸውንና ጥቅማቸውን የማመጣጠን ችግር አለ፡፡ ይኸንን ሁኔታ ለመቀየር መሰረታዊ ችግሮቻችንን ለመፍታት የሚረዱትን፣ ተመጣጣኝ በሆነ ወጪ የሚለሙትን፣ በቀላሉ ገበያ የሚያገኙትና አዋጭነት ያላቸውን እየመረጡ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

በኢነርጂ በኩል ያለው ሁኔታም ከዚሁ ጋር የሚቀራረብ ነው፡፡ ሀገሪቱ ለጉልበት ምንጭ የሚሆን ከፍተኛ የውሃ ሀብት ቢኖራትም በጥቅም ላይ ለማዋል የአቅም ችግር አለባት፡፡ አሁን ያለውን የኢነርጂ መጠን ማሻሻል እስኪቻል ድረስ አጠቃቀሙን ፍትሃዊ ማድረግና በቁጠባ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን መስራት ይጠይቃል፡፡ ጥቅም ላይ ያልዋለውን የኢነርጂ ክምችት መጠ ቀም እስኪቻል፣ ተጨማሪ አቅም እሰኪፈጠርና በቂ መጠባበቂያ እስኪኖር ድረስ አማራጭ የኢነርጂ ምንጮችን መጠቀም እንዲሁም እንደአስፈላጊነቱ ፍጆታን መቀነስ ይገባል፡፡ በጥቅም ላይ የዋለውን እንደገና መልሶ መጠቀም የሚቻልበትን መንገድ መፈለግ ሌላው ዘዴ ነው፡፡

ከሁሉም በላይ የአካባቢን ደህንነት የማይጎዳና ለአካባቢ ተስማሚ የሆነ የኢነርጂ አጠቃቀም ስርዓት መኖር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መስክ የግል ባለሀብቶች እንዲሳተፉ ማድረግ ለአገልግሎት ጥራት አስተማማኝነትና ለተጠቃሚው ቀልጣፋ አገልግሎት ለመስጠት ወሳኝ ነው፡፡ የመንግስት ተግባርና ኃላፊነት ደግሞ ለዚህ አገልግሎት ውጤታማነት የሚረዱ ሕጋዊ ስርዓቶችን ማውጣት ነው፡፡ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለአስቸኳይ ጊዜ መጠባበቂያና ለኢነርጂ ስርጭት ቀውስ መከላከያ ሕጎችን ማውጣትና በስራ ላይ ማዋል የመንግስት ተግባር ነው፡፡ የተረጋጋ የኢነርጂ ስርጭትና ዋጋ መኖሩን ማረጋገጥ የመንግስት ኃላፊነት ነው፡፡

የኢነርጂ አቅርቦት አስተማማኝ እንዲሆን፣ በቁጠባ ጥቅም ላይ እንዲውልና አማራጭ የኢነርጂ ምንጮች እንዲፈጠሩ ማድረግ የመንግስት ግዴታ ነው፡፡

## 3.1 የማዕድን ሀብት ልማት

የማዕድን ሀብት ለኢንዱስትሪው መስፋፋት እንዲያግዝና የውጭ ምንዛሪ ለማዳንና ለማፍራት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ለማድረግ ያስችላል፡፡ ሆኖም ይህንን ሀብት አጠቃቀም ተገቢ ግምት የሚሰጥ እንቅስቃሴ ባለመደረጉ በአጠቃላይ ኢኮኖሚው ሊኖረው የሚገባውን ሚና ሊጫዎት አልቻለም፡፡ የማዕድን ዘርፉ የውጭ ምንዛሪ ማዳንና ማፍራት፣ ሠፊ የሥራ ዕድል በመፍጠር ለአገር ውስጥ

ኢንዱስትሪዎች ጥሬ ዕቃ ማቅረብ የመሳሰሉትን አስተዋጽኦ በበቂ ደረጃ ሊያበረክት አልቻለም። በመሆኑም በማዕድን ሀብታችን ግብዓትነት ሊመረቱ ይችሉ የነበሩ ቁሳቁሶችን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ እየወጣ ነው። ውስን የግብርና ውጤቶችን ወደ ውጭ አገር በመላክ የሚገኘውን የውጭ ምንዛሪ በሌሎች ሀብት ፈጣሪ በሆኑ የኢኮኖሚ ዘርፎች ላይ እንዳይውል ተሻምቷል። የማዕድን ዘርፍ ለአገራችን ኢኮኖሚ አስፈላጊውንና የሚገባውን አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ከኢንዱስትሪ ልማት ጋር የማዕድን ልማትን በማጣጣም አጋዥነቱን ለማረጋገጥ መጣር ተገቢ ነው።

የኢትዮጵያን የሥነ ምድር ሁኔታ መሠረት በማድረግ አገሪቱ ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የማዕድን ሀብት እንዳላት ቢገመትም ጥቅም ላይ የዋሉት በጣም ጥቂቶቹ ሲሆኑ እስካሁን የተካሄዱ የማዕድን ልማት ሥራዎች በአመዛኙ በወርቅ ላይ ያተኮሩ ሆነው ቆይተዋል። የአገሪቱ የማዕድን ሀብት ልማት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በመሆኑ ክፍለ-ኢኮኖሚው ለጠቅላላ ዓመታዊ የአገር ውስጥ ምርት የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከሁለት በመቶ አይበልጥም። ለዚህ ከሚጠቀሱ ምክኒያቶች ውስጥ የማዕድን ሀብታችንን ለማልማትና በጥቅም ላይ ለማዋል ያለው የኢንቨስትሜንት አቅምና የሳይንስና ቴክኖሎጂ መሠረት ደካማ መሆን፣ የአገር ውስጥ የማዕድን ጥሬ ዕቃ ፍላጎት ውስን መሆንና በዘርፉ ያለው የመረጃ ሀብት መጠንና ጥራት ደካማ መሆን ዋና ዋናዎቹ ናቸው። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ለኮንስትራክሽን ሥራዎች፣ ለሴራሚክስ፣ ለሲሚንቶ፣ ለመሥታዎት ሥራዎችና ለማዳበሪያ ማምረቻ በጥሬ ዕቃነት ሊያገለግሉ የሚችሉ ማዕድናት እንዳሉ ይታወቃል። በአገሪቱ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ በኢነርጂ ምንጭነት የሚያገለግል ከፍተኛ የከርሠ ምድር እንፋሎት ክምችትና በኦጋዴን አካባቢ ከፍተኛ የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት መኖሩ ተረጋግጧል። እንዲሁም የነዳጅ ዘይት መኖርን የሚያሳዩ አንዳንድ ምልክቶች እንዳሉ ጥናቶች ያመለክታሉ።

በአገራችን አሉ ከሚባሉት በስፋት ከሚገኙ ማዕድኖች አንዱ ጨው ነው። የጨው ምርት ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች ካሉት ጥቅሞች በተጨማሪ ሶድየም ሰልፌት የሚባል በተለይም ለወረቀት ሥራ ወሳኝ የሆነ ኬሚካል ለማምረት ያስችላል። በጨው ምርት ራሳችንን ከመቻላችንም በላይ ለተለያዩ አገልግሎቶች በሚውል የወረቀት ምርትም ራሳችንን እንድንችል ይረዳል።

የብረት ማዕድን በበቂ መጠን በአገራችን እያለ፣ እስካሁን የብረት ፍላጎታችንን ማለትም ላሜራ፣ ብረት ዘንግና የመሳሰሉትን በብድርና በእርዳታ ከምናገኘው የውጭ ምንዛሬ እያሟላን ነው። በቂ ኢነርጂ የማምረት እምቅ ሀብታችንን ተጠቅመን በርካሽ ማቅለጥ ከቻልን የዚህ ሀብት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል።

ከዚህ ሌላ በተለያዩ አካባቢዎች የሚገኙ እንደ ወርቅ የመሳሰሉ ማዕድናት አዋጪ በሆነ የማምረት ዘዴ ተጠቅሞ በማምረት አሁን ካለው የበለጠ ተጨማሪ የውጭ ምንዛሪ ለማፍራት ይቻላል።

## 3.2 የኢነርጂ ሀብት ልማት

ኢነርጂ ለኅብረተሰቡ ሕልውናና ለኢኮኖሚ ልማት መሠረት ነው። ኢትዮጵያ በጥቅም ላይ የዋሉና ያልዋሉ፣ መኖራቸው የተረጋገጠላቸውና ፍንጭ የታየባቸው ታዳሽና አላቂ የኢነርጂ ሀብት አለኝታዎች አሏት። የሰውና የእንስሳት ጉልበት ሳይታከል 94 በመቶ የሚሆነው የኢትዮጵያ የኢነርጂ ፍላጎት የሚሟላው ከባህላዊ የኢነርጂ ምንጮች ማለትም ከእንጨት፣ ከእንስሳት ፍግና ኩበት፣ ከእርሻ ቃርሚያና ከመሳሰሉት ሲሆን ቀሪው 6 በመቶ ደግሞ ከዘመናዊ የኢነርጂ ምንጮች ማለትም ከነዳጅ ዘይት፣ ጋዝና ኤሌክትሪክ ኃይል የሚሟላ ነው። በአገሪቱ ከፍተኛ የኢነርጂ ተጠቃሚ የቤተሰብ አግልግሎት ዘርፍ ነው። ዘርፉ ከአጠቃላይ የኢነርጂ አቅርቦት ውስጥ ከ85 በመቶ በላይ የሚሆነውን የሚጠቀም ሲሆን ይህም አብዛኛው የአገሪቱ የኢነርጂ አቅርቦት ለልማት እንደማይውል ያመለክታል። በአገሪቱ ሚዛናዊ የኢነርጂ ሀብት ልማት ባለመኖሩ የባህላዊ የኢነርጂ ምንጮች ላይ ያለው ጥገኝነት ለደን መራቆት፣ ለአፈር ልምላሜ መቀነስ፣ ለማገዶ እንጨት እጥረትና ዋጋ መናር የበኩሉን አስተዋጽኦ ያደርጋል። ዘመናዊ የኢነርጂ ምንጮች ለአጠቃላይ የኢነርጂ አቅርቦት ያላቸው ድርሻ ዝቅተኛ ይሁን እንጂ አቅርቦታቸው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪን የሚጠይቅ ነው። የአገሪቱ የኢነርጂ ችግር የተወሳሰበ፣ በሌሎች ክፍለ-ኢኮኖሚዎች እንቅስቃሴና በኅብረተሰቡ አኗኗር ወሳኝ ተፅዕኖ የሚያሳድርና

አፋጣኝ እስተራክቸራል ለውጥ ካልታየበት እየተባባሰ ወደሚሄድ ቀውስ የሚያመራ እንደመሆኑ ለዘርፉ ልዩ ትኩረት የሚሰጥ አግባብነት ያለው ፖሊሲ ያስፈልገዋል።

በ1992 ዓ.ም የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካ አገሮችን በነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ኃይል ፍጆታን (በሚሊዮን ኪሎ ዋት/በሰዓት) በንጽጽር ማየት በኢነርጂው መስክ ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል። በኢትዮጵያ 22.2 ብቻ ሲሆን በኬንያ 129.5፣ በግብፅ 861.1 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 534.6 ነው። ኢትዮጵያ ከሁሉም ወንዞቿ 410 ሜጋ ዋት የውሃ ኤሌክትሪክ ስታመነጭ ግብፅ ግን ከናይል ብቻ አሥር ሺህ ሜጋ ዋት ታመርታለች፤ ማለትም የግብጽ ምርት የኢትዮጵያን 24 ጊዜ ነው ማለት ነው።

ኢትዮጵያ በመሬት አቀማመጧና ባላት የውሃ ሀብት ምክኒያት እጅግ በጣም በርካታ የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት የሚያስችሉ ፕሮጀክቶችን ለመገንባት ተስማሚነት ያላቸው ብዙ አካባቢዎች አሏት። እስከ አሁን ድረስ በሥራ ላይ ከዋሉት ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች ቆቃ፣ ፊንጫ፣ መልካ-ዋከናና አባይ ፏፏቴ ሲሆኑ የግልገል ጊቤ ችሮጀክቶችም በቅርብ ጊዜ ሥራ እንደሚጀምር ይገመታል። የጎጀብና የተከዜ ፕሮጀክቶችም በቅርብ ጊዜ ተገንብተው አገልግሎት እንደሚሰጡ ይጠበቃል። እነዚህ የኤሌክትሪክ ማመንጫዎች የሚሰጡት የኢነርጂ መጠን በአጠቃላይ ከኢትዮጵያ ሊገኝ ከሚችለው ኢነርጂ ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። እስካሁን ድረስ በተደረጉ ግርድፍ ጥናቶች በተለያዩ ተፋሰሶች በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ የውሃ ኢነርጂ ማመንጨት እንደሚቻል ተጠቁሟል። እስካሁን ድረስ ማልማት የተቻለው ከሁለት በመቶ ያነሰ ነው።

የውሃ ሀብታችንን ተጠቅመን የኤሌክትሪክ ኃይል በብቃት ልናመነጭ ባለመቻላችን እየተጎዳን ነው። አማራጭ ኢነርጂ በማቅረብ የደኖቻችንን መጨፍጨፍ መግታት አልቻልንም። በቂ የኤሌክትሪክ ኃይል በማቅረብ ለኢንዱስትሪ መስፋፋት አመቺ ሁኔታ መፍጠር ይቻላል።

# 4. ንግድና ፋይናንስ

## 4.1 ንግድ

የንግድ እንቅስቃሴ በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ አስተዋፅኦ እንዳለው የታወቀ ነው። ብዙ የሰው ኃይል በዚህ የኢኮኖሚ መስክ ተሰማርቶ ሕይወቱን ይመራል። የንግድ ባለሀብቱ ብቻ ሳይሆን በመስኩ ተሰማርቶ እውቀቱንና ጉልበቱን እየሸጠ የሚተዳደረው ብዙ ነው። በሀገሪቱ ውስጥ በስራ ክፍፍል ላይ የተመሰረተ ዘመናዊ አኮኖሚ እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋፅኦ እያደረገ ነው። አምራቹን፣ ሻጩንና ገዥውን የማገናኘት ሚና ይጫወታል። ምርትና አገልግሎትን የማሰራጨት ትልቅ ተግባር ያከናውናል። ጅምላ ነጋዴው የንግድ እቃዎችን ለሌሎች ነጋዴዎች፣ አምራቾች፣ የኢንዱስትሪ ተቋሞች፣ በሰፊው ለሚጠቀሙ ድርጅቶችና ግለሰቦች ያቀርባል። ለማምረቻ ድርጅቶች የካፒታል ሸቀጦችን፣ ጥሬ እቃዎችንና ሌሎች ለምርት ስራ የሚያገለግሉትን ያቀርባል። ለቸርቻሪዎችም በቀጥታ ለተጠቃሚው ሊደርሱት የሚችሉትን እቃ ያቀርባል።

በችርቻሮ ንግድ የተሰማራው ደግሞ በምርትና አገልገሎት ስርጭቱ ስርዓት ውስጥ ከተጠቃሚው ጋር በቀጥታ የሚያገናኝ የመጨረሻው ድልድይ እንደመሆኑ በሚያቀርበው ምርትና አገልገሎት ዓይነት፣ በአቀራረቡ ጥራትና በአሰራሩ ቅልጥፍና የማያቋርጥ መሻሻልና እድገት ማሳየት ይጠበቅበታል። ለዚህ ሁኔታ መሟላት አንዱ ጠቃሚ ዘዴ በውድድር ሕግ እንዲሰራ ማድረግ ነው። በችርቻሮ ነጋዴዎች መካከል ውድድር በሚኖርበት ጊዜ አነስተኛ በሆነ ትርፍ ለገዥው ሕብረተሰብ ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለማቅረብ ያስችላል። ተገልጋዩ ሕዝብ ራሱ በራሱ እንዲጠቀም በሚያስችለው መንገድ አውቶሜትድ ማድረግ፣ የዋጋ ቅናሽ ማድረግ፣ ተጠቃሚው የሚፈልገውን አይነት ምርትና አገልግሎት ለይቶ ማቅረብ፣ ምርትና አገልግሎትን በሰፊው ማቅረብ፣ የሞያተኛ ምክር መጠቀምና የመሳሰሉት ዘዴዎች በውድድሩ ውስጥ ለመቆየትና ውጤታማ ለመሆን የሚያስችሉ አማራጮች ሲሆኑ እንዲህ ዓይነት ውድድር ሲኖር ተጠቃሚው የተሻለ ጥራትና ብቃት ያለው አገልግሎት ለማግኘት ይችላል። በእርግጥ አገልገሎቶችን አውቶሜትድ ማድረግና ተጠቃሚው ራሱን በራሱ እንዲረዳ ማድረግ ጥቅም እንዳለው ሁሉ የነጋዴውን ወጪ ከፍ በማድረግና ተጨማሪ የስራ እድል እንዲኖር በመገደብ

*አሉታዊ ውጤትም ስለሚያስከትል ጥቅሙንና ጉዳቱን እያመዛዘኑ መስራት ያስፈልጋል:: በውድድሩ ውስጥ አነስተኛና መካከለኛ በሆነ ችርቻሮ የተሰለፉት ከፍተኛ አቅም ባላቸው እየተገፉ በቀላሉ ከጨዋታ ውጭ እንዳይሆኑ በመንግስት በኩል የቴክኒክ፣ የምክርና የብድር አገልግሎት ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል::*

*ከዚህ በተጨማሪ የችርቻሮ ንግድ ማህበራትን በመመስረት የአነስተኛ ነጋዴዎች ሕልውና እንዲጠበቅ ማድረግም ይገባል:: ለሀገራችን ልማትና ለሕዝቡ ሕልውና አስፈላጊ የሆኑትን ምርቶችና አገልግሎቶች የማምረትና የማቅረብ አቅማችን ዝቅተኛ በመሆኑ የአለም አቀፍ ንግድ ጥገኞች መሆናችን የታወቀ ነው:: ይኸንን ፍላጎታችንን ለማሳካት ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሰላማዊ ትብብር መመስረትና በአለም አቀፉ ኢኮኖሚያዊ ትስስር ውስጥ ስፍራ እንድናገኝ ያላሰለሰ ረት ማድረግ ይኖርብናል:: እንደእኛ ያለ ድሃ ሀገር የንግድ መርሆዎቻችን ራስ ቻይነትን ከአለም አቀፉ የስራ ክፍፍል ጋር፣ የንግድ ቀጥጥርን ከአለም አቀፉ የውድድር ስርዓት ጋር፣ የኢኮኖሚ ነጻነትን የጋራ ጥቅምን ከማቻቻል ጋር ያቀናጁ መሆን ይኖርባቸዋል:: አንዱን ከሌላው ነጥሎ ለማራመድ መሞከር ችግራችንን ይበልጥ የሚያባብስ እንጂ የሚያሻሽል አይሆንም:: የራሳችንን ጥቅም ከወቅቱ የንግድ ፍልስፍናና ስርዓት ጋር ለማቻቻል በመጣር በአንድ በኩል ጥቅማችንን ሙሉ በሙሉ አሳልፎ ላለመስጠት በሌላ በኩል ደግሞ ከዓለም አቀፉ የንግድ ስርዓት ጨዋታ ውጭ ላለመሆን እንደሁኔታው ሊለዋወጥ የሚችልና በተቻለ መጠን ተጠቃሚነታችንን የሚያሳድግ የተጠና ፖሊሲ ሊኖረን ይገባል::*

*ሕገወጥ ንግድን በጥብቅ መከላከል፣ ከማምረቻ ዋጋቸው በታች የሚሸጡና ተገቢውን የጥራት ደረጃ የማያሟሉ የውጭ ምርቶች እንዳይገቡ መቆጣጠር ያስፈልጋል:: ምንም እንኳ ከፍተኛ እውቀት ያለው የሰው ኃይል፣ ከፍተኛ የፋይናንስ ወጪ፣ ብቃት ያለው የአመራረት ስርዓትና ረጅም ጊዜ የሚወስድ ቢሆንም የገቢና ወጪ ንግድ ሚዛናችንን ለመጠበቅ በሚያስችል አቅጣጫ የተቃኘ የንግድ ፖሊሲ ማራመድ ይገባል:: የኤክስፖርት አይነትና መጠን በማያቋርጥ ሁኔታ እንዲያድግ፣ የገቢ ንግዳችን ደግሞ እጅግ መሰረታዊና አስፈላጊ በሆኑት ላይ ያተኮረ እንዲሆን ለማድረግ ከፍተኛ ጥረት ማሳየት ይኖርብናል:: የገቢ ንግዳችን በቅንጦት እቃዎችና ጥራት በሌላቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ላይ እንዳይውልና ለሌላ መሰራታዊ ተግባር የሚያስፈልገንን ውስን የውጭ ምንዛሬ እንዳይሻማ የተለያዩ መከላከያዎችን መጠቀም ይገባናል:: በሂደት ኤክስፖርታችን ከገቢ ንግዳችን እንዲበልጥ ከፍተኛ ርብርብር ማድረግ አለብን:: የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶች የማሟላቱ ስራ በገቢና ወጪ ንግድ ሚዛን አጠ ባበቅ ወሳኝ እንደመሆኑ የሀገር ውስጥ ምርቶችና አገልግሎቶች ጥራትና መጠን እንዲያድግ፣ ለተጠቃሚው የተሟላ መረጃ እንዲሰራጭና በሰፊው ለሽያጭ እንዲቀርብ ነጋዴው ሕብረተሰብና መንግስት በቅንጅት መስራት አለባቸው:: ከኤክስፖርት የሚገኘው ጥቅም እንዲያድግ ከተፈለገ ጥሬ እቃና በአብዛኛው የተወሰነ ዓይነት የግብርና ምርት አቅራቢ የሆነበትን ሁኔታ ለመለወጥ ጥረት ማድረግ ይገባናል:: ኤክስፖርት የምናደርገውን አይነት ማብዛት፣ ጥራቱን መጨመር፣ ያለቀለት አድርጎ ወይም በከፊል ያለቀለት* (processed of semi-finished) *አድርገን፣ አጣርተንና አሽገን የምንልክበትም መንገድ መፈጠር አለበት:: ከኤክስፖርት የሚገኘውን የውጭ ምንዛሬ ለዘላቂ እድገት በሚጠቅም አግባብና በቁጠባ መጠቀምም ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ መገንዘብ ያስፈልጋል::*

*እንደዚህ ዓይነት ዘዴዎችን እየተጠቀምን በመስራት በአለም ገበያ ውስጥ ቦታ የምናገኝበትን መንገድ ማፋጠን ይገባል:: የንግድ አጋሮቻችንን ማብዛት ለኤክስፖርት ንግዳችን ማደግ አንድ ጠቃሚ ነገር ነው:: አጋሮቻችን እንዲበዙ ነፃ ገበያን፣ በሚገባ የሚያሰራ የገንዘብ ስርዓት፣ የተረጋጋ የፖለቲካ አመራርና መልካም አስተዳደር፣ ነፃ የፍትህ ስርዓት፣ በጋራ ጥቅም መርህ የተመሰረተ የዲፕሎማሲ ግንኙነት የመፍጠር ግዴታና ኃላፊነት አለብን:: ለኢንቨስትሜንት መስፋፋት የሚያግዝ፣ ትርፋማነትን፣ የስራ እድልንና የኑሮ ሁኔታን የሚያሻሽል ፖሊሲና ግልፅ የንግድ ስርዓት ከሌለ የኤክስፖርት ንግድን ማሳደግ አይቻልም:: የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በጋራና በተናጠል ካፒታላቸውን ኢንቨስት እንዲያደርጉ የሚያስችል ፖሊሲና አሰራር ሲኖር በተለይ የውጭ ባለሀብቶችን እውቀትና ልምድ ለመቅሰም፣ የቴክኒዎሎጂ ሽግግር እንዲኖር ይረዳል:: ለውጭ ምንዛሬ እድገት፣ ለካፒታል ምስረታ፣ ለስራ እድል መስፋፋት፣ የሀገር ውስጥ ፍላጎትን ለማሟላትና ለዘላቂ እድገት መሰረት ለመጣል ወዘተ. በአለም አቀፉ የንግድ ሥርዓት ውስጥ ቦታ የሚያስገኝልን የኢንቨስትሜንትና የኤክስፖርት ፖሊሲ ሊኖረን*

ይገባል፡፡ ለዚህ እንቅስቃሴ የሚያግዝ የንግድ ትርኢትና ኤግዚቢሽን በሀገሪቱ ማዘጋጀትና በሌሎች ሀገሮች በሚደረጉት ደግሞ የነቃ ተሳትፎ ማድረግ ከሌሎች ጋር ለመገናኘትና ያለንን መልካም ነገር ለማስተዋወቅ ያስችላል፡፡ በዚህ ረገድ የንግድ ምክር ቤቶች የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መሆን አለበት፡፡ በመንግስት በኩልም ለም/ቤቶቹ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

## 4.2 **ባንክና ፋይናንስ**

የሀገሪቱ ከረንሲ ለረጅም ጊዜ የተረጋጋ ሆኖ እንዲቀጥል በማድረግ ጤናማ የኢኮኖሚ ሁኔታ መፍጠር አስፈላጊ ነው፡፡ ከፌዴራል መንግስት ተፅዕኖና ቁጥጥር ነፃ ሆኖ የሚሰራ የፌዴራል ባንክ እንዲኖር በማድረግ የሀገሪቱ የፋይናንስ ስርዓት በነፃ ገበያ ሕጎች እንዲገዛና በዚሁ አቅጣጫ እንዲቃኝ ማስቻል ይገባል፡፡ እንደዚህ ዓይነት በነፃነት የሚሰራ የፌዴራል ባንክ ሲኖር በገበያ ሕግ የሚመራ የገንዘብና የብድር ፖሊሲ ለማውጣትና በስራ ላይ ለማዋል ይቻላል፡፡ የራሱን አስተዳደርና አመራር አጠቃላይ አቅጣጫ በነፃነት የሚወስን፣ የባንክ ኖቶችን የሚያትም፣ በዝውውር ላይ መዋል የሚገባውን የገንዘብ መጠን፣ ለአምራቾች አገልግሎቶች ብድር የሚቀርበውን የገንዘብ ልክ ወዘተ. የመወሰን ስልጣን ያለው የፌዴራል ባንክ ሲኖር ከገበያ ሕጎች ጋር የሚጣጣም የፋይናንስ ፖሊሲ ማውጣት ይቻላል፡፡ ነፃና በሕግ የሚመራ የውስጥና ዓለም አቀፍ የባንክ ክፍያ ልውውጥ እንዲኖር የዚህ ዓይነቱ ነፃነት ያለው ብሔራዊ ባንክ ያስፈልጋል፡፡ በዚህ መንገድ የተደራጀና የሚሰራ የፌዴራል ባንክ ሀገሪቱ እንዲኖራት ማድረግ ከተቻለ ለልማትና ለኢኮኖሚ እድገት መረጋገጥ ዋስትና የሚሆን የፋይናንስ ስርዓት ተፈጠረ ማለት ነው፡፡ የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች የሚተማመኑበት የፋይናንስ ፖሊሲ ለማውጣትና ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችል መሰረት ተጣለ ማለት ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት አስተማማኝ ዋስትና መኖሩ ሲረጋገጥ የውስጥና የውጭ ኢንቨስትሜንትን ለመሳብ ሰፊ እድል ይኖራል፡፡ መንግስት እንደፈለገ የሚቆጣጠረውን ተፅዕኖ የሚያደርግበት የባንክ አሰራር ባለበት ሁኔታ ባለሀብቶች እምነት የሚጥሉበትና በኢንቨስትሜንት ስራ በሰፊው ለመሳተፍ የሚደፋፈሩበት መንገድ አይኖርም፡፡ የገበያ ኃይሎችን በመንግስት ትዕዛዝ ብቻ የመወሰን ጣልቃ ገብነት ቢፈጠርና ተገቢ ያልሆነ ኪሣራ ቢደርስ መከላከያ መንገድ ስለሌለ በዚህ አደገኛ ስጋት ውስጥ ገብቶ ለመስራት የሚደፍር ጠንካራ የልማት ኃይል ማግኘት አይቻልም፡፡ በነፃነት ተደራጅቶ የሚንቀሳቀስ ብሔራዊ ባንክ ይኑር ሲባል የሀገሪቱን አጠቃላይ ኢኮኖሚ የሚደግፍና ለኢኮኖሚ እድገት አስፈላጊ የሆነውን የፋይናንስ አቅርቦት በተገቢው ጊዜ፣ ቦታና መጠን የሚያቀርብ ጠንካራ የፋይናንስ ተቋም ይኑር ማለት ነው፡፡

የመንግስት፣ የማህበራትና የግል አበዳሪ ተቋሞች በሰፊው እንዲዘረጉና የብድርና የቁጠባ አገልግሎት እንዲኖር ማድረግ አንድ ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ በእርሻ፣ በኢንዱስትሪ፣ በኮንስትራክሽን፣ በማዕድንና ኢነርጂ፣ በንግድ፣ በአገልግሎትና በመሳሰሉት መስኮች ለሚደረግ ኢንቨስትመንት የብድር አገልግሎት በመስጠት ሳይወሰኑ ዜጎች ለመኖሪያ ቤት ግዥና ግንባታ፣ ለሥልጠናና ለሌላም ተግባር የሚያስፈልጋቸውን ገንዘብ ያበድራሉ፡፡ ገንዘብ ለሚያስቀምጡም የቁጠባ አገልግሎት ይሰጣሉ፡፡ በተለይ የመኖሪያ አፓርታማዎችን፣ የንግድ ማዕከሎችንና የኤግዚቢሽን አዳራሾችን ለሚገነቡ ባለሀብቶች ብድር የሚሰጥ የሞርጌጅ ባንክ በግል ባለሀብቶች እንዲቋቋም ማድረግ በዚህ መስክ ያለውን ችግር በመቀነስ ረገድ ትልቅ አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡ እነዚህን የፋይናንስ ተቋሞች አገልግሎት አሰጣጥ በሚገባ እየገመገሙ ጤናማ የኢኮኖሚ ኃይል እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ባንኮች ለግል ባለሀብቶች ኢንቨስትሜንት የሚሰጡት የብድር መጠን እንዲያድግ ቁጠባን የሚያደፋፍር ፖሊሲም መኖር አለበት፡፡ ከዚሁ ጋር የቁጠባና የብድር ወለድ መጠን ለአስቀማጮችም ሆነ ተበዳሪዎች ጥቅም በሚያስገኝ አግባብ በገበያ ኃይሎች እንዲወሰን ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የገንዘብ ቁጠባ ሥርዓቱ ግለሰቦች ካፒታል እንዲመሰርቱ አስተዋፅኦ በሚያደርግ መንገድ መመራት አለበት፡፡

# 5. ቱሪዝም

ኢትዮጵያ ብዙ ዓይነት ማራኪ የቱሪስት መስህቦች አሏት። የታሪክ፣ የባህልና የተፈጥሮ መስህቦች የሞላባት ሀገር ብትሆንም እነዚህን ለሀገር ውስጥና ለውጭ ጎብኝዎች ክፍት በማድረግ የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ በሚገባ ለማስተዋወቅም ሆነ ለኢኮኖሚው ድጋፍ በሚሰጡበት ሁኔታ ጥቅም ላይ ለማዋል የተጠናከረ ጥረት ባለመደረጉ ከዚህ ዘርፍ የሚገኘው ጠቀሜታ ዝቅተኛ ነው። ከኢትዮጵያ ያነሰ መስህብ ያላቸው የጎረቤት ሀገሮች ለዘርፉ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠታቸው ከሀገራቸው ጠቅላላ ዓመታዊ ገቢ ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆነውን ከቱሪዝም ማመንጨት ችለዋል። የስራ እድል በመፍጠር፣ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ በማስገኘትና ከውጭው ዓለም ጋር ያላቸውን ትስስር በማሳደግ ከቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ጥቅም አግኝተዋል። ይኸንን ዘርፍ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚወጣው ወጪ ሌሎች የኢኮኖሚና የአገልግሎት ዘርፎችን ለማልማት ከሚያስፈልገው መጠን ጋር ሲነፃፀር እጅግ አነስተኛ ነው። እንዲያውም ለሌሎች ዘርፎች ልማት በሚወጣው ወጪ ብቻ ቱሪዝምን መጠቀም ይቻላል። ለእርሻ፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለጤና፣ ለትምህርትና ለመሳሰሉት ዘርፎች የሚሰራ መንገድ፣ ኤሌክትሪክ፣ ስልክ፣ ውሃና ሌላም መሰረተ ልማት መልሶ ለቱሪዝም ልማት ሊውል ይችላል። ለተፈጥሮ ሀብት፣ ለታሪክና ለባህል እንክብካቤና ጥበቃ የሚዘረጋው መሰረተ ልማት ለቱሪዝም እንዲያገለግል በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ማግኘት ይቻላል። የቱሪዝም ዘርፍ በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ ጥቅም የሚያስገኝ ነው።

ጎብኝዎች በታሪክና በባህል ቅርሶች ብቻ ሳይሆን በተፈጥሮ ሁኔታዎችና በሀገሪቱ የመሬት ገጽታም እንደሚሳቡ የታወቀ ነው። ወደእነዚህ ማራኪ የተፈጥሮ መስህቦች የሚደርሱ የመሰረተ ልማት አውታሮች ከሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎች ጋር ተቀናጅተው እንዲሰሩ በማድረግ ከዘርፉ የሚገኘውን ጥቅም ማሳደግ ይቻላል። እስካሁን ድረስ በተነፃፃሪ ደረጃ የተሻለ የቱሪስት አገልገሎት የሚሰጠው ታሪካዊ መስመር በሚገባው በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ነው። በመሀል፣ በደቡብና በምስራቅ የሀገሪቱ ክፍል የሚገኘው ልዩ ልዩ መስህብ ገና በሰፊው ጥቅም ላይ አልዋለም። ሀገሪቱን በሚገባ የሚያስተዋውቁ የቱሪስት መምሪያዎች፣ ብሮሸሮች፣ ፓስት ካርዶች፣ ፖስተሮች፣ ካርታዎች፣ በራሪ ጽሑፎችና የመሳሰሉት በሚገባው ጥራትና መጠን እየተዘጋጁ አይሰራጩም። በዲፕሎማሲ ስራ የሚመደቡ ሰዎች አብዛኞቹ የፖለቲካ ካድሬዎች በመሆናቸው እንደዚህ ላለው የኢኮኖሚ ዘርፍ ያላቸው እውቀት፣ ተነሳሽነትና ትኩረት ዝቅተኛ ነው። በመሆኑም ቱሪስቶችን ለመሳብ የሚሰጡት ጠንካራ ድጋፍ የለም። መንግስት ራሱ ስለዘርፉ ያለው ግምትና አመለካከት ዝቅተኛ በመሆኑ ዘርፉን በሰፊው ጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችል ግልጽ ፖሊሲ የለውም። የቱሪዝምን ዘርፍ የሚመራው ተቋም አደረጃጀት፣ የባለሞያና የበጀት አቅሙ እጅግ ደካማ መሆኑ መንግስት ስለዘርፉ ያለውን ዝቅተኛ ትኩረት የሚጠቁም ነው።

ስለዚህ ኢትዮጵያ ከቱሪዝም ከፍተኛ ጥቅም ለማግኘት የሚያስችል ልዩ ልዩ ዓይነት መስህብ ያላት በመሆኑ ዘርፉ ጠንካራ በሆነ መንገድ እንዲመራ ከፍተኛ ትኩረት መደረግ ይኖርበታል። በመስኩ ለሚሰማሩ የግል ባሀብቶች ተገቢ ድጋፍና ማበረታቻ መስጠት ይገባል። በጉዞ ውክልና፣ በአስጎብኝነት፣ በሳፋሪ አገልግሎት፣ በሆቴሎችና በሌሎችም ለቱሪዝም እድገት በሚጠቅሙ የስራ መስኮች ለሚሰማሩ ባለሀብቶች መንግስት ተጨባጭ ድጋፍ የሚሰጥበትን ግልፅ የፖሊሲ አቅጣጫ ማውጣት ይገባዋል። ከውስጥና ከውጭ ለሚመጡ ቱሪስቶች እንደ ኢኮኖሚ አቅማቸው፣ እንደ እድሜ ሁኔታቸውና እንደየምርጫቸው የሚፈልጉትን መስህብ እንዲጎበኙ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አለበት። ጎብኝዎች በቡድን እንዲንቀሳቀሱ፣ በመስህቦቹ አካባቢ ረዘም ላለ ጊዜ እንዲያሳልፉ፣ በቆይታቸው ወቅት ምቾት እንዲሰማቸውና ደጋግሞ (ተመላልሶ) ለመጎብኘት ፍላጎት እንዲያድርባቸው የተቀናጀ ስምሪት፣ ምቾት ያለው የትራንስፖርትና የሆቴል አገልገሎት፣ የደህንነት ጥበቃና ጥሩ የእንግዳ አቀባበል እንዲኖር የሚያስችል ሁኔታ መፈጠር አለበት። በተለይም የቱርስት መስህብ በሆኑት የሀገሪቱ ከተሞች በከፍተኛ ደረጃ እየተበራከተ የመጣው የለማኞች ቁጥር፣ የስርዓት አልበኛ ወጣት አስጎብኝዎችና የአካባቢ ንፅህና ጉዳይ ልዩ ትኩረትና መፍትሄ የሚያሻው ነው። በተጨማሪም የቪዛና የውጭ ምንዛሬ አገልግሎትን የሚያቀላጥፍ አሰራር መዘርጋት አለበት።

የቱሪዝምን ልማት ከማሳደጉ ጎን ከፍተኛ ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ የአካባቢ ጥበቃ ነው። በየትኛውም ዓለም ከቱሪዝም ጋር የተያያዙ በተለይም ከማስ ቱሪዝም ጋር የተገናኙ የአካባቢ ችግሮች ያጋጥማሉ። የትራፊክ መጨናነቅ፣ የከተሞች መጣበብ፣ የአየርና የውሃ መበከል

በተፈጥሮ አካባቢና በሰው ልጅ ጤንነት ላይ የሚደርሱት ችግር እንዲባባስ ቱሪስቶች የራሳቸውን ጎጂ አስተዋፅኦ እንዳያደርጉ ልዩ ልዩ የመከላከያ ዘዴዎችን ስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል፡፡ በአደን፣ በደን ቃጠሎና በሌሎች ጎጂ ሁኔታዎች የዱር አራዊትና እፅዋት አደጋ እንዳይደርስባቸው የመከላከያ ጥንቃቄዎች መኖር አለባቸው፡፡ ጠቃሚ የባህልና የታሪክ ቅርሶች በስርቆት እንዳይባክኑ፣ ጉዳት እንዳይደርስባቸውና ከሀገር እንዳይወጡ የሚያስችል ግልፅ አሰራር መኖር አለበት፡፡ የዝሙት ቱሪዝም እንዳይስፋፋ፣ አደገኛ እፅ ወደ ሀገር እንዳይገባ፣ ተላላፊ የጤና ችግሮች እንዳይስፋፉ የሚከላከል ስርዓት ማዘጋጀት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢው ሕዝብ ከቱሪዝም ገቢ ራሱ ተጠቃሚ መሆን የሚያስችል አደረጃጀትና አሰራር መፍጠር ይገባል፡፡ እነዚህንና የመሳሰሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ሀገሪቱ በዝቅተኛ ወጪ ከቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ገቢ እንድታገኝ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ ዘርፉ ለውጭ ምንዛሬ መገኘት፣ ለስራ እድል መከፈትና ለሀገሪቱ መልካም ገጽታ መታወቅ እንዲያገለግል በማድረግ ከሀገሪቱ ጠቅላላ አመታዊ ገቢ ያለውን ድርሻ ማሳደግና ጠንካራ የኢኮኖሚ ኃይል እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ለቱሪዝም መስህብነትና ለተፈጥሮ ጥበቃ ትልቅ አስተዋፅኦ ያላቸውን ፓርኮች፣ ጥብቅ ክልሎችና መዝናኛ ስፍራዎች ዘመናዊ የሆነ አደረጃጀትና ቀልጣፋ አሰራር እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል፡፡ በተለይም በፓርኮች አካባቢ የሚደረጉ የሕዝብ ሰፈራዎችን፣ የደን ምንጣሮዎችንና የአደን ተግባሮችን ስርዓት ማስያዝ የሚያስችል ሕጋዊ ሁኔታ መፈጠር አለበት፡፡ በዚህ መስክ አፋጣኝ የሕግ ጥበቃዎች ካልተደረገና ተግባራዊ መሆን ካልጀመሩ ብርቅና ድንቅ የሚባሉ የዱር እንስሳትና አዕዋፋት በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጥፋት እድል ያጋጥማቸዋል፡፡ ስለዚህ ለቱሪዝም ገቢ ብቻ ሳይሆን ለእነዚህ ብርቅዬ እንስሳትና አእዋፍ ደህንነት ሲባል አፋጣኝና ሕጋዊ በሆነ አግባብ ዘላቂ መፍትሔ ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

# 6. የከተማ ልማት

## 6.1 የከተሞች ሕዝብ ብዛት

በኢትዮጵያ የከተሞች ሥርጭትና የሕዝብ ብዛት በጣም የተራራቀ ነው፡፡ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ባለሥልጣን መረጃ መሠረት በ1993 ዓ.ም መጨረሻ ላይ የነበረው ጠቅላላ የከተሞች ሕዝብ ብዛት 10 ሚሊዮን ነበር፡፡ በዚሁ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት በጠቅላላው 65.5 ሚሊዮን እንደነበር ይገመታል፡፡ ከዚህ መረዳት የሚቻለው የከተሞች ሕዝብ ብዛት ከጠቅላላው ሕዝብ 15 በመቶ ብቻ መሆኑን ነው፡፡ የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካ አገሮችን የከተማ ሕዝብ ብዛት ከጠቅላላው ሕዝብ ጋር ሲተያይ በመቶኛ በንጽጽር ማየት የከተማን ሁኔታ በተመለከተ ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል፡፡ በኢትዮጵያ 15 ከመቶ ሲሆን በኬንያ 28 ከመቶ፣ በሱዳን 31 በመቶ፣ በግብፅ 45 በመቶ እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 35 በመቶ ነው፡፡

በዚሁ ሰነድ ውስጥ 927 ከተሞች የተመዘገቡ ሲሆን ከአስር ሺህ በላይ የሕዝብ ብዛት ያላቸው 164 ብቻ ናቸው፡፡ ሌሎች 763 ከተሞች የሕዝባቸው ብዛት ከአስር ሺህ ያነሰ ነው፡፡ ከመቶ ሺህ በላይ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ከተሞች 11 ብቻ ሲሆኑ አዲስ አበባ ከሁሉም እጅግ ከፍተኛ ሕዝብ የሚኖርባት ከተማ ናት፡፡

አዲስ አበባ ሦስት ሚሊዮን ገደማ ነዋሪ አላት፡፡ በሕዝብ ብዛት ከአገራችን የሁለተኛ ደረጃ የያዘችው ድሬ ዳዋ ከተማ ነች፡፡ ይሁን እንጂ የአዲስ አበባ ከተማ ሕዝበ ብዛት የድሬ ዳዋን ከተማ ሕዝብ ብዛት 15 ጊዜ ያህል ይሆናል፡፡ ሐረር፣ ድሬዳዋ፣ ናዝሬት፣ ደብረዘይት፣ አዋሳ፣ ጂማ፣ ደሴ፣ ባሕርዳር፣ ጎንደርና መቀሌ ከአዲስ አበባ ሌላ በአገራችን ከፍተኛ የሕዝብ ብዛት ያላቸው ከተሞች ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የነዚህ የአሥሩም የሕዝብ ብዛት ሲደመር ውጤቱ የአዲስ አበባን 53 በመቶ ወይም ግማሽ ያህል ነው፡፡ ይህ የሚያሳየው አዲስ አበባ ከሌሎች ከተማዎች ጋር ስትነፃፀር እጅግ ሠፊ መሆኗን ነው፡፡ በተጨማሪም አዲስ አበባ የብዙ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ማዕከል ናት፡፡

ለእድገታችን ወሳኝ ከሆኑት አንዱ የከተሞች በቁጥርም፣ በመጠንም በጥራትም ማደግ ነው፡፡ ትክክለኛ የሆነ የእድገት አቅጣጫ ከተከተልን አሁን ተበታትነው የሚገኙ መንደሮች በሂደት እየቀነሱ ሰዎች በተማከለ አቀማመጥና የተሻለ የመሠረተ-ልማት አገልግሎት ወዳላቸው

*መንደሮች እየተሰባሰቡ በሚሄዱበት ጊዜ ከተሞች ይስፋፋሉ:: አሁን ያሉትም ከተሞች ስብጥር በኢንዱስትሪ ዘርፍ እድገት ሲታገዝ፣ አግባብነት ያለው የተመጣጠነ ይዘት ይኖራቸዋል:: በተጨማሪም፣ ዘመናዊ ሰፋፊ እርሻዎች ሲስፋፉ ከነሱ ጋር ተያይዞ በሚመጡት ኢንዱስትሪዎች አካባቢም ከተሞች ይፈጠራሉ:: ለዚህም ጥቂት ምሳሌዎችን ማቅረብ ይቻላል:: በአሁኑ ጊዜ 19 ሺህ ሕዝብ ያላት የወንጂ ገፈርሳ ከተማ የተፈጠረችው በወንጂ የመስኖ እርሻና ከሱም ጋር በተያያዘው የስኳር ፋብሪካ ምክኒያት ሲሆን በድምሩ 15 ሺህ ሕዝብ ያላቸው መልካ ወረርና መልካ ሰዲ የተፈጠሩት በአሚባራ የመስኖ እርሻ ምክኒያት ነው:: እንዲሁም 13 ሺህ የሕዝብ ብዛት ያላት ዱብቲ ከተማም የተፈጠረችው በዱብቲ የመስኖ እርሻ ምክኒያት ነው::*

# *6.2 በከተሞች ያጋጠሙ ችግሮች*

*በየከተሞቹ ያሉትን ችግሮች ለመገንዘብ ይቻል ዘንድ የአዲስ አበባ ከተማን ችግሮች በምሳሌነት ማየት ይቻላል:: በእርግጥ አዲስ አበባ ከተማ ከሌሎች ከተሞች ጋር ስትነፃፀር በብዙዎቹ መለኪያዎች የተሻለች ናት:: ሆኖም መሠረታዊ ችግሮቿ የመጠን ልዩነት ይኑራቸው እንጂ በዓይነት ከሌሎች ከተሞች ችግሮች ጋር ተመሳሳይነት አላቸው::*

*የአዲስ አበባ ዋነኛ ችግሮች ድህነትና የመልካም አስተዳደር እጦት ናቸው:: በግምት ከአዲስ አበባ ነዋሪ ሕዝብ ግማሹ በአስከፊ ድህነት ውስጥ ማለትም ከከፍተኛ የድህነት ወለል በታች ይኖራል:: ለድህነት መንሰራፋት ዋነኛው ምክኒያት የሥራ እጦት ነው:: ሥራ እጦት መባባስ ደግሞ የአገዛዝ ሥርዓቱ ውጤት ነው::*

*የአዲስ አበባ ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ ሥራ ማጣት፣ የቤት እጥረት፣ የሕክምና አገልግሎት ማነስ፣ የመንገድ መረብ (ኔትወርክ) ማነስ፣ የቆሻሻ ማስገድና የሳኒቴሽን አገልግሎት ማነስ፣ የስፖርትና የመዝናኛ ማዕከሎች ማነስ፣ አረንጓዴ የመናፈሻ አካባቢዎች ማነስ፣ የመቃብር አግልግሎት ማነስ፣ የመሳሰሉት ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ችግሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ::*

*በአዲስ አበባ ከጠቅላላው ነዋሪ መካከል ሠርቶ መተዳደር የሚችለው (ኢኮኖሚካሊ አክቲቭ የሆነው) ሕዝብ ብዛት 40 ከመቶው ብቻ ነው:: ከጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ሥራ ያለው ከ30 ከመቶ ያነሰ ነው:: ሥራ አላቸው የሚባሉትም አብዛናዎቹ የትምህርትና የሥልጠና ደረጃቸው ዝቅ ያለ ነው:: ሥራ ካላቸው ነዋሪዎች ውስጥ የቴክኒሺያንነትና ከዚያ በላይ የሙያ ደረጃ ያላቸው ነዋሪዎች 10 ከመቶ አይሞሉም:: ሥራ ካላቸው ነዋሪዎች ውስጥ በቀጥተኛ ምርት (በማኑፋክቸሪንግ) ሥራ ላይ የተሠማሩት ከ20 በመቶ ያንሳሉ::*

*በቤት እጥረት በኩል ያለው ሁኔታ ደግሞ በተለይም ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ከ80 በመቶ በላይ የሚሆኑት ነዋሪዎች የቤት ችግራቸው የጠና ነው:: አሉ የሚባሉትም ቤቶች ለመኖሪያነት ያላቸው አመቺነት እጅግ በጣም ዝቅ ያለ ነው:: 60 ከመቶ የሚሆኑት ቤቶች በቁማቸው ሊፈርሱ የተቃረቡ ናቸው:: ከ80 ከመቶ በላይ የሚሆኑት የተሠሩት ከእንጨትና ከጭቃ ሲሆን ከብሎኬትና ከጡብ የተሠሩት 10 ከመቶ አይሞሉም:: ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ኮርኒስ የላቸውም:: የቧንቧ ውሃ በውስጣቸው የተዘረጋ ቤቶች ከ5 በመቶ ያነሱ ናቸው:: ግማሽ ገደማ የሚሆኑት የቧንቧ ውሃ በግቢያቸው ውስጥ እንኳን የላቸውም:: የኤሌክትሪክ ቆጣሪ የብቻ ያላቸው ቤቶች ከግማሽ ያነሱ ናቸው:: አንድ አራተኛ ያህሉ ማብሰያ ቤት የላቸውም፣ 5 ከመቶዎች ብቻ ናቸው ዘመናዊ ማብሰያ ያላቸው::*

*በከተማው የሚታየው የጽዳት ችግር አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል:: ከአንድ-ሦስተኛ የሚበልጠው ደረቅ ቆሻሻ አይሰበሰብም:: አዲስ አበባ ካሉት ቤቶች ውስጥ አንድ አራተኛዎቹ ፈጽሞ መጸዳጃ የላቸውም:: ግማሽ የሚሆኑት የሚጠቀሙት በጋራ መጸዳጃ ቤት ነው:: አንድ አራተኛዎቹ ብቻ ናቸው የብቻ መጸዳጃ ቤት ያላቸው:: ከ90 ከመቶ በላይ የሚሆኑት መታጠቢያ ቤት የላቸውም::*

*በአዲስ አባባ ውስጥ ያለው የጤና ችግር እጅግ አስከፊ ደረጃ ላይ ደርሷል:: ይህንን በአንዳንድ ምልክቶች ማየት ይቻላል:: 1000 ሕፃናት ተወልደው 80 የሚሆኑት ከተወለዱ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ:: 110 የሚሆኑት 5 ዓመት ሳሞላቸው ይሞታሉ:: አማካይ የዕድሜ መጠን 58 ዓመት ነው:: አማካይ የውሃ አቅርቦት ለአንድ ሰው 30 ሊትር በቀን ነው::*

ከአዲስ አበባ ነዋሪ 60 ከመቶ የሚሆነው በታክሲ ለመገልገል አቅም የለውም፣ 20 ከመቶ የሚሆነው ደግሞ በአውቶቡስ እንኳን ለመጠቀም አቅም የለውም:: ነፍሳቸውን ሸጠው ሌሊት ሌሊት ከእንጦጦ አውሬዎች ጋር ሲታገሉ አድረው የሚሰበስቡትን የባህርዛፍ ቅጠል በመሸጥ ራሳቸውንና ቤተሰቦቻቸውን የሚያስተዳድሩት የአዲስ አበባ ነዋሪ ሴቶች ብዙ ናቸው:: ከእህል መሸጫና ከወፍጮ ቤቶች አካባቢ የሚፈስ እህል ለቅመው የሚተዳደሩም በርካቶች ናቸው:: በየመንገዱ ተሠማርተው በልመና ኑሯቸውን የሚገፉት ለቁጥር ያታክታሉ:: አንኳር አንኳሮች ብቻ ተጠቀሱ እንጂ የአዲስ አበባን ችግሮች ዘርዝሮ መጨረስ አይቻልም::

# 6.3 የከተሞችን ችግር ለመቀነስ መወሰድ ያለባቸው ርምጃዎች

## 6.3.1 ብቃት ያለው አስተዳደር መፍጠር

የከተሞችን ችግሮች ለመቀነስ ነዋሪዎችን አስተባብሮ መምራት የሚችል መልካም አስተዳደር መመሥረት ወሳኝ ነው:: ይህን ለማድረግ ራስን በራስ ለማስተዳደር የሚያበቃ ሙሉ ነፃነትን የሚያጎናፅፍ አስተዳደር ሊኖራቸው ይገባል:: ሙሉ ኃላፊነትና ሥልጣን የሚኖራቸው በነዋሪዎች በቀጥታ የሚመረጡ አስተዳደሮች መመሥረት አለባቸው::

ከተሞች ለኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን ወሳኝ የሆኑ ማዕከሎች ናቸው:: ለትራንስፖርትና ለመገናኛ፣ ለእቃና አቅርቦትና ለአገልግሎት፣ እንዲሁም ለእውቀት እምብርት ሆነው የሚያገለግሉ ማዕከሎች ናቸው:: የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች በግንባር ቀደምትነት የሚካሄዱባቸው፣ በርካታ መዋቅሮች የተዘረጉባቸው ወሳኝ ማዕከሎች ናቸው::

የከተሞች ባሕሪይ ሁሉንም ዘርፍ የሚዳስስ ብዙ ገፅታዎች ያሉትና ውስብስብ ነው:: ስለሆነም ዘርፈ-ብዙ የሆኑትን ችግሮችን ለመፍታት ብዙ ዓይነት ሞያተኞች በቅንጅት በመሥራት በየአቅጫው በማጥናት ብሎም መፍትሔ የመፈለግ አቅጣጫን መከተል ወሳኝነት አለው:: የከተሞችን ችግሮች ለመፍታት ውስን የሆነ የማያፈናፍን የአይዲዮሎጂ መስመር መከተል አያዋጣም:: ሁሉን አቃፊና አሳታፊ አካሄድ መከተልና ተግባራዊ ማድረግ ብሎም በውሳኔ መስጠት ሂደት ውስጥ የነዋሪዎችን ተሳትፎ ዋነኛ መሣሪያ ማድረግ ወሳኝነት አለው::

የከተማ አስተዳዳሪዎች ሥልጣንና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ ለመወጣትና በሥራቸው የተሳካ ውጤት ለማግኘት በርካታ ነገሮችን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ይኖርባቸዋል:: የነዋሪዎች ፍላጎትና ጥቅም እንደተጠበቀ ሆኖ እንዴት አድርጎ ከግሉ ዘርፍ ጋር መተባበር እንደሚቻል ዘዴ መፈለግ ይኖርባቸዋል::

ከተሞች የነዋሪዎቻቸው ደህንነት እንዲጠበቅ ለማድረግ የተለያዩ ሁኔታዎችን በዘላቂነት ማሟላት ይኖርባቸዋል:: ለኑሮ አመቺ መሆን መቻል ይጠበቅባቸዋል ማለትም የተሻለ የኑሮ ደረጃና ፍትሐዊነት ያለው ቀልጣፋ አገልግሎት ለሁሉም ነዋሪዎች መስጠት መቻል፣ ምርታማና ብቃት ያላቸው ተወዳዳሪ ሆኖ መገኘት፣ ዘላቂ የሆነ የፋናንስ ምንጭ መፍጠር፣ እና መልካም አስተዳደር ማደራጀት ይጠበቅባቸዋል::

ከተሞችን ለኑሮ አመቺ ለማድረግ ብቃት ያላቸው አስተዳደሮች መኖር ቅድመ ሁኔታ ነው:: ብቃት ያላቸው አስተዳደር ማለትም የገንዘብ አጠቃቀምንና ሌሎችንም ተግባራት በተመለከተ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መርህ አድርገው በቂ እውቀትና ችሎታን አጣምረው የነዋሪዎችን ጥቅምና ፍላጎት ለማርካት ተግተው የሚሠሩ ማለት ነው::

## 6.3.2 የኢንዱስትሪ መስፋፋት

ለከተሞች ኢኮኖሚ እድገት አቅጣጫ በኢንዱስትሪው ዘርፍ መስፋፋት ላይ የተመሠረተ መሆን ይገባዋል:: ይህ ዘርፍ በአግባቡ ከተያዘ ለከተማ ነዋሪዎች ሠፊ የሥራ ዕድል ከመፍጠሩም በላይ ለአገሪቱ ኢኮኖሚ በአጠቃላይ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ ይችላል:: በከተሞች ውስጥ በየትኛ ውም መስፈርት ቢለካ ከሌሎች አገሮች መሰል ከተሞች ጋር ሲነፃር የኢንዱስትሪው ዘርፍ አሁን ያለበት ደረጃ እጅግ ደካማ ነው:: ምርታማነቱም በጣም ዝቅተኛ ነው:: በመሆኑም በዓለም አቀፍ ውድድር ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ብዙ ትግል ይጠብቀዋል:: ለኢንዱስትሪ ልማት ማነቆ

*የሆኑት ጉዳዮች፣ ከቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ችግሮች፣ የገበያ ችግር፣ የፋይናንስ ችግር፣ የግብአት አቅርቦት ችግር፣ ብዙ ልምድ ካላቸው የውጭ ተፎካካሪዎች በተወሰነ ደረጃና ለተወሰነ ጊዜ የሚደረግ ጥበቃ አለመኖር፣ የመሳሰሉት ናቸው።*

*አገራዊ ጥቅም ሊኖራቸው የሚችሉ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት፣ እንዲሁም ወደ ውጭ የምንልካቸውን ምርቶች ዓይነት የሚያበዙና ለወደፊቱ በዓለም አቀፍ ንግድ ተፎካካሪ የሚሆኑ ኢንዱስትሪዎችን ለመምረጥና ለመለየት የሚያግዙ የኢንዱስትሪ ፖሊሲዎች ማዳበር አስፈላጊ ነው። የአገር ውስጥ አምራቾች በአገር ውስጥ ገበያ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ፣ ብሎም ወደ ውጭ ገበያ ምርቶቻቸውን እንዲያቀርቡ ማበረታታት አስፈላጊ ነው። ይህ አካሄድ የውጭ ኢንቨስተሮችንም ይስባል።*

## *6.3.3 የግሉ ዘርፍ አስተዋጽኦ*

*ለከተሞችን የመሠረተ ልማትም ሆነ ማኅበራዊ አገልግሎትን በመስጠት በኩል አመርቂ ውጤት ለማግኘት ከተፈለገ የተቻለውን ያህል ሥራዎችን ለግሉ ዘርፍ በኮንትራት መስጠት እየተለመደ መምጣት አለበት። የከተሞች አስተዳደር ቀስ በቀስ ከአብዛኛው አገልግሎት የመስጠት ተግባር ራሳቸውን በማግለል ሕግ፣ ደንብና ሥርዓት በማደራጀት፣ እንቅስቃሴዎችን በመቆጣጠርና ሁኔታዎችን በማመቻቸት ተግባር ላይ ቢሠማሩ መልካም ነው። ቀጥተኛ የሆነ የተግባር እንቅስቃሴውን በግሉ ዘርፍ በአቅም ማነስ ወይም በሌላ ምክኒያት ሊከናወኑ በማይችሉና በማይመቹት ላይ ብቻ ቢያተኩሩ ይበጃል። በዚህ መልኩ የከተማው አስተዳደር ኃላፊነቱን ቢወጣ የሚገኘው ውጤት ለነዋሪዎች ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል። በአጠቃላይ፣ ነፃ ውድድር ካለ፣ ቴክኒካዊ ብቃት ካለ፣ ተጠያቂነት ካለ፣ ከሁሉም በላይ ፖለቲካዊ መልካም ፈቃድ ካለ የግሉ ዘርፍ የተሻለ ውጤት እንደሚያስገኝ የተለያዩ አገሮች ልምድ ያሳያል።*

*የደረቅ ቆሻሻ ማስወገድ፣ ፈሳሽ ቆሻሻ ማስወገድ፣ የውሃ አቅርቦትና የኤሌክትሪክ አቅርቦት፣ የመንገድ ሥራ፣ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የመንገድ ሥራ፣ የትምህርት ቤት ግንባታ ሥራ፣ የጤና አገልግሎት መስጫ ግንባታ ሥራ፣ የመሳሰሉት በብዙ አገሮች እየተለመዱ የመጡ በግሉ ዘርፍ የሚከናወኑ በኮንትራት የሚሰጡ ሥራዎች እየሆኑ ነው። ታላላቅ የውሃ ፕሮጀክቶች፣ የኤሌክትሪክ ኃይል ፕሮጀክቶችና የቴሌኮሙኒኬሽን ፕሮጀክቶች የመሳሰሉት አሁንም ቢሆን በብዙ አገሮች በመንግሥት ባለቤትነት የሚሠሩ ናቸው። የማኔጅመትን፣ የኦፐሬሽንና አገልገሎት መስጠትን በተመለከተ ግን በግሉ ዘርፍ በኮንትራት ቢከናወኑ ውጤቱ ቀልጣፋና አስተማማኝ እንደሚሆን በቂ ልምድ አለ።*

## *6.3.4 የመሬት ይዞታ ሁኔታ*

*የከተሞችንም ሆነ የገጠር አስተዳደሮችን የሚፈታተነው አቢይ ችግር እጅግ በጣም ውስብስብ የሆነው ድህነት ነው። ድህነትን ለመቀነስ ሥራ አጥነትን መቀነስ ዋነኛው የመፍትሔ አቅጣጫ ነው። ይህም ይሳካ ዘንድ ከተሞች በንግድና ኢንዱስትሪው ዘርፍ ጉልህ እድገት ማሳየት ይጠበቅባቸዋል። ከተሞች በኢንዱስትሪው ዘርፍም ሁነ በሌላው ዘርፍ እድገት እንዲያሳዩ ወሳኙ ነገር ለግል ባለሀብቶች እንቅስቃሴ አበረታች በሆነ መልኩ መሬት የማቅረብ ጉዳይ ነው። የባለቤትነት መብትን በሚያረጋግጥ ሁኔታ የተሟላ የሕግ ድጋፍ ያለው ለግንባታ የሚውል መሬት በተቀላጠፈ ሁኔታ ማግኘት ወሳኝ ነው። ይህ ከሆነ ባለሀብቶች መሬታቸውንና በላዩ ላይ የገነቡትን ንብረታቸውን አስይዘው ገንዘብ ሊበደሩ ወይም ሸጠው ለውጠው ገንዘባቸውን በሌላ አማራጭ ቢዝነስ ላይ በማዋል ሊጠቀሙ ይችላሉ። እስካሁን ለመገንዘብ እንደተቻለው ብዙ በንግድና ኢንዱስትሪው ዘርፍ ለመሰማራት የሚፈልጉ ሰዎች በከፍተኛ ዋጋ መሬት ገዝተው ለሕንጻ ግንባታ፣ ለማምረቻ መሣሪያ፣ ለሠራተኛ ሥልጠና፣ ለሥራ ማስኬጃ፣ ወዘተ፣ የሚሆን ገንዘብ ማሟላት አይችሉም። በመሆኑም ለንግድና ኢንዱስትሪ አገልግሎት እንዲሁም ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የሚሆን መሬት ለሚፈልጉ ሰዎች አቅማቸውን በማገናዘብ ችግር ፈቺ የሆነ ልማትን የሚያራምድ ፖሊሲ መኖር አለበት።*

## *6.3.5 አግባብነት ያለው ፖሊሲና ዕቅድ አስፈላጊነት*

*ጠንካራ የከተማ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የሚያስችል ዕቅድ ማዘጋጀት ከየከተሞች አስተዳደር የሚጠበቅ ዋና ተግባር ነው። የተሳካ ውጤት ለማግኘትም (1) ስለከተማዎች ኢኮኖሚ ጠንካራና*

ደካማ ጎን በቂ ግንዛቤ የሚሰጥ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ዕውቀት፣ (2) ስለወደፊቱ የከተሞች እድገት ሂደት አስተማማኝ «ራዕይ» ያለው ጠንካራና ቁርጠኛነት ያለው ፖለቲካዊ አመራር፣ (3) ከተለያዩ አጋሮች ማለትም ከነጋዴዎች፣ ከማኅበሮች፣ ከምሁራን፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ወዘተ ጋር መመካከር፣ የመሳሰሉት ወሳኝ ጉዳዮች ከግምት ውስጥ መግባት አለባቸው።

የማምረትና የንግድ እንቅስቃሴ፣ የፋይናንስ አገልግሎት፣ የሆቴልና የቡና ቤቶች አገልግሎት፣ የመረጃ አገልግሎት፣ የቱሪዝም መስህቦች፣ የመጓጓዣና የመገናኛ አገልግሎት፣ የመሳሰሉ የኢኮኖሚ ዘርፎች በቂ ትኩረት ሊያገኙ ይገባል። በተጨማሪም እንደ ጤና አገልግሎት፣ ትምህርት፣ ባሕል፣ ስፖርት፣ የመሳሰሉትም ለነዋሪዎች አስፈላጊ ከመሆናቸውም በላይ ኢንቬስተሮችን ለመሳብ ወሳኝ ናቸው።

የተጠቀሱትን ጉዳዮች ባግባቡ ለማስተናገድ የሚበጅ የከተሞች ፖሊሲ መፍጠር ወሳኝ ጉዳይ ነው። ለፖሊሲውም ውጤታማነት ዋናው ጉዳይ በቀረጻና በተግባር የማዋሉ ሂደት ላይ ግልጽነት መኖር ነው። ፖሊሲዎች በሚነደፉበት ጊዜ ሕዝቡ በውይይት በሚዘጋጁ መድረኮች አማካይነት በደንብ እንዲያውቃቸውና ባለሀብቶች በሂደቱ እንዲካፈሉ መደረግ አለበት። የተወሰኑ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ቡድኖች የራሳቸውን የግል ጥቅም በመሻት ፖሊሲውን እንዳያጣምሙት በአተገባበሩ ላይ የግልፅነት መኖር በጣም አስፈላጊ ነው።

በከተሞችም ሆነ በገጠር በጠቅላላ በአገሪቱ ድህነትን ለመቀነስ ከተፈለገ ለግሉ ዘርፍ እድገት በሚያመጡ እርምጃዎች ላይ ልዩ ትኩረት መስጠት አስፈላጊ ነው። ይህ ዘርፍ ብዙ የሥራ እድል መፍጠር ይችላል። ስለሆነም የግሉን ዘርፍ በማንኛውም አመቺ መንገድ ሁሉ መደገፍና ማበረታታት እንዲሁም በፖሊሲ ቀረፃ ሂደት ማሳተፍ አስፈላጊ ነው።

የከተሞችን ችግር ለመቀነስ ተደራጅተው የሚቀሳቀሱ የሲቪል ማኅበረሰብ ወሳኝ አጋሮች ናቸው። መደራጀት የከተሞችን ውስብስብ ችግሮች በመቀነስ እንቅስቃሴ እስከ መጨረሻው በቀጣይነት ለመሳተፍ አስፈላጊ ነው። ያልተደራጁ ሥርዓት ባለው መልክ በስትራቴጂ ቀረፃ፣ በክንውንና በግምገማ ሂደት በቀጣይነት ለመሳተፍ ይቸገራሉ።

# 6.4 ቤቶችና የከተማ ልማት

በከተማ ውስጥ ከሚኖረው ሕዝብ መካከል የራሱ ቤት ያለው እጅግ አነስተኛ ነው። አብዛኛው ሕዝብ በኪራይ ቤት ውስጥ የሚኖር ነው። የራስን ቤት ለመስራት የሚያስችል አቅም ባለመኖሩ የቤት ባለቤት መሆን ከባድ ነው። በመንግስት በኩልም ቤት ለሌላቸው ቤት እንዲሰሩ የሚያደፋፍር ድጋፍ አይሰጥም። የራስ ቤት ለመስራት ካለው ችግር ባላነሰ ሁኔታ የኪራይ ቤት ማግኘትም ከባድ ችግር ነው። መንግስት ለተከራዮች የሚያገለግሉ ቤቶችን የመስራት ተነሳሽነት ካለማሳየቱም በላይ ቤት ሰርተው ለሚያከራዩ የግል ባለሀብቶችም የሚያደርገው ድጋፍና ማበረታቻ ጠንካራ አይደለም። በሀገሪቱ ከተሞች በተለይ በአንፃራዊ ሁኔታ ትላልቅ በሚባሉት ውስጥ የከፋ የቤት እጥረት አለ። በርካታ ቤተሰብ ያላቸው፣ አዳዲስ ትዳር የሚመሰርቱና በተለያየ መንገድ ወደከተማ የሚገቡ ዜጎች አስከፊ የቤት እጥረት ችግር አለባቸው።

ለቤት እጥረት እንደዋነኛ ምክንያት የሚጠቀሱት ፈጣን የሆነ የሕዝብ ቁጥር እድገት፣ ከገጠር ወደከተማ የሚደረገው ፍልሰት፣ ድህነትና አቅም ማጣት ቢሆኑም የመንግስት ፖሊሲ ችግሮችም ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። የሕዝብ ቁጥር እድገትን ለመቀነስ፣ ከገጠር ወደከተማ የሚደረገውን ፍልሰት ለመቆጣጠር፣ ድህነትን ለመቀነስ፣ የቤት መስሪያ ቦታ ለመስጠት፣ የብድርና የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ለማቅረብ የሚያስችል ምቹ የፖሊሲ ሁኔታ ባለመኖሩ ችግሩ ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ እንጂ እየቀነሰ አልሄደም። የከተማ ቦታ የሊዝ ዋጋ መናር፣ የውሃ፣ የመብራት፣ የመንገድ፣ የፍሳሽና የመፀዳጃ፣ የስልክ፣ የትራንስፖርትና የመሳሰሉ የመሰረተ ልማት ስራዎች ደካማ መሆን በከተሞች ውስጥ ያለውን የኑሮ ችግር ይበልጥ አስከፊ አድርገውታል።

በአሁኑ ጊዜ ለተከራዮች አገልግሎት የሚሰጡና በቀበሌም ሆነ በኪራይ ቤቶች አስተዳደር ስር የሚገኙ ቤቶች ጥገናና እድሳት ሳይደረግላቸው ወደ 30 ዓመታት ገደማ በማስቆጠራቸው የምግብ ማብሰያና የቆሻሻ ማስወገጃ የላቸውም። ጥራታቸው ከሚከፈለው ኪራይ ጋር የሚመጣጠ

ን አይደለም። ለተከራዮች የሚሰጡበትም ስርዓት ግልፅነት የሌለውና ፍትሃዊነት የጎደለው በመሆኑ የዘመድ አዝማድ መጠቃቀሚያና በከፍተኛ ደረጃ ሙስና የሰፈነበት ነው። በአከራዩ አካል ወይንም በተከራዩ ጥገና እንዲደረግላቸውና አገልግሎታቸው እንዲሟላ የሚያስችል የማስፋፋት ስራ የሚከናወንበት ፕሮግራምና ስርዓት ባለመኖሩ ብዙዎቹ በተከራዮቹ ላይ እየወደቁ ይፈርሳሉ።

ከእነዚህ አሳሳቢ ችግሮች ለመውጣት የሚያስችሉ መፍትሔዎች መገኘት አለባቸው። ሊቀርቡ ከሚችሉት መፍትሔዎች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው። በመጀመሪያ ቤት ለመስራት አቅም ለሚያንሳቸው ዜጎች መንግስት የብድር ድጋፍ የሚሰጥበት አሰራር በሰፊው ጥቅም ላይ መዋል አለበት። የመሬትን የሊዝ ዋጋ ማንሳትና ቦታ ለማግኘት ያለውን የቢሮክራሲ ውጣ ውረድ ማስቀረት ሌላው ጠቃሚ እርምጃ ነው። ቤት ሰርተው ለሚያከራዩ ባለሀብቶች የተለየ ድጋፍ ማድረግ፣ የታክስ ቅነሳ ማድረግ፣ ለተወሰነ ጊዜ ከታክስ ክፍያ ነፃ ማድረግ፣ ለግንባታ ከውጭ የሚያስገቧቸው ማሽነሪዎችና መሳሪያዎች ከቀረጥ ነፃ ሆነው እንዲገቡ ማድረግ፣ ለግንባታ የሚውለውን ካፒታል ለመሬት ሊዝ የሚከፍሉበትን ሁኔታ ማስቀረት፣ እንደመንገድ፣ ውሃ፣ ስልክና መብራት የመሳሰሉትን የመሰረተ ልማት ስራዎች መስራት ከመንግስት የሚጠበቁ ናቸው።

አሁን የኪራይ አገልግሎት እየሰጡ ያሉት የቀበሌና የኪራይ ቤቶች አስተዳደር ቤቶች ነዋሪዎቹ አቅም ካላቸው እንዲጠግኑና ለጥገና ያወጡት ከኪራዩ እንዲታሰብላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። በግለሰብ ቤት ተከራይተው የሚኖሩ ዜጎች ያልተጠበቀ ከፍተኛ የኪራይ ጭማሪ በዘፈቀደ እንዳይደረግባቸው፣ ያለበቂ ማስጠንቀቂያና የመዘጋጃ ጊዜ ከተከራዩት ቤት እንዲወጡ የሚገደዱበት ሁኔታ እንዳይኖር የመከላከያ ሕግ ማውጣትም በመንግስት በኩል መሰራት ያለበት ነው። አዲስ ቤት ለመስራት የጠየቁ ዜጎች የሚሰጣቸው የቤት መስሪያ ቦታ መጠን እጅግ እያነሰ የመጣበት ሁኔታ እንዲሻሻልና ለኑሮና ለጤንነት አመች የሆነ መኖሪያ ቤት መገንባት የሚያስችል መጠን ያለው በቂ ቦታ ለአንድ ጊዜ እንዲያገኙ መደረግ ይኖርበታል።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ከተሞች ዕድገት በጥናት ላይ በተመሰረተ ዕቅድ እንዲመራና ከአገሪቱ አጠቃላይ የማህበራዊና የኢኮኖሚ ዕድገት ኘላን ጋር እንዲጣጣም ለማድረግ አገር ተቀፍ የአከታተም ስልት መቀየስና የከተሞችን ኘላን በዚሁ ስልት መሠረት አዘጋጅቶ ማስፈጸም አስፈላጊ ነው። ይህንኑም አገር አቀፍ የአከታተም ስልት በመከተል ስለከተሞች ኘላን አዘገጃጀት ጥናት የሚያደርግና የከተሞችን ኘላን አዘጋጅቶ የሚያቀርብ ራሱን የቻለ የመንግስት መስሪያ ቤት ተቋቁሞ ስለከተሞች ኘላን ያለው ሣይንሳዊ አሰራር ከሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎ ጋር ተቀናጅቶ ሊዘጋጅና ሊፀድቅ የሚችልበት ሥርዓት በህግ ሊወሰን ይገባል።

በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ካሉት ከተሞች ውስጥ ማስተር ኘላን ያላቸው 11፣ የዕድገት ኘላን ያላቸው 62፣ የገቢር ኘላን (Action Plan) ያላቸው ደግሞ 16 ብቻ ናቸው። ይህ ደግሞ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ከተሞች ብዛት አንፃር ሲታይ ኢምንት ነው። ስለሆነም የከተሞች የአከታተም ሥርዓት ትኩረት የሚያሻው ጉዳይ መሆኑ አያጠራጥርም።

# 7. የኢንፎርሜሽን፣ የመገናኛና ትራንስፖርት ሥርዓት

## 7.1 የኢንፎርሜሽን አስፈላጊነት

ኅብረተሰብ በፖሊሲ ጉዳዮች ላይ መሳተፉ ተጨባጭ እንዲሆን መንግሥት በኢንፎርሜሽን ላይ ያለውን ብቸኛ ባለቤትነት እንዲለቅ ማድረግ ያስፈልጋል። ሕዝብ በኢኮኖሚና በማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ግልጽ ውይይት እንዲያደርግ አስተማማኝ ኢንፎርሜሽን ማግኘት አለበት። ምንም ዓይነት ቁም ነገር ያለው ሕዝባዊ ውይይት በሌለባቸው ሁኔታዎች የተወሰኑ ፖሊሲዎችን ሕዝቡ በሙሉ ድምፅ እንደደገፈ ተደርጎ በመንግሥት ሲነገር ይሰማል። በሌላ በኩል ደግሞ መንግሥት የሚለውን ማንኛውንም ነገር ሕዝቡ ጨርሶ አለማመኑ ወይም በጥርጣሬ መመልከቱ የተለመደ ቲያትር ሆኗል።

ፖሊሲ በመንደፍና በማውጣቱ፣ የወጡትን ፖሊሲዎች ተግባራዊነት በመገምገሙ ሂደት ውስጥ ሕዝብ በተደራጀ መልኩ በንቃት እንዲሳተፍ ማድረግ ያስፈልጋል። በፖሊሲው ጉዳዮችም ይሁን በሌሎች ጉዳዮች የሚከናወኑት ማናቸውም ነገሮች በትክክል መፈፀማቸውን ለማረጋገጥ ከተፈለገ ሕዝቡ የሚቀበለውን አስተማማኝ ኢንፎርሜሽን ማዘጋጀትና ማሰራጨት ያስፈልጋል። ይህንን ለማሟላት ደግሞ ከመንግሥት የተለዩ ነፃ የኢንፎርሜሽን ማከማቻና ማሰራጫ ተቋማትን መፍጠር ወይም ከመንግሥት ተፅእኖ ነፃ ሆኖ ሊሠራበት የሚችል የኢንፎርሜሽን ማረጋገጫ ዘዴ መቀየስን ይጠይቃል።

በየዘርፉ የሚያስፈልገው የመረጃ ዓይነት በባሕሪይው ብዙና ሰፊ ነው። በየዘርፉ የሚያስፈልገው የኢንፎርሜሽን እጥረት ከተፈጠረ ፍሬያማ ውይይት ማካሄድ አይቻልም። ተገቢና ፍሬያማ የሆነ ትንታኔ ለማድረግ አስተማማኝ መረጃ አስፈላጊ ነው። በፖለቲካ መረጋጋት እንዲሁም በኢኮኖሚና ማኅበራዊ እንቅስቃሴ መሳካት መካከል ያለው ግንኙነት የጠበቀ ነው። በመሆኑም የሚያስፈልጉትን መረጃዎች አግባብ ባልሆነ መንገድ የመጠቀሙ አዝማሚያና ፈተና ከፍ ያለ ነው። አንዳንድ ውጤቶችን አስመስሎ ለማቅረብ ሲባል የተዛቡ አኃዛዊ መግለጫዎችን ማቅረብ ደጋግሞ ያጋጥማል።

ከተለያዩ መሠረታዊ ምንጮች የተውጣጡ መረጃዎችን የያዘ አስተማማኝ የመረጃ ግምጃ ቤት (ዴታ ቤዝ) ማዘጋጀት እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። በዚህም የመረጃ ግምጃ ቤት ባለሙያዎች ከመንግሥት ተፅእኖ ነፃ በሆነ መልኩ ሊጠቀሙበት ይገባል። ግልፅ በሆነ፣ ዘለቄታ ባለው፣ ሥርዓት በያዘና ገንቢ በሆነ መንገድ ለሕዝቡና ለፖሊሲ ነዳፊዎች በኢኮኖሚና ማኅበራዊ ጉዳዮች ላይ ነፃ የሆነና ሙያዊ ብቃት ያለውንና በመረጃ የተደገፈ አስተያየታቸውን ለማቅረብ የሚያስችላቸው ሁኔታ መመቻቸት አለባቸው። የሚዘጋጁ ዕቅዶችና የሚካሄዱ ክንውኖች አዋጭነትና ዘላቂነት እንዲኖራቸው ለማድረግ ነፃ የሆነ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት መፍጠር አማራጭ የሌለው ነገር ነው።

ከዚህ በማስከተልም በተለያዩ ዘርፎች የኢንፎርሜሽን ሥርዓት መፍጠር ምን ያህል ወሳኝነት እንዳለው ለማሳየት ለምሳሌ ያህል የኢንዱስትሪና የጂኦ-ኢንፎርሜሽንን በምሳሌነት ለማሳየት ተሞክሯል።

## 7.1.1 ኢንዱስትሪ - ነክ ኢንፎርሜሽን

ቴክኖሎጂ-ነክ ኢንፎርሜሽን በፈለጉበት ቦታ ሁሉ ስለማይገኝና የዓለም ገበያም እንደሚባለው ሙሉ በሙሉ በነፃ ፉክክር ላይ የተመሠረተ ስላልሆነ፣ በተለይ የቴክኖሎጂን ምንጮች የሚጠቁም ኢንፎርሜሽንን በሚመለከት፣ ለገበያ ውድቀት አስፈላጊውን መፍትሔ የሚያቀርቡ የቴክኖሎጂ ተቋማት መኖር አለባቸው። የኢንዱስትሪ ዘርፍ ያለበት አንድ ዐቢይ እንከን፣ ለዘርፉ ልማት ተገቢውን ድጋፍ የሚያደርጉ ተቋማት አለመኖራቸው ነው። አሁን ያሉትም ተቋማት ቢሆኑ፣ ወይም በቂ የሰው ኃይልና ብቃት ያለው አመራር ይጎድላቸዋል፤ አሊያም የሥራ ማስኬጃም የሚሆን በቂ ገንዘብ የላቸውም። ከዚህም በተጨማሪ በቢሮክራሲ ውጣ-ውረድና በፖሊሲ፣ በህግ፣ በደንብና በመመሪያ ምክኒያት ተተብትበዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ስለ ቴክኖሎጂም ሆነ ስለ ገበያ ሁኔታ ኢንፎርሜሽን የሚያቀርቡ ተቋማት የሉም። በምርት ተግባር ውስጥ ደግሞ ተገቢውን ቴክኖሎጂ - ማለትም ከአገር ውስጥ ሁኔታዎች ጋር አቀራኝቶ፣ አብላልቶና እንዲመጣጠን አድርጎ በሥራ ላይ ለማዋል የሚመች ቴክኖሎጂን መምረጥ በኢንፎርሜሽንና በተገኘው ኢንፎርሜሽን በደንብ መጠቀምን በመቻል ላይ የተመሠረተ ነው። ኢንፎርሜሽን በባሕሪዩ ሕዝባዊ በመሆኑና ለመሰብሰብና ለማደራጀትም ሰፊ ወጪና ዝግጅት ስለሚጠይቅ፣ የግሉ ዘርፍ በዚህ መስክ የሚያስፈልገውን ያህል ኢንቨስት አያደርግም፤ ምክኒያቱም ከመስኩ የሚገኙትን ጥቅሞች ሁሉ በሥራ ላይ ሊያውላቸው አይችልም። በመሆኑም መንግሥት ቴክኖሎጂ ነክ ኢንፎርሜሽንን ለመሰብሰቡና ለማሰራጨቱ ተግባር ትኩረት መስጠት አለበት። መንግሥት ይህንን ተግባር የሚያከናውኑ ተቋማትን መሥርቶና በሥራውም ለተሠማሩት ድጎማ በመስጠት ተጠቃሚዎች አቅም በሚፈቅደው ዋጋ አስፈላጊውን የኢንፎርሜሽን አገልግሎት እንዲሰጡ ማድረግ አለበት። ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ውስጥ በትልልቅና በትንንሽ ተቋማት መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የለም፤ ወይም ኢንፎርሜሽን ለማቅረብ አቅም ለሌላቸው አነስተኛ የኢንፎርሜሽን ተቋማት ተገቢውን ተቋማዊ ድጋፍ በመስጠት ለኢንፎርሜሽን ስርጭት አመቺ ሁኔታ አልተፈጠረም። ነገር ግን በከፍተኛ ደረጃ ለሚንቀሳቀሱትም ተቋማት ቅልጥፍናም ሆነ ለአነስተኛ ተቋማት መስፋፋት እንዲበጅ የኢንፎርሜሽን ሥርጭትን ተግባር ለመካከለኛ ባለኮንትራቶች ማደላደሉ አስፈላጊ ስለመሆኑ በማስረጃ የተደገፉ ጠንካራ አስተያየቶች አሉ።

## 7.1.2 ጂኦ-ኢንፎርሜሽን

ጂኦ-ኢንፎርሜሽን የካርታ ሥራ፣ የሜትሮሎጂ፣ የሃይድሮሎጂ፣ የሴስሞሎጂ፣ ወዘተ የመሳሰሉትን ኢንፎርሜሽን ያጠቃልላል:: የሪሞት ሴንሲንግና የአየር ፎቶግራፍ ቴክኖሎጂዎችን ለካርታ ሥራ፣ ለማዕድን፣ ለውሃ፣ ለአፈርና ለሌሎች የተፈጥሮ ሀብቶች ፍለጋና ጥናት፣ እንዲሁም ለአየር ባህሪይና ለአካባቢ ጥናት በቅንጅትና ውጤታማ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ለማዋል የሚካሄዱ የጥናትና የማደራጀት ሥራዎችን መሥራት አስፈላጊ ነው:: በተለያዩ ድርጅቶችና ተቋማት ተሰብስቦ ተጠናቅሮና ተከማችቶ የሚገኝ የዘርፉን መረጃ ለተጠቃሚዎች በቀላሉ እንዲዳረስ ለማድረግ የሚያስችል የመረጃ ሥርጭትና ልውውጥ ሥርዓት ለመዘርጋት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች መበረታታት አለባቸው:: ጂኦ-ኢንፎርሜሽን የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የማጠናቀር፣ የመተንተንና ለተለያዩ ተጠቃሚዎች በሚስማማ መልኩ በማዘጋጀት ለፖሊሲና ዕቅድ ዝግጅት፣ ለማኔጅሜንት ውሳኔዎችና ለምርምርና ሥርፀት በስፋት ጥቅም ላይ የሚውልበትን መንገድ ለማደራጀት፣ ለዚህ የሚረዱ እንደ ጂኦግራፊክ ኢንፎርሜሽን ሲስተምስ ያሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማሸጋገርና ለአገራችን ሁኔታ በሚመች መልክ በማሻሻል ጥቅም ላይ ለማዋል የሚከናወኑ ተግባራት እጅግ አስፈላጊ ናቸው:: ጂኦ-ኢንፎርሜሽን በስፋት ጥቅም ላይ እንዲውልና ለዚህም ወሳኝነት ያለው የካርታ አጠቃቀም በስፋት እንዲለመድ የሚያግዝ የአሕዝቦት ሥራ መሥራትና በጂኦ-ኢንፎርሜሽን መስክ የሚያስፈልገውን የሰው ኃይል በአገር ውስጥ የማሰልጠን አቅም እንዲጠናከር ማድረግ ጠቀሜታ አለው:: እንዲሁም በዘርፉ መረጃ ለመሰብሰብ፣ ለማከማቸት፣ ለማጠናቀር፣ ለመተንተንና ለመጠቀም የሚያስችሉና ለምርምርና ሥርፀት ድጋፍ የሚሠጡ ቤተ ሙከራዎችንና ወርክሾፖችን የማጠናከርና የማስፋፋት ተግባሮችን ማካሄድ ከፍ ያለ ጠቀሜታ አለው::

በአጠቃላይ መረጃ የማመንጨት ተግባር የተጠቃሚዎችን ፍላጎት ለይቶ በማወቅ ላይ የተመሠረተ ማለትም የተጠቃሚውን ጥያቄ የሚያሟላ እንዲሆን ማድረግ እንዲሁም መረጃ አሰባሰብና ትንተና እንዲሁም የመረጃ ሥርጭት ያልተማከለ ነገር ግን የተቀናጀ እና በተቻለ መጠን ደረጃው አንድ ወጥ የሆነ መሆኑን ማረጋገጥ አስፈላጊ ነው:: በስፋት በጥቅም ላይ የሚውሉ መረጃዎች ሊገኙ የሚችሉበትና ለልዩ ልዩ ተጠቃሚዎች የተዘጋጁ መረጃዎች የሚገኙባቸው ቦታዎች የሚረጋገጡበት ማዕከላዊ ስፍራ ወይም ድርጅት እንዲኖር ማድረግ ወሳኝነት አለው::

# 7.2 የኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ

## 7.2.1 የቴክኖሎጂው አስፈላጊነት

አሁን ያለንበት ዓለም የሚታወቀው የዓለም-አቀፋዊ ኢንፎርሜሽን ማኅበረሰብ በፈጠረው በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ኢኮቴ) አብዮት ነው:: ይህም ሁኔታ በዋነኛነት የሚገለጽበት ኢንተርኔት ነው:: በመሆኑም ሕይዎትን የሚመለከቱ ጉዳዮች ማለትም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ኢንፎርሜሽንና እውቀት በማይታመን ፍጥነት ይዘዋወራል:: በዚህ ኢንፎርሜሽን ዘመን የአንድን አገር በዓለም-አቀፍ (ግሎባል) ኢኮኖሚ ውስጥ ተወዳዳሪነት የሚወስነው ኢኮቴን በብቃትና በጥራት መጠቀም ነው::

ኢትዮጵያ ከዚህ የኢንፎርሜሽን አብዮት ጠርዝ ላይ ቆማ መቅረት አትችልም:: ኢትዮጵያን ለዓለም-አቀፋዊው ኢንፎርሜሽን ማኅበረሰብ አስፈላጊና ብቃት ያላት አጋር ለማድረግና ዜጎች ከዓለም አቀፍ እውቀት ተጠቃሚ የሚሆንበት ዋስትና ለማግኘት ኢኮቴን መጠቀን አስፈላጊ ነው:: ድህነትን ለመዋጋትና የኢትዮጵያውያንን ኑሮ ለማሻሻል ለሚደረገው ጥረት አስተዋፅኦ ለማድረግ፣ መልካም አስተዳደርን ለመፍጠርና የመንግሥት ተቋማትን አገልግሎት ብቃት እንዲኖረው ለማድረግ ኢኮቴ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው:: ኢትዮጵያ የኢኮቴ ተጠቃሚ ብቻ ሳይሆን አምራችም የምትሆንበትን መንገድ ከወዲሁ ማመቻቸት ያስፈልጋል::

በሃያኛው ምዕተ ዓመት መጨረሻ ገደማ ጀምሮ በፖለቲካው፣ በኢኮኖሚውና በማኅበራዊ ሥርዓቶች መሠረታዊ ለውጦች በዓለማችን እየተከሰቱ እንደሆነ እየታየ ነው:: የዓለም ሕዝብ እየተቀራረበ፣ የፖለቲካ አጥር እየተጣሰ፣ ገበያዎች እየተዋሃዱ፣ የውድድር አድማስ እየሰፋ በሚሄድበት በአሁኑ ወቅት ታዳጊ አገሮችም ጭምር በሂደቱ ውስጥ ራሳቸውን ቦታ ለማስያዝ እየገሰገሱ ነው:: የዘመኑ ውጤታማነት የሚለካው ለውጥን ለመልመድ ቀልጣፋና ፈጣን ሆኖ በመገኘት ነው::

ኢኮቴ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ለውጦች ለማምጣት የሚበጁ ውሳኔዎችን ለማስተላለፍ የሚያስችሉ መረጃዎችን በማመቻቸት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ኢኮቴ የግሉ ዘርፍ ኢንቬስትሜንቱን እንዲያስፋፋና ሥራ መፍጠር እንዲችል ብሎም የሕዝቡ ኑሮ እንዲሻሻል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

በዚህ ሠነድ ውስጥ ኢኮቴ ማለት ኮምፒዩተርን፣ የኮምፒዩተር መረብን፣ ሬዲዮንን፣ ቴሌቪዥንን፣ ስልክን፣ ፋክስን፣ የኢሌክትሮኒክስ ሜይልን፣ ኢንተርኔትን፣ ቴሌ-ኮንፈረንስን፣ ቪዲዮ-ኮንፈረንስን፣ ወዘተ. ያጠቃልላል፡፡ እነዚህ የተጠቀሱት የኢኮቴ ዘርፎች በተናጠል ሳይሆን በቅንጅት በተቀነባበረ መልኩ ስለሚሠሩ ውጤቱ እጅግ ቀልጣፋና አመርቂ እንዲሆን አስችሏል፡፡

የኢኮቴ መኖር ታይቶም ተሰምቶም በማይታወቅና ከፍተኛ በሆነ ፍጥነት እውቀትና ልምድን ለመለዋወጥ አስችሏል፡፡ ለግለሰቦችና ለአገሮች ማኅበረ-ኢኮኖሚ ልማት ለማምጣትና በዓለም-አቀፉ ሕብረተሰብ እንቅስቃሴ ሂደት በብቃት ተሳታፊ ለመሆን ኢኮቴ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የዓለም ሠፊ የግንኙነት መረብ የሆነው የኢንተርኔት መኖር ሃሳብ ለመለዋወጥ፣ ለንግድና ለሌሎችም ጉዳዮች የሚሆን መረጃ ምንጭ በመሆን ከፍተኛ ጥቅም አስገኝቷል፡፡

ያለመታደል ሆኖ ይህ ቴክኖሎጂ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው ሥርጭትና አጠቃቀሙ ላይ አዋዋሉ እጅግ አነስተኛ ደረጃ ላይ ነው፡፡ የስልክ መስመሮችና የኮምፒዩተሮች ማነስ በቤታችን፣ በመሥሪያ ቤታችንና በሌሎች አመቺ ቦታዎች ሁሉ በቀላሉ ያለድካም «ቁልፎችን በመነካካት» በኢንተርኔት አማካይነት ማግኜት እንችል የነበረውን ጠቃሚ መረጃ እንድናጣ አድርጎናል፡፡ በመሆኑም አገራችን ብቁ ተወዳዳሪ እንድትሆን ሁኔታዎች በፍጥነት መለወጥ ይኖርባቸዋል፡፡ ኢኮቴ ለበርካታ ብሔራዊ ልማት ዘርፎች ሞተር ሆኖ ሊያገለግል ይችላል፡፡ አገራችን በዓለም አቀፉ ኢኮኖሚ ውስጥ ተሳታፊ እንድትሆን፣ የሚያስችል፣ መልካም አስተዳደርን ለማስፈን፣ የዜጎችን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል የሚበጅ መረጃና እውቀት ማግኜት ያስችላል፡፡

በኢኮቴ ተጠቃሚ ለመሆን የተለያዩ ወገኖች ፖሊሲ በመቅረፅ፣ ዕቅድ በማውጣትና በተግባራዊ ልማቱ ተሳታፊ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ውስን ሀብት፣ አነስተኛ የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትና አነስተኛ የተማረ የሰው ኃይላችንን አስተባብሮ በኢኮቴ በአግባቡ ለመጠቀም ከሌሎች ሁኔታዎች አመቺ ከሆኑላቸው አገሮች የበለጠ ፈተና አለብን፡፡ ይሁን እንጂ ፈተናው ሊቀርም ሊተላለፍም አይገባውም፣ ፈተናውን በአግባቡ ማለፍ እንጂ፡፡

በኢኮቴ ልማትና ለአገራዊ ዘላቂ ልማት መገልገያ መሣሪያ በማድረግ ሂደት ውስጥ መንግሥት የሚጫወተው መሠረታዊ የሆነ ወሳኝ ሚና አለው፡፡ የመንግሥት አንዱ ሥራው የኢኮቴን አቅርቦት፣ አገልግሎትና አጠቃቀም በተመለከተ የሚያስፈልገውን የሕግ ማዕቀፍ ማዘጋጀት ነው፡፡ ከዚህም በተጨማሪ የመንግሥት ሚና በግሉ ዘርፍና በመንግሥት፣ በኢንዱስትሪ፣ በኢንፎርሜሽንና በኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ሙያዊና ማኅበራዊ ድርጅቶች፣ እና ሲቪል ማኅበረሰብ መካከል የትብብር መድረክ እንዲፈጠር ማመቻቸት ነው፡፡

የመንግሥትን በቴሌኮሙኒኬሽን ላይ ያለውን ብቸኛ ባለቤትነት አስወግዶ የተወዳዳሪነትን መርህ የተከተለ አሠራር ማስፈን ይቆይ የማይባል ነው፡፡ ሆኖም በአሁኑ ጊዜ ጠንካራ ብሔራዊ የግል ዘርፍ የውጭ ባለሀብቶች በኢኮቴ ዘርፍ እንዲሳተፉ ሁኔታዎች መመቻቸት ይኖርባቸዋል፡፡ የብሔራዊ የግል ዘርፉ ከውጭ ባለሀብቶች ጋር ተቀናጅቶ እንዲሰማራ ማድረግ ደግሞ የቴክኒክ እውቀትና የማኔጅሜንት ችሎታ እንዲያዳብር ስለሚረዳ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡

በእርግጥ በአደጉ አገሮች ዋነኛ የኢኮቴ አንቀሳቃሽ ሞተር የግሉ ዘርፍ ነው፡፡ በአገራችን ግን ይህንን የግንባር ቀደምነት ሚና ገና ለጋ በሆነው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ በሚገኘው በብሔራዊ የግል ዘርፍ ላይ መጣል አይቻልም፡፡ ሆኖም የግሉ ዘርፍ አሁንም ቢሆን በዘርፉ ሊያደርግ የሚችለው አስተዋጽኦ የሚናቅ አይደለም፡፡ በተለይም ከኮምፒውተር ጋር በተያያዘ - በማቅረብ፣ በመጠገን፣ በማሰልጠን - የግሉ ዘርፍ እያደረገ ያለውና ሊያደርግ የሚችለው አስተዋፅኦ አበረታች ነው፡፡

## 7.2.2 ኢኮቴና የርቀት ትምህርት

ኢኮቴ በተለይም ኢንተርኔት ለትምህርት በርካታ ጠቀሜታዎችን አስገኝቷል፡፡ ከነዚህም መካከል አንዱ የርቀት ትምህርት ነው፡፡ አንድ ቦታ ባለ በአንድ መምህር መላ አገራችንን በሚያዳርስ ሁኔታ ርቀት ሳይገድበው ብዙ ሺህ ተማሪዎችን ማስተማር ይቻላል፡፡ የተለያዩ ለጥናት የሚረዱ ሰነዶች በኢንተርኔት አማካይነት በቀጥታ ወይም በቴሌ-ማዕከላት ለመምህራን፣ ለተማሪዎችና

ለኀብረተሰቡ በማቅረብ በኩል ጠቀሜታ አለው:: የትምህርት አስተዳደር፣ የትምህርት አሰጣጥ፣ የፈተና ዝግጅት፣ ወዘተ. በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በሚመለከታቸው ክፍሎች መካከል የሃሳብ ልውውጥ ለማድረግ ያስችላል::

ዘመኑ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ ፍጥነት እየጨመረ፣ እውቀት በፍጥነት እየጨመረና እያደገ እንዲሁም የፖለቲካዊ አስተሳሰብና ንቃት እየዳበረ የመጣበት ዘመን ነው:: በዚህ ሁኔታ ውስጥ ብቁ ሆኖ ለመገኘት ትምህርትን በስፋትና በቀጣይነት መስጠት አስፈላጊነቱ እየጨመረ መጥቷል:: ስለሆነም ወደኋላ ላለመቅረት ከዚያም አልፎ ወደኋላ ላለመውደቅ ብዙ ማሳወቅና በተሻለ ጥራት ማስተማር አስፈላጊ ነው::

በሀገራችን አብዛኛው ሕዝብ የትምህርት ቤት በር እንኳን ደርሶ አያውቅም:: በርካታ ወጣቶች ለአንድና ለሁለት ዓመታት ሞክረው በተለያዩ ምክኒያቶች መቀጠል ባለመቻላቸው አቋርጠዋል:: በድምሩ የትምህርት ዕድል ማግኘት ያልቻሉ ዜጎች ብዙ ናቸው:: በአጭር ጊዜ ውስጥ በቂ ትምህርት ቤቶች ለመገንባትና በርካታ ተጨማሪ መምህራን ለመቅጠር አቅም ስለማይኖር ይህ ችግር ለሚቀጥሉት ዓመታትም ይቀጥላል::

ምንም ያህል ጥረት ቢደረግ በተለመደው አሠራር ብቻ ለዜጎች ሁሉ ትምህርትን ማዳረስ አይቻልም:: ትምህርት አሁን ካለበት ጥቂቶችን ብቻ ከሚያሳትፍበት ደረጃ አልፎ በፍጥነት ለብዙዎች መዳረስ አለበት:: ቀስ በቀስም ከብዙዎች አልፎ ለሁሉም ዜጎች የሚዳረስ የትምህርት ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ነው:: የተለመደው የትምህርት አሰጣጥ አንድ መምህር፣ አንድ ክፍል፣ ዓይነት አካሄድ ለዚህ ዓላማ ግብ መምታት ብቻውን ብቁ አይሆንም::

በትምህርት በኩል ያለውን ፍላጎት ለማሟላት ከተፈለገ ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም ጠቀሜታ አለው:: ትምህርት በአራት ግድግዳ ታጥሮ መቅረት የለበትም:: ትምህርት ለሕፃንም ለሽማግሌም፣ ለገጠርም ለከተማም፣ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ማቀፍ አለበት:: ትምህርት ሊደርሳቸው ላልቻሉ ተነጥለው ለሚኖሩ በብዙ ሚሊዮን ለሚቆጠሩ ዜጎች ማድረስ የሚቻለው እንደ ሬዲዮና ቴሌቪዥን በመሳሰሉ መገናኛ ብዙሃንና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ብቻ ነው:: በአሁኑ ጊዜ በዋነኛነት ለፖለቲካዊ ፕሮፓጋንዳ የሚውሉት ሬዲዮና ቴሌቪዥን መማር ለሚፈልጉ ዜጎች ትምህርት በመስጫነት ሊያገለግሉ ይችላሉ፤ ይገባልም:: ሬዲዮና ቴሌቪዥን የሳተላይት ቴሌኮሙኒኬሽንን ጨምሮ በሁሉም የአገራችን አካባቢዎች ትምህርትን ለማሰራጨት እጅግ ጠቃሚ ቴክኖሎጂዎች ናቸው::

የርቀት ትምህርተ በርካታ ጠቀሜታዎች አሉት:: ሬዲዮም ሆነ ቴሌቪዥን በተለመደው አሠራር አንድ መምህር ሊደርስ ከሚችለው ከአንድ ክፍል ተማሪዎች በላይ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ተማሪዎችን መድረስ ያስችላል:: በሬዲዮንና ቴሌቪዥን የሚተላለፉ ትምህርቶችን አነስተኛ የትምህርት ደረጃ ያላቸውም ሆነ ምንም ትምህርት የሌላቸው ሰዎች ሊከታተሉት ይችላሉ:: የርቀት ትምህርት የትምህርት ቤት ግንባታ አያስፈልገውም::

የርቀት ትምህርት የርቀትና የጊዜ መሰናክሎች ይቀርፋል:: የርቀት ትምህርት ተነጥለው ለሚገኙ ሩቅና ጉራንጉር አካባቢዎች ሊደርስ ይችላል:: ከዚያም በላይ ሥራን በማያስተጓጉልና ቀንም ይሁን ማታ ለተማሪዎቹ አመቺ የሆነ ጊዜ መርጦ ማሠራጨት ይቻላል:: የርቀት ትምህርት የሚጠይቀው ወጪ ከተለመደው ትምህርት አሰጣጥ ጋር ሲነፃፀር እጅግ አነስተኛ ነው::

በሬድዮም ሆነ በቴሌቪዥን የሚሰጠው ትምህርት በአማካይ በየትምህርት ቤቱ በክፍል መምህር ከሚሰጠው ትምህርት እጅግ የላቀ ጥራት አለው:: ትምህርቱን የሚያቀርቡት መምህራን ከፍተኛ ሥልጠናና ልምድ ያላቸው፣ በቂ የዝግጅት ጊዜ ያላቸውና በበቂ የትምህርት መርጃ መሣሪያዎች የተደገፉ ናቸው::

የርቀት ትምህርት የተለያዩ ጥቅሞች አሉት:: በተለይም በመደበኛ ትምህርት ቤቶች በቂ ሥልጠና በሌላቸው መምህራን የሚሰጠውን የክፍል ትምህርት አቀራረብ ለማሻሻልና የመምህራኑን የማስተማር ችሎታ ለማሳደግ ይረዳል:: በሬዲዮና በቴሌቪዥን የሚያስተምሩ መምህራንን የማስተማር ጥበብ በመከታተልና ልምድ በመቅሰም በየትምህርተ ቤቶች ያሉ መምህራን ችሎታቸውን ማሳደግ ይችላሉ::

## 7.2.3 ሌሎች የትኩረት አቅጣጫዎች

የተለያዩ አገሮች ልምድ እንደሚያሳየው፣ ኢኮቴ በጤና አገልግሎትም በኩል በርካታ ጥቅሞችን አስገኝቷል:: ለምሳሌ፣ ለሕሙማን በቴሌ-ሜዲስን አማካይነት ከፍተኛ እውቀትና ልምድ ካላቸው ሐኪሞች ጋር በመተባበር የተሻለና የጠለቀ ምርመራና ሕክምና እንዲያገኙ ማድረግ ይቻላል:: በተጨማሪም የጤና ባለሙያዎች ስለበሽታዎችና በሽተኞች ታክመው ስለሚድኑበት ሁኔታ ወቅታዊ የሆነ መረጃና እውቀት እንዲያገኙ ያደርጋል::

ለእርሻ ልማት፣ ለአካባቢ ጥበቃ፣ ለቱሪዝም፣ ለውሃ ልማት፣ ለማዕድን ልማትና ለሌሎች የተፈጥሮ ሀብት የሚውሉ ጠቀሜታ ያላቸው ሥራዎች በኢኮቴ አማካኝነት ማከናወን ይቻላል:: በተለይም በጂኦግራፊያዊ ኢንፎርሜሽን ሥርዓት አማካይነት በርካታ መረጃዎችን በቀላሉ ለማከማቸት፣ ለማቀነባበር፣ለመተንተንና ለማሰራጨት ጉልህ ድርሻ አለው::

ኢኮቴ የምርምር ተቋማት የልምድ ልውውጥ የሚያደርጉበት፣ አስፈላጊም ከሆነ የምርምርና ጥናት ውጤቶችን በተመለከተ ሕትመቶችን የሚያገኙበት የተመቸ ሁኔታ መፍጠር ያስችላል::

## 7.2.4 የኢኮቴ አንፃራዊ ሁኔታ

በ1992 ዓ.ም የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪካ አገሮችን በየአንድ ሺህ ሰው የነበረውን ስልክ፣ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርሻ በንጽጽር ማየት በኢንፎርሜሽንና ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መጠቀም በኩል ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል:: ቴሌፎን መስመርን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ 3 ብቻ ሲሆን በኬንያ 9፣ በሱዳን 3፣ በግብፅ 9 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 18 ነው:: ሞባይልን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያና ሱዳን ወደ ዜሮ የተጠጋ ሲሆን በኬንያ 1፣ በግብፅ 3 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 14 ነው:: እንደዚሁም ቴሌቪዥንን በተመለከተ፣ በኢትዮጵያ 6 ብቻ ሲሆን በኬንያ 22፣ ሱዳን 173፣ በግብፅ 183 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 59 ነው:: ሬዲዮን በተመለከተ ደግሞ፣ በኢትዮጵያ 196 ሲሆን በኬንያ 104፣ ሱዳን 271፣ በግብፅ 160 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 214 ነው::

የኮምፒዩተርና ኢንተርኔት አገልግሎት ድርሻን በተመለከተም ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል:: ፐርሰናል ኮምፑዩተር (የአንድ ሚሊዮን ሰዎች ድርሻ)፣ በኢትዮጵያ 740 ብቻ ሲሆን በኬንያ 4240፣ በሱዳን 2940፣ በግብፅ 1200 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 8770 ነው:: የኢንተርኔት አገልግሎትን በተመለከተ ደግሞ (የአንድ ሚሊዮን ሰዎች ድርሻ)፣ በኢትዮጵያ 10 ብቻ ሲሆን በኬንያ 250፣ በግብፅ 550 እና በአፍሪካ አማካይ ደግሞ 2300 ነው::

## 7.2.5 ፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን

የፖስታና ቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎትን ብቁና ቀልጣፋ ለማድረግ በንግድ ሕግ መሰረት እንዲሰሩና በተወሰነ ደረጃ የራሳቸው ነፃነት እንዲኖራቸው ማድረግና የደንበኞችን ፍላጎት ለማሟላት መጣር አስፈላጊ ነው:: የእነዚህን የአገልግሎት ስርዓት እያደገ ከሚገኘው የሕዝብ ፍላጎትና የአለም አቀፍ ግንኙነት መስፋት ጋር ተወዳዳሪ እንዲሆኑ በሚያስችል መንገድ እንደገና ማዋቀር ይገባል:: ዘርፉ ተወዳዳሪ እንዲሆንና በንግድ ሕግ እንዲመራ በማድረግ ወጪያቸውን ለመሸፈን የሚያግዝ ገቢ መፍጠር ተገቢ ቢሆንም ሁልጊዜም የተገልጋዩ ሕዝብ ጥቅም መጠበቁን ማረጋገጥ ያስፈልጋል::

ለዜናና መረጃ ልውውጥ መቀላጠፍ የሚያገለግል የቴሌኮም ተቋም በማደራጀትና ስራ ላይ በማዋል ሁሉንም የቴሌኮሚኒኬሽን ፋሲሊቲዎች በሰፊው ለማሟላት ጥረት መደረግ ይኖርበታል:: የቴሌኮሙኒኬሽን ፋሲሊቲ ሲባል የቴሌፎን መረብ፣ የሞባይል ስርዓትና የዓለም አቀፍ ሳተላይት ግንኙነትን ሁሉ የሚያጠቃልል ነው:: የመገናኛ መሳሪያዎችንና ሲስተሞችን ለደንበኞች በማቅረብ ረገድ የግል ባለሀብቶችም ተሳትፎ እንዲኖራቸው በማድረግ ዘርፉ በውድድር እንዲንቀሳቀስ በማስቻል የአገልግሎቱን ጥራትና ቀልጣፋነት ማረጋገጥ ይገባል::

የቴሌፎን ግንኙነት በሚዘረጋበት ጊዜ የንግድ ተቋሞችና ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ቅድሚያ የሚያገኙበትን አሰራር መከተል ይገባል። የፖስታ አገልግሎት አሰጣጥ የደንበኞችን እምነትና ተቀባይነት እንዲያገኝ በከፍተኛ ጥንቃቄ መካሄድ ያለበት ሲሆን በተቻለ መጠን ፈጣን እንዲሆን በሚያስችል ብቃት መመራት ይኖርበታል።

## 7.2.6 ትራንስፖርት

እንደ ኢትዮጵያ ያለ ሰፊ የጂኦግራፊ ክልልና በፍጥነት እየጨመረ የሚሄድ ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ያለው አገር ሰፊ የትራንስፖርት መረብ ሊኖረው ይገባል። ሰዎች ለተለያየ ጉዳይ እንዲንቀሳቀሱ ምርታቸውንና አገልግሎታቸውን እንዲያጓጉዙ፣ የሚኖሩበትንና የሚሰሩበትን አካባቢ በቀላሉ ለመምረጥ እንዲችሉ፣ እንዲሁም በመካከላቸው ያለው የኑሮ ሁኔታ ልዩነት እንዲቀራረብ፣ የተጠናከረ የባህል፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ግንኙነት እንዲፈጥሩ በማድረግ ረገድ ትራንስፖርት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል። በስፋት የተዘረጋ የትራንስፖርት ስርዓት ከሌለ የኢንዱስትሪና የንግድ እድገት መፍጠር ቀርቶ ከሕይወት ጋር የተሳሰሩ መሰረታዊ አገልግሎቶችን እንኳ ለዜጎች ማቅረብ አይቻልም።

በሀገራችን ያለው የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ገና ያላደገ መሆኑ በድርቅ ጊዜ ለዜጎች እርዳታ ለማቅረብ እንኳ በማይቻልበት ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ኢንቨስትመንት በሀገሪቱ እንዲስፋፋና የጤና፣ የመጠጥ ውሃ፣ የመብራት፣ የስልክና የትምህርት አገልግሎቶችን ለዜጎች ለማዳረስ ሲፈለግ ትልቁ እንቅፋት የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ደካማ መሆን ነው። የዜጎችን ሰላም ለመጠበቅ፣ ሕግና ስርዓትን ለማስፈንና ቀልጣፋ አስተዳደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሲታሰብ ከባዱ ፈተና የትራንስፖርት መሰረተ ልማት አለመኖር ነው። በገጠርና በከተማ፣ በእርሻና በኢንዱስትሪ፣ በመሀሉና በጠረፉ መካከል ጠንካራ ግንኙነት ለመፍጠር ትልቁ መሰናክል የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ደካማ መሆን ነው። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱን ከባድ ችግር ለማስወገድ በትራንስፖርት መሰረተ ልማት ዘርፍ ሰፊ ርብርብ መደረግ ይገባዋል።

ሀገሪቱ ካላት የትራንስፖርት ዘዴ መካከል የየብስ ትራንስፖርት የመጀመሪያውን ደረጃ የያዘ ነው። ምንም እንኳ እንደየብስ ትራንስፖርት ባይሆንም በተለይ ወደ ውጭ በሚደረግ የጉዞ አገልግሎት መልካም ስም ያለው ታዳጊ የአየር ትራንስፖርት አለ። ብዙ እቃና መንገደኞችን በአንድ ጊዜ ከውጭ ለማስገባትና ከሀገር ለማስወጣት ያለው ጠቀሜታ የማይናቅ ቢሆንም እጅግ ኋላቀር በመሆኑ መሰረታዊ ለውጥ ካልተደረገለት በስተቀር ከፍተኛ ተስፋ ሊጣልበት የማይችል መጠነኛ የባቡር ትራንስፖርት አለ። ሀገሪቱ የነበራትን የተፈጥሮ የባህር በርና እጅግ መጠነ ሰፊ ሀብት አፍስሳ የገነባችውን ወደብ ሕገወጥ በሆነ መንገድ በመነጠቋ በወጪና ገቢ እቃ ማጓጓዝ ትልቅ አስተዋፅኦ የነበረውን የባህር ትራንስፖርት እንዳጣች የሚቆጠር ነው።

አሁን በስራ ላይ ያሉት ሁሉም የትራንስፖርት ዘዴዎች በአብዛኛው (በዋናነት) በመንግስት ባለቤትነት ስር የሚሰሩ በመሆናቸው በውድድር መርህ የሚንቀሳቀሱና ብቁ አገልግሎት ለማቅረብ ብርቱ ጥረት የሚያደርጉ አይደሉም። በዚህ መስክ ያለውን ግዙፍ ችግር ለመቀነስ የግል ባለሀብቶችም በዘርፉ በሰፊው እንዲሳተፉ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ይገባል። የትራንስፖርት መሰረተ ልማት ለማስፋፋት የሚቀየሱ ፕሮጀክቶች ዋነኛ ትኩረት ከተማና ገጠ ርን፣ ጠረፉንና መሀሉን በሚያገናኙ የየብስ መንገዶች ላይ መሆን አለበት። ከዚህ ጎን ለጎን ከየብስና ከአየር ትራንስፖርት ጋር ሲነፃፀር አካባቢን የሚጎዳ ባለመሆኑና በአንድ ጊዜ በርካታ እቃና መንገደኞችን ለማጓጓዝ የሚያስችል በመሆኑ የባቡር ሀዲድ እንዲዘረጋ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል። የአየር ትራንስፖርት ደግሞ አሁን ካለው በበለጠ ነፃና ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲንቀሳቀስ፣ የሀገር ውስጥ አገልግሎቱን እንዲያሰፋና የውጭውንም አጠናክሮ እንዲቀጥል ማድረግ ይገባል። በዚህ አገልግሎት የግል ባለሀብቶችም በሰፊው እንዲሳተፉ በመንግስት የተጣሉ አላስፈላጊ ገደቦች መነሳት አለባቸው።

በገጠር የሚሰራው የየብስ መንገድ ወረዳን ከወረዳ፣ ክልልን ከክልል፣ ወረዳን ከቀበሌና ከክልል የሚያገናኝ ማድረግ ብቻ ሳይሆን በክረምትና በበጋ የማያቋርጥ ደረጃውን የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል። እንዲህ አይነት መንገድ ሲኖር በሰውና በንብረት ላይ የሚደርሰውን ጉዳት

ይቀንሳል:: ለተሽከርካሪዎች ደህንነትና ለመለዋወጫ የሚወጣውን ዋጋ ለመቀነስ ይረዳል:: በክረምትና በበጋ ከሚያገለግሉ የአስፓልትና የጠጠር መንገዶች በተጨማሪ በሕዝብ ትብብር የሚሰሩ መጋቢ መንገዶችም እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል:: የመስኖ ልማት ባለባቸው፣ በግል ባለሀብቶች ሊለሙ በሚችሉ የእርሻ አካባቢዎች፣ አርብቶ አደሩ በሚኖርባቸውና ለሀገሪቱ ደህንነት ጥበቃ ጠቃሚ በሆኑ የጠረፍ አካባቢዎች የየብስ መንገዶች በፍጥነት እያደገ የመጣውን የትራፊክ መጨናነቅና አደጋ ለመቀነስ በሚያስችል ሁኔታ ማዘጋጀት ይገባል::

ለኢንቨስትሜንት በተመረጡ፣ የኢንዱስትሪ ዞን ሆነው በተከለሉና ትላልቅ የገበያ ማዕከላት በሚገኙባቸው አካባቢዎች፣ በስፖርት ማዘውተሪያዎች፣ በኤግዚቢሽን ማዕከላትና በእምነት ስፍራዎች፣ በጤናና በትምህርት መስጫ ተቋሞች አካባቢ የሚያልፉ መንገዶች በተለየ ትኩረት እንዲገነቡ በቂ የመተላለፊያ ስፍራ፣ የመኪና ማቆሚያና የመንገደኞች ማቆያ ኮሪደር ያላቸው ሆነው መገንባት አለባቸው:: በረጅም ጊዜ ሂደት ለሚዘረጉ የከተማ ትራሞችና በኤሌክትሪክ ለሚንቀሳቀሱ የሕዝብ ማጓጓዣዎች ዝውውር በሚበቃ መጠን ስፋት ያላቸው ሆነው መገንባት አለባቸው:: በአጭር ጊዜ ውስጥ እንዳይበላሹ የጥራት ደረጃቸውን ጠብቀውና የተሟላ የፍሳሽ መተላለፊያ እንዲኖራቸው ተደርገው መሰራት ይኖረባቸዋል:: ከባድ ብልሽት ሳይደርስ እድሳትና ጥገና ሊደረግላቸው ይገባል:: የግል ባለሀብቶች በመንገድ አስተዳደር፣ ጥበቃና ግንባታ ተሳትፎ የሚያደርጉበትን ስርዓት ማበጀት ለመንገዶች ደህንነትና ጥራት አንድ ጠቃሚ ዘዴ ነው::

ከቤት ወደቤት ለሚደረግ እንቅስቃሴ፣ ለመዝናኛና ለሌሎችም ማህበራዊ ጉዳዮች የመኪና ትራንስፖርት ከፍተኛ ጥቅም ያለው ቢሆንም ከኢንዱስትሪዎችና ከግል መኖሪያ ቤቶች ከሚወጣው ጭስ ጋር ተዳምረው በአካባቢ ብክለ የሚያደርሱት ጉዳት አለ:: የዚህ ዓይነቱን አደጋ ለመቀነስ አካባቢን በከፍተኛ ሁኔታ የሚበክል ጭስ የሌላቸውን መኪኖች ለሚገዙ የታክስ ቅናሽ በማድረግ ማበረታታት ይገባል:: መንገዶችን በጥራት በመገንባት፣ ወቅቱን የጠበቀ እድሳትና ጥገና በማካሄድ ዘመናዊና ቀልጣፋ አገልግሎት ከማቅረብ በተጨማሪ በየትምህርት ቤቱ የትራፊክ ደህንነት ትምህርት በመስጠትና በቀላሉ ለአደጋ የማይጋለጡ ተሽከረካሪዎች እንዲገዙ በማድረግ ለሰውና ለንብረት ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል:: የአሽከርካሪዎች ማሰልጠኛዎች እንዲስፋፉ ማደፋፈርና በቂ የትራፊክ ተቆጣጣሪዎችን አሰልጥኖ ማሰማራት ብቁ ለሆነ የትራንስፖረት አገልግሎት መኖር መሰረታዊ ጉዳዮች ናቸው::

ለሀገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት አገልግሎት የሚውሉ ተርሚናሎችን ማስፋፋት፣ ለአካባቢ ደህንነት ጉዳት የማያስከትለውንና በተለይም ለረጅም ጉዞና በርካታ ሕዝብ በሰፈረባቸው አካባቢዎች ያለውን የትራንስፖርት ፍላጎት ለማሟላት እጅግ ጠቃሚ የሆነውን የባቡር ትራንስፖርት ማስፋፋት አስፈላጊ ነው:: ሀገሪቱ ወደብ አልባ በመደረጓ የጎረቤት ሀገሮችን ወደቦች በመጠገን፣ የተለያዩ አስተዳደራዊና ፖለቲካዊ ተፅዕኖዎችን በመሸከም ከባድ ችግር ቢኖርባትም ለትራንስፖርት አመቺ በሆነ መንገድ የደረቅ ወደብ አገልግሎትን ማስፋፋት ያስፈልጋል:: የሀገሪቱ የንግድ መርከቦች ከሌሎች ጋር ተወዳዳሪ ለመሆን የሚያስችላቸው አደረጃጀትና አሰራር እንዲኖራቸው፣ ዘመናዊነታቸው እንዲጠበቅና ቀልጣፋ አገልግሎት በመስጠት ታማኝነትና ተቀባይነት እንዲያገኙ ማድረግ ይገባል::

# 8. የአካባቢ ጥበቃ

የተፈጥሮ ሀብቶች የኢኮኖሚ መሠረት ናቸው:: የአነስተኛ አርሶ አደሮች ግብርና፣ በአንዳንድ ቦታዎች ውስጥ የደን ሥራን ጨምሮ፣ ከጠቅላላው የአገር ውስጥ ምርት ወደ 45 በመቶ፣ ከውጭ ንግድ 85 ከመቶ እና ከሥራ ቅጥር 80 ከመቶውን የያዘ ዋነኛ ዘርፍ ነው:: በፖሊሲ ድክመት፣ በእርስ በርስ ጦርነት፣ በተፈጥሮ ሀብት መመናመንና በመሠረተ ልማት ዝቅተኝነት ምክኒያት የግብርና ምርት አለመጨመር በኢኮኖሚ የጠቅላላ የአገር ውስጥ ምርት እድገት ማነስ ዋና መንስኤ ናቸው::

መሠረታዊ የምግብ፣ የመጠጥ፣ የልብስና የመጠለያ ፍላጎቶችን የሚያሟሉት ታዳሽ የተፈጥሮ ሀብቶች እንደ መሬት፣ ውሃ፣ ደኖችና ዛፎች እንዲሁም ሌሎች የብዝሀ ሕይወት ዓይነቶች፣ ጥራታቸው አሽቆልቁሎ ዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ ላይ ደርሰዋል:: በብዙዎቹ የኢትዮጵያ ደጋማ ቦታዎች በአሁኑ ወቅት ያለው የእንጨት ፍጆታ የተፈጥሮ ደኖች ራሳቸውን ከሚተኩበት የምርት መጠን ይበልጣል:: በአብዛኛው በዝናብ የሚጠቀም ግብርናን ለማስፋፋት የሚጨፈጨፈው የደን መሬት መጠን በዓመት ከ20 እስከ 80 ሺህ ሄክታር እንደሚሆን ይገመታል::

ፍግ አፈርን እንዲያዳብር በማድረግ ፈንታ በኩበትነት መቃጠሉ፣ በዓመት ለ 5.5 ሚሊዮን ኩንታል የእህል ምርት ቅነሳ ምክኒያት እንደሆነ ይገመታል:: በሰው ሠራሽ የአፈር መከላት በዓመት ወደ 0.4 ሚሊዮን ኩንታል የሚገመት የእህል ምርት እየጠፋ ነው:: የቤት እንስሳት በገጠርና በብሔራዊ ኢኮኖሚ ውስጥ ከፍተኛ ሚና ይጫወታሉ፣ ይሁንና በየዓመቱ 0.2 ሚሊዮን ሄክታር የግጦሽ መሬት በአፈር መከላት ጠፍቷል:: የመሬት ሀብት መመናመን ከፍተኛ የቤት እንስሳት ምርት ቅነሳ እንደሚያስከትል ሲገመት፣ ሁኔታው ቁጥጥር ካልተደረገበት የምርት ማሽቆልቆሉ የባሰ እየከፋ ይሄዳል::

ከኢኮኖሚ አንጻር ሲታይ፣ እ.አ.አ በ1990 የአፈር መከላት ምክኒያት ሳይገኝ የቀረው የግብርና ምርት (ማለትም አዝመራና የቤት እንስሳት) በዋጋ ሲተመን ወደ 40 ሚሊዮን ብር ሲገመት፣ የእንስሳት ፍግንና አገዳን በማገዶነት የማቃጠል ዋጋ ደግሞ 650 ሚሊዮን ብር ይደርሳል:: በዚሁ ዓመት በአፈር መከላት ሳቢያ ለዘለቄታው የጠፋው የአገሪቷ አፈር ሀብት በዋጋ ሲተመን 60 ሚሊዮን ብር እንደሚሆን ተገምቷል:: የደን መመናመን የዋጋ ስሌት ደግሞ 140 ሚሊዮን እንደሆነ ይገመታል::

ኢትዮጵያ ለመስኖ ግብርናና ለውሃ ኃይል ማመንጫ ካላት ከፍተኛ የውሃ ሀብት 1 ከመቶ ብቻ ጥቅም ላይ ውሏል:: የኃይሉ ዘርፍ ከዓለም በአነስተኛ ደረጃ ከለሙት አንዱ ሲሆን፣ የአገሪቱ የኃይል ፍላጎት 90 በመቶው የሚሟላው ከዕጽዋት ነው:: የኢትዮጵያ የአዝዕርት፣ የብርቅ ዕጽዋትና እንስሳት ዝርዎች ብዛት በሕዝብ ብዛትና በግብርና መስፋፋት ምክኒያት እቀነሰ ነው:: ጥቅም ላይ ሊውሉ የሚችሉ የማዕድን ሀብቶች በመጠንና በጥራት ቢኖሩም፣ በአሁኑ ወቅት የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ከጠቅላላው የአገር ውስጥ ምርት ወደ ሁለት በመቶ ብቻ ነው::

የወቅቱ የከተሞች ሕዝብ መጠን ከአጠቃላዩ የሕዝብ ብዛት 15 ከመቶ ብቻ ነው:: ዓመታዊ እድገቱ ግን 5.4 በመቶ ነው:: በአሁኑ ወቅት የከተሞች መኖሪያ ቤቶች አቅርቦት ብቃት የሌለውና በጣም ዝቅተኛ የጥራት ደረጃ ያለው ነው:: በአዲስ አበባ ውስጥ ከሚገኙት መኖሪያ ቤቶች ከ30 በመቶ የሚበልጡት የንጽሕና መገልገያዎች የሌሏቸው ሲሆኑ፣ በሌሎች ከተሞች ይህ መጠን 50 ከመቶ ገደማ ይሆናል:: የንጽሕና አገልግሎቶች ያለመሟላት፣ ተገቢ የፍሳሽ አገልግሎት መሠረተ ልማቶች አለመኖር በከተሞች ውስጥ እንደፈለጉ መፀዳዳት አደገኛ የጤናና የአካባቢ ችግሮችን ፈጥረዋል:: በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ የከተማ ማዕከሎች አቅራቢያ የሚገኙት ወንዞችና ትናንሽ ጅረቶች እንደ ክፍት የፍሳሽ ቦዮች በማገልገላቸው የተቅማጥና የሌሎች በሽታዎች ዋነኛ ምንጮች ሆነዋል:: በርካታ መፀዳጃ ቤቶች የብዙ ሰዎች የጋራ መጠቀሚያ በመሆናቸውና ብዙውን ጊዜ በር እንኳን ስለማይኖራቸው ለመፀዳዳት አመቺ አይደሉም::

የኢትዮጵያ ከፍተኛ ተፈጥሮአዊና ባህላዊ ቅርሶች በእያንዳንዱ ሰው የዕለት ተዕለት ኑሮ ሁኔታ ውስጥ ዘልቀው ይታያሉ:: በመሆኑም ለብሔራዊ ስሜት ጥንካሬና ለማኅበራዊ ውህደት ኃይል ይሰጣሉ:: ለአገር ጎብኚዎችም ዋና መስህብ መሆን ስለሚችሉ የቱሪስት ኢንዱስትሪን ከማልማት አኳያ እጅግ ጠቃሚ ናቸው:: ሆኖም አብዛኛው ቅርስና ባህል በእንክብካቤ ጉድለት፣ በመስረቅ ወይም በመጎዳት እንዲሁም በግልጽ በማይታዩና በማይዳሰሱ ተለዋዋጭ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶች፣ በባዕድ አመለካከቶችና አገር ውስጥ በገቡ ቴክኖሎጂዎች አማካኝነት በመጎሳቆል ላይ ይገኛሉ::

## 8.1 መከላከልንና ያጠፋ የሚከስበትን መርህ የተከተለ አሰራር

የአካባቢ ጥበቃ መሰረታዊ ከሆኑት የሀገሪቱ ትኩረቶች መካከል አንደኛው ነው:: ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ውሃ፣ አየርና አፈር ለከባድ የብክለት ችግር በመጋለጣቸው የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን የሌሎችም እንስሳትና እፅዋት ሕልውና አደጋ ላይ እየወደቀ ነው:: ይኸንን አደጋ በመገንዘብ ፈጣን የመከላከል እርምጃ መውሰድ ካልተጀመረ ፈታኝ ችግር እንደሚከሰት መጠ ራመር አይቻልም:: የአካባቢ መበከል በራሱ የሚያደርሰው ፈርጀ ብዙ ችግር እንዳለ ሆኖ ሌሎች ችግሮችን እንዲባባሱ በማድረግ ተጨማሪ ጉዳት ማስከተሉ ደግሞ ሌላው አስከፊ ገጽታ ነው::

የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲያችን መከላከልን መሰረት ያደረገ ሆኖ መቃኘት ይኖርበታል። በመንግስት፣ በግል ባለሀብቶችና በሕብረተሰቡ የሚታቀዱ የልማት ፕሮጀክቶች የአካባቢ ችግር የማያስከትሉ መሆናቸው ሲረጋገጥ ብቻ ተግባራዊ የሚሆኑበትን የሕግ ቅጣት የመቀበል ግዴታ መኖሩን የሚያረጋግጥ መሆን አለበት። ከዚህ በተጨማሪ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲያችን በትብብር ላይ የተመሰረተ የጋራ ጥረትን የሚያቀናጅ መሆን አለበት። መንግስት፣ የምርትና የአገልግሎት ተቋሞች፣ ግለሰቦች ሕብረተሰቡ በአጠቃላይ በአካባቢ ጥበቃ ተቀናጅተው የሚንቀሳቀሱበትን የትብብር አሰራር መከተል አለባቸው። ዋነኛው የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲ ትኩረት ሰፊ የማስተማርና የማሳወቅ ስራ መካሄድ እንዳለበት በመገንዘብ በዚህ ጉዳይ ላይ የሕዝቡን አስተሳሰብ ለማሳደግ በሚጠቅም መንገድ ተከታታይ ጥረት ማድረግ ነው።

በሀገራችን ለሚታየው የአካባቢ ብክለት አንዱ መሰረታዊ መንስኤ በአካባቢ ጥበቃ ረገድ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ መሆን ነው። ይህ የግንዛቤ ችግር ሕዝቡን የሚመለከት ብቻ ሳይሆን በመንግስትም በኩል በሰፊው የሚንፀባረቅ ነው። አዳዲስ ፕሮጀክቶች ሲዘጋጁ በአካባቢ ጥበቃ ላይ ያላቸው አሉታዊ ተፅዕኖ ምን እንደሆነ ለመገምገም የሚወሰደው ጥንቃቄ ደካማ ነው። ፕሮጀክቶች በስራ ላይ ከዋሉ በኋላ ጉዳት ማድረሳቸውን ለማወቅ የሚካሄደው ክትትል ደካማ መሆኑ ብቻ ሳይሆን አልፎ አልፎ ጉዳት ማድረሳቸው በታወቀ ሁኔታዎች ላይ ፈጥኖ ለማስተካከል የሚደረግ ሙከራ የለም። ለአፈር ማዳበሪያት፣ ለፀረ ተባይ መከላከያና ማጥፊያነት ጥቅም ላይ የሚውሉ ኬሚካሎች በአፈር፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በውሃና በአየር ላይ ጉዳት የማያስከትሉ መሆናቸው ሳይረጋገጥ ወይም ጉዳቱን ለመቀነስ የሚያስችል የጥንቃቄ ዝግጅት ሳይደረግ በአገልገሎት ላይ ይውላሉ። ለኮንስትራክሽን፣ ለማገዶና ለውጭ ገበያ የሚቆረጡ ዛፎች የሚተኩበት ሕጋዊ ስርዓት ባለመዘጋጀቱ በረሃማነት እየሰፋና የዝናብ እጥረት ችግር እየተባባሰ ነው። ከፋብሪካዎች፣ ከከተሞችና ከመኖሪያ ቤቶች የሚወጡ ጭሶች፣ ደረቅና ፈሳሽ ቆሻሻዎች አየርንና ውሃን እንዳይበክሉ የሚያደርግ የመከላከል እርምጃ ስለሌለ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ላይ ከባድ ጉዳት እየደረሰ ነው።

የመጠጥ ውሃ ጉድጓዶች፣ ሐይቆች፣ ወንዞችና ጅረቶች ለከፍተኛ ብክለት ስለተጋለጡ ከባድ የጤና ችግር እያስከተሉ ነው። በተለይ በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ለአደገኛ የጤና ችግር የተጋለጡ ሆነዋል። ትራፊክ በበዛባቸው ከተሞች ከተሽከርካሪዎች የሚወጣው ጭስና ከፍተኛ ድምፅ በጤና ላይ ከባድ ጉዳት እያደረሰ ነው።

ስለዚህ የአካባቢ ጥበቃ ፖሊሲያችን ለአፈር፣ ለደን፣ ለዕፅዋትና ሰብሎች፣ ለውሃ፣ ለአየር፣ ለእንስሳት ወዘተ ደህንነት መረጋገጥ በሚያስችል መንገድ መቃኘት ይኖርበታል። በተለይም የሰውን ልጅ ጤንነት የሚፈታተን፣ የሌሎችን እንስሳትና ዕፅዋት ሕልውና አደጋ ላይ የሚጥል ብክለት ከመድረሱ በፊት መከላከል ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ነው። ብክለት መድረሱ ሲረጋገጥ ደግሞ ፈጣን የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ ይኖርበታል።

የአካባቢ ጥበቃ ትኩረት በመከላከል ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት ሲባል የሕዝቡን ግንዛቤ ከማሳደግ ጎን በመንግስት በኩል ለዚህ ተግባር ውጤታማነት የሚያገለግሉ ሕጋዊ ስርዓቶች በግልፅ ወጥተው ስራ ላይ መዋል አለባቸው ማለት ነው። የቆሻሽ ማስወገጃ ስርዓቶችን ማሻሻል፣ አገልገሎት ሰጥተው የሚጣሉ ቁሳቁሶች ተመልሰው አገልግሎት ላይ የሚውሉበትን ዘዴ ማዳበር፣ የኬሚካል ማዳበሪያዎችንና ፀረ-ተባይ መከላከያዎችን በማከማቸት ጥቅም ላይ በማዋልና ጊዜ ያለፈባቸውን በማስወገድ ረገድ ያሉትን የጥንቃቄና የአሰራር ችግሮች መፍታት ያስፈልጋል።

በተቆረጡ ደኖች ምትክ አዲስ የመትከልና የመንከባከብ ግዴታን ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል ሕግ ማውጣት ይገባል። ደን በማልማትና በመጠቀም የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ እንዲኖር ማበረታታትና ከአካባቢ ጥበቃ ሕብረተሰቡ ሊጠቀም የሚችልበትን አሰራር መቀየስ ተገቢ ነው። ብሔራዊ ፓርኮች፣ ጥብቅ ደኖች፣ ፍልውሃዎችና ሌሎችም የተፈጥሮ መስህቦች ለቱሪዝም አገልግሎት እንዲውሉ በሚደረግበት ጊዜ ከዚህ አገልግሎት የሚገኘው ገቢ በአብዛኛው መስህቦቹን ለመጠበቅና ለመንከባከብ እንዲውል ማድረግ፣ ያካባቢው ሕዝብ የስራ እድል እንዲፈጠርለትና መተዳደሪያ ገቢ እንዲያገኝ ማስቻል ለአካባቢ ጥበቃ ጠቃሚ ዘዴ ነው። በአጠ ቃላይ ለአካባቢ ጥበቃ የሚረዱ ጥናቶችንና ምርምሮችን የሚያደርግ፣ የመከላከያ ዘዴዎችን

የሚቀይስ፣ ለአካባቢ ጥበቃ የሚረዱ የሕግ ሀሳቦችን የሚያፈልቅ፣ የአካባቢ ጥበቃ ስርዓቶችን ተግባራዊነት የሚቆጣጠር መንግስታዊ ተቋም በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በክልልና በአካባቢ እንዲያውም እስከ ቀበሌ ባሉት የአስተዳደር እርከኖች መዘርጋት ይገባል። መንግስት ለኤድስ፣ ለትምህርት፣ ለሥራ አጥነት ወዘተ. ችግሮች መስጠት ከሚገባው ትኩረት ባላነሰ ሁኔታ ለአካባቢ ጥበቃም ያለበትን ኃላፊነት ተገንዝቦ ከባለሀብቶችና ከሕብረተሰቡ ጋር የተቀናጀ ጥረት ማድረግ አለበት። ሕብረተሰቡ በአጠቃላይና እያንዳንዱ ግለሰብ በተለይ ለአካባቢ ጥበቃ የሚያደርገው ጥንቃቄ ለራሱ ሕይወት የሚደረግ ጥንቃቄ መሆኑን አምኖ በኃላፊነት መንፈስ እንዲንቀሳቀስ ብርቱ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል።